ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

ረቡዕ | 83ኛ ዓመት ቁጥር 142 ጥር 22 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10.00 | ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!






# የበጋ መስኖ ስንዴ ፈታውራሪው

ውብሸት ሰንደቁ

አቶ ወራቦ ዲማ የአምስት ወንድ እና የአምስት ሴት ልጆች አባት ናቸው። በዳውሮ ዞን፣ በገና ወረዳ በዲላሞ ማረቃ ቀበሌ ነዋሪ ናቸው። ልጆቻቸውን ለማሳደግ የሚያመርቱት ምርት አልበቃ ያላቸው፤ አንገታቸውን ደፍተው ለመኖር የተገደዱ አርሶ አደር ነበሩ።

ልጆቻቸውን ትምህርት ቤት ለመላክ እጅ የሚያጥራቸው እና ማኅበራዊ ወጪዎች የሚያሸማቅቋቸው ደሃ አርሶ አደር በመሆናቸው ይቆጫሉ። ልጆቻቸው ጠግበው በልተው እና ትምህርት ሲማሩ ማየት ይመኛሉ። ግን በተለመደው የአኗኗር ዘዬ ይህን ተግባራዊ ለማድረግ እጅግ ፈታኝ ሆኖባቸው እንደቆየ ነው የሚያወሱት።

ለወትሮው በጋ ግፋ ቢል ለጓሮ አትክልት ማልሚያ እንጂ ስንዴ የሚበቅልበት ወቅት ነው ብለው አያምኑም ነበር። በሀገር አቀፍ ደረጃ የበጋ መስኖ ስንዴ ትኩረት እንደተሰጠው ካወቁ ጀምሮ ለምን አልሞከረውም የሚል ሃሳብ አደረባቸው። ካላቸው መሬት ላይ በብርቱ ጥርጣሬ ሩብ ሄክታር ለክተው አረሱ። በእፍኛቸው ዘግነውም ዘሩበት።

ስንዴው ከክረምት ጊዜ አበቃቀሉ ፈጥኖ፤ ከበረዶ ስጋት ድኖ

የበጋ መስኖ... ወደ ገጽ 8 ዞሯል



መንገሻ ፈንታው (ዶ/ር)

## የአማራ ክልል ሠላም ወደ ተሻለ ደረጃ መሸጋገሩን አስታወቀ

ገጽ 8

# መገናኛ ብዙኃን አሰባሳቢ የብሔራዊነት ትርክትን ለመገንባት ትኩረት ሰጥተው መሥራት ይጠበቅባቸዋል

## - የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት ያስገነባውን ዘመናዊ የሚዲያ ኮምፕሌክስ አስመርቋል

ፋንታነሽ ክንዴ

አዲስ አበባ፡- መገናኛ ብዙኃን ብዝኃነትን ባከበረ መልኩ አሰባሳቢ የብሔራዊነት ትርክትን ለመገንባት ትኩረት ሰጥተው መሥራት እንዳለባቸው የኢፌዴሪ ፌዴሬሽን ምክር ቤት አፈጉባኤ አቶ አገኘሁ ተሻገር አሳሰቡ። የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት ያስገነባውን ዘመናዊ የሚዲያ ኮምፕሌክስ ትናንት አስመርቋል።

አቶ አገኘሁ ተሻገር በምረቃ ሥነ-ሥርዓቱ ላይ ባስተላለፉት መልእክት እንዳሉት፤ መገናኛ ብዙኃን ብዝኃነትን ባከበረ መልኩ አሰባሳቢ የብሔራዊነት ትርክትን ለመገንባት ትኩረት ሰጥተው መሥራት አለባቸው።

ኢትዮጵያ የብዝኃ ባህል፣ ማንነት፣ አስተሳሰብና ሃይማኖት ባለቤት መሆኗን እንደ ፀጋ በመቀበል በእኩልነት ማስተናገድ ለሀገራዊ አንድነት ከፍተኛ ፋይዳ አለው ያሉት አፈጉባኤው፤ አገራችን ብሔራዊ አንድነቷ እንዲጠበቅ ብዝኃነትና እኩልነት ሳይነጣጠሉ የሚስተናገዱበት ዓውድ መፍጠር ያስፈልጋል። በዚህ ረገድ መገናኛ ብዙኃን አስተሳሳሪ የብሔራዊነት ትርክት በመገንባት ሂደት የማይተካ ሚና እንዳላቸው ገልጸዋል።

በሕዝቦች መካከል መልካም ግንኙነት እንዲፈጠር የአመለካከትና የሀሳብ ብዝኃነትን ባከበረ መልኩ መሥራት

መገናኛ ብዙኃን... ወደ ገጽ 8 ዞሯል



ፎቶ፡ ዳኜ አበራ

አቶ አገኘሁ ተሻገር



አስሙ ስሜ (ዶ/ር)

# አውቶብሶች

## ፈጣን አገልግሎት እንዲሰጡ ለማድረግ የግል ተሽከርካሪዎች የሚንቀሳቀሱበት ሰዓት ሊገደብ ነው

ቃልኪዳን አሳዬ

አዲስ አበባ፡- በአዲስ አበባ ከተማ በሥራ መግቢያና መውጫ ሰዓቶች የሕዝብ ማመላለሻ አውቶቡሶች ፈጣን አገልግሎት እንዲሰጡ ለማድረግ የግል ተሽከርካሪዎች የሚንቀሳቀሱበትን ሰዓት የሚገድብ አሠራር በቅርቡ ተግባራዊ እንደሚያደርግ የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር አስታወቀ።

አውቶብሶች... ወደ ገጽ 8 ዞሯል








## “ለኢትዮጵያ የባሕር በር ተጠቃሚነት የሌሎች ጎረቤት ሀገራት አማራጮችን ማየት አስፈላጊ ነው”

- ቆስጠንጢኖስ በርኸተስፋ (ዶ/ር)

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡-ኢትዮጵያ የሌሎች ጎረቤት ሀገራትን የባሕር በር ለመጠቀም አማራጮች የማየት መብት አላት ሲሉ መምህርና የፖሊሲ ጉዳዮች አማካሪ ቆስጠንጢኖስ በርኸተስፋ (ዶ/ር) ገለጹ።

ቆስጠንጢኖስ በርኸተስፋ (ዶ/ር) ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ለኢትዮጵያ የባሕር በር ተጠቃሚነት የሌሎች ጎረቤት ሀገራት አማራጮችን ማየት አስፈላጊ ነው።

ከሶማሌላንድ ጋር የተደረገው የመግባቢያ ሰነድ የቀጣናውን የኢኮኖሚያዊ ትስስር የሚያጠናክር መሆኑን አማካሪው ተናግረዋል።

ለኢትዮጵያ የባሕር በር ተጠቃሚነት ጉዳይ በአንድ ላይ ብቻ የሚተው አለመሆኑን የገለጹት ዶክተር ቆስጠንጢኖስ፤ በዲፕሎማሲያዊ መንገድ ከሌሎች ጎረቤት ሀገራት ጋርም በመስማማት የወደብ ተጠቃሚነቱን ማስፋት ያስፈልጋል ብለዋል።

ለኢትዮጵያ የባሕር በር አልምቶ የመጠቀም ሂደት የበርበራና አሰብ ወደቦች ትልቅ አማራጭ መሆናቸውን ጠቁመው፤ የጂቡቲ ወደብን ጨምሮ፣ የሱዳንና፣ የላሙ ወደብ አማራጮችንም ማየት አስፈላጊ መሆኑን አመላክተዋል።

ኢትዮጵያ ከሶማሌላንድ ጋር በፈረመችው የመግባቢያ ስምምነት መሠረት ከሌሎች ጎረቤት ሀገራት ጋርም መስማማት ያስፈልጋል ያሉት አማካሪው፤ አሰብን ለመጠቀም ከኤርትራ ጋር የተጀመረውን ወዳጅነትን ማስቀጠል ተገቢ ነው ሲሉ ተናግረዋል።

ሀገሪቱ ከጎረቤቶች ሀገራት ጋር ያላትን ግንኙነት ይበልጥ ማጠናከር እንደሚያስፈልጋት ገልጸው፤ ከሱማሊያ ጋርም በዲፕሎማሲያዊ መንገድ መነጋገሩ ተገቢ መሆኑንም አስታውቀዋል።

ኢትዮጵያ ከፍተኛ የዲፕሎማሲ ግንኙነትን በማድረግ በመግባቢያ ስምምነቱ መሠረት በበርበራ ወደብ ላይ የምትጠቀምበትን መንገድ ማመቻቸትም እንደሚያስፈልጋት ጠቁመው፤ ከሌሎች ጎረቤት ሀገራት ጋርም ይበልጥ መነጋገርና መስማማት የሚቻልበት ሁኔታ መፍጠር አስፈላጊ መሆኑን አመላክተዋል።

የኢትዮጵያና ሱማሌላንድ ስምምነትን ተከትሎ ሱማሊያ ተቃውሞ ማንሳቷን ያስታወሱት አማካሪው፤ የመግባቢያ ስምምነቱን የሱማሊያ መንግሥት የሚቀበልበትን ዲፕሎማሲያዊ ሁኔታ መፍጠር አስፈላጊ መሆኑን ጠቁመዋል።

ኢትዮጵያ ሱማሊያን ለማረጋጋት ከፍተኛ ዋጋ በመክፈል በርካታ የውይይት መድረኮችን ማዘጋጀቷን ገልጸው፤ አሸባሪዎች ሲቆጣጠሯት ወታደሮችን በመላክ የውድ ልጆቿን ደም ዋጋ የከፈለችና አሁንም እየከፈለች መሆኑን አስረድተዋል።

የባሕር ኃይል ጉዳይ ለኢትዮጵያ የባሕር ጥቅሞቿን ማስጠበቅ እንድትችልና ከሌሎች ሀገር ፈቃድ ተላቃ ራሷ እንድትጠቀም የሚያስችል በመሆኑ በራስ አቅም የምንጠቀምበት ወደብ አስፈላጊ ነው ብለዋል።

የአፍሪካ ኅብረትም እየተሠራ የሚገኘው የኢኮኖሚ ትስስር የተለያዩ ሀገራት ነፃ የኢኮኖሚ ግንኙነትና ቁርኝት እንዲኖራቸው ዕድል የሚፈጥር መሆኑን ተናግረው፤ ትስስር ኢትዮጵያ ለጂቡቲ የምትከፍለውን በቢሊዮን የሚቆጠር ዶላር በመቀነስና በባሕር በር ጉዳዮች ተሳታፊ ሆና ልትሠራበት የምትችልበት ሁኔታን ማጠናከር የሚያስችል መሆኑን አስረድተዋል።

# የፀረ-ሙስና ትግልን ውጤታማ ለማድረግ የሚረዳ የአመራር ሥነ-ምግባር ሥልጠና ይሰጣል

**አማን ረሺድ**



አዲስ አበባ፡- የፀረ-ሙስና ትግሉን ውጤታማ ለማድረግ የሚረዳ የአመራር ሥነ-ምግባር ሥልጠና እንደሚሰጥ የፌደራል ሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽንና የአፍሪካ አመራር ልህቀት አካዳሚ አስታወቁ።

የፌዴራል ሥነ-ምግባርና ጸረ-ሙስና ኮሚሽን እና የአፍሪካ አመራር ልህቀት አካዳሚ በጋራ መሥራት የሚያስችላቸውን ስምምነት ትናንትና አድርገዋል።

የፌዴራል ሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር ሳሙኤል ኡርቃቶ(ዶ/ር) በወቅቱ እንደገለጹት፤ የተደረሰው ስምምነቱ በመንግሥት፣ በልማት ድርጅቶችና በሕዝባዊ ተቋማት ውስጥ የሚገኙ አመራሮችና ሠራተኞች ሥነ-ምግባር የተላበሱና ሙስናን የሚታገሉ እንዲሆኑ የሚያስችል ነው።

በስምምነቱ መሠረት ኮሚሽኑ ከአፍሪካ አመራር ልህቀት አካዳሚ ጋር በመተባበር የአመራር ሥነ-ምግባር ማሠልጠኛ ማዕከል ይገነባል ብለዋል።

በአካዳሚው የሚገነባው ማዕከል በአንድ ዓመት ውስጥ የሚጠናቀቅ ሲሆን፤ አመራሮች ጠንካራ የሥነምግባር ስብዕና እንዲኖራቸውና ኃላፊነታቸውን መወጣት እንዲችሉ ይረዳል ሲሉ አመላክተዋል።

የትብብር ስምምነት መደረጉ በሁለቱ ተቋማት መካከል ያለውን ሀብት ያለብክነት በመጠቀም ውጤታማ የጸረ-ሙስና ትግል ለማከናወን እንደሚረዳ አመላክተዋል።

በሚገነባው የሥልጠና ማዕከል የአመራሮችን የሥነ-ምግባር ጉድለት ችግሮች የሚያሻሽሉ ዝርዝር ጥናቶችን ለማካሄድና የአመራሮችን የሥነ-ምግባር ልዕልና የሚያሻሽሉ ትምህርቶችን ለማቅረብ የሚያስችል መሆኑን ኮሚሽነሩ ጠቁመዋል።

በአካዳሚው ውስጥ የሚገነባው ማዕከል ሲጠናቀቅ የተለያዩ የአቅም ማጎልበቻ ሥልጠናዎች መስጠት ያስችላል ያሉት ኮሚሽነሩ፤ ሙስናን የሚጠየፍ አመራር የመፍጠሩ ተግባር ቀጣይነት ባለው ሁኔታ ይሠራል ብለዋል።

የአፍሪካ አመራር ልህቀት አካዳሚ ርዕሰ አካዳሚ አቶ ዛዲግ አብርሃ በበኩላቸው፤ ስምምነቱ ሁለቱ ተቋማት ውጤታማና ግልጽ አሠራር እንዲኖራቸው የሚያግዝ ነው ሲሉ ተናግረዋል።

አካዳሚው በሀገር አቀፍ ደረጃ መልካም ሥነ-ምግባር የተላበሰ አመራር ለማፍራት እየሠራ እንደሚገኝ ገልጸው፤ ከኮሚሽኑ ጋር ተባብሮ በመሥራት አስተዳደራዊ ችግሮችን ለመቅረፍ እንደሚሠራ ጠቁመዋል።

የተለያዩ ተቋማት ማዕከላትን በአካዳሚው እየከፈቱ መሆናቸውን ጠቅሰው፤ ይህም አካዳሚው በተለያዩ ኃላፊነት ቦታዎች ላይ ብቁ አመራሮችን ለማፍራት ያግዛል ብለዋል።

በሀገር ውስጥ መልካም ሥራዎች እየተሠሩ መሆናቸውን ጠቅሰው፤ የተገኙ ወጤቶች ቀጣይነት እንዲኖራቸው ሁሉም ተቋማት ሥነ-ምግባርና ሐቀኝነትን መርሕ አድርገው መሥራት እንደሚገባቸው አቶ ዛዲግ ተናግረዋል።

# ሜዲካል ኮሌጁ በቀጣይ 5 ዓመታት ወደ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅነት ያድጋል

**ዮርዳኖስ ፍቅሩ**




አዲስ አበባ፡- የካቲት 12 ሆስፒታል ሜዲካል ኮሌጁን በቀጣዮቹ 5 ዓመታት ወደ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅነት ለማሳደግ እየተሠራ መሆኑ ተገለጸ።

የሆስፒታሉ የአስተዳደርና ልማት ምክትል ፕሮቮስት አቶ ዓለሙ ክብረት ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ኮሌጁ ከጥቂት አንጋፋ የጤና ተቋማት መካከል አንዱና በየዘመናቱ ለጤናው ዘርፍ የበኩሉን አስተዋፅዖ ሲያደርግ የቆየ ነው።

ባለፈው ዓመት 100 ዓመት የሞላው የካቲት 12 ሆስፒታል ሜዲካል ኮሌጅ፣ አሁን ደግሞ በተለየ ሁኔታ እድሜውንና ስሙን የሚመጥን አገልግሎት ለመስጠት የ10 ዓመታት ስትራቴጂክ እቅድ አውጥቶ ለስኬቱ እየሠራ ይገኛል ብለዋል።

ኮሌጁን በሚቀጥሉት 5 ዓመታት ወደ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅነት ለማደግም በሕክምናና በትምህርቱ ዘርፍ የሚሰጠውን አገልግሎት በየጊዜው በማስፋትና በማዘመን ላይ ነው።

ከ13 ዓመታት በፊት በመሠረታዊነት ከሚሰጠው የሕክምና አገልግሎት በተጨማሪ የሕክምና ሙያ ትምህርትንም እንዲሰጥ የተደረገው ሜዲካል ኮሌጁ፣ የማስተማር አገልግሎቱ ከጀመረ ወዲህ ለጤናው ዘርፍ በርካታ ብቁ የጤና ባለሙያዎችን እንዳበረከተ ጠቁመዋል።

ይህን አገልግሎቱን የበለጠ በማስፋት በየጊዜው በተለያዩ የትምህርት ዘርፎች ተማሪዎችን እየተቀበለና እያስተማረም ይገኛል ሲሉም ተናግረዋል።

ዘመናዊነትን መላበስን ጨምሮ ትኩረት ልንሰጥባቸው የሚገቡ የትኩረት አቅጣጫዎችን ለይተናል ያሉት አቶ ዓለሙ፣ በሕክምናውም ሆነ በትምህርቱ ዘርፍ እያገለገለው ያለው መላው ሠራተኛ ለተቋሙ እድገት የበኩሉን እየተወጣ እንደሚገኝም አስታውቀዋል።

የሜዲካል ኮሌጁ የድንገተኛና የጽኑ ሕሙማን ስፔሻሊስት ሐኪምና የሕክምና አገልግሎት ምክትል ፕሮቮስት ዶ/ር አንተነህ ምትኩ በበኩላቸው፣ የካቲት 12 ሆስፒታል ሜዲካል ኮሌጅ ስሙንና እድሜውን የሚመጥን አገልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኝ ተቋም መሆኑን አንስተዋል።

የሕክምና አገልግሎት ላይ ያሉ ማነቆዎችን ለመፍታት የሚያግዙና ሥራን በጥራትና በቅልጥፍና ለማከናወን የሚያስችሉ የተለያዩ ሪፎርሞችን እየተገበረ እንደቆየም አመላክተዋል።

እርሳቸው እንዳሉት፣ ሆስፒታል ኮሌጁ 39 የሚደርሱ የሕክምና ዘርፎች ሲኖሩት፣ በዓመት ለ500ሺ ያህል ሰዎች የሕክምና አገልግሎት ይሰጣል።

በሕክምና ትምህርት ዘርፍም በዓመት እስከ 1500 ተማሪዎችን በሕክምና የመጀመሪያ ዲግሪ ጀምሮ እስከ ሰብ ስፔሻሊቲ ድረስ እያስተማረ ሲሆን ይህን አገልግሎት ለመስጠት 2300 የሚደርሱ ሠራተኞች አሉት ብለዋል።

ከእነዚህ ውስጥ 1400ው የጤና ባለሙያዎችና የሕክምና አገልግሎቱን የሚያግዙ ሠራተኞች መሆናውንም አብራርተዋል።

ኮሌጁ በሁሉም ዘርፎች የሚሰጠውን አገልግሎት በማስፋትና በማዘመን ጥራቱን የጠበቀና ጊዜውን የዋጀ ዘመናዊ አገልግሎት በመስጠት በሚቀጥሉት 5 ዓመታት ወደ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅነት የማደግ ርዕይ ሰንቆ እየሠራ ይገኛል።

## ስደተኞች የዲጂታል...

ከ8ኛው ገጽ የዞረ

የዓለም አቀፉ የሥራ ድርጅት ቢሮ ዳይሬክተር አሌክሲዮ ሙሲንዶ በበኩላቸው፤ በዲጂታል ኢትዮጵያ 2025 ስትራቴጂ መሠረት ትኩረት ሰጥታ እየሠራች ነው።

ኢትዮጵያ ከደቡብ ሱዳን፣ ሶማሊያና ኤርትራ የተውጣጡ ከ916 ሺህ በላይ ስደተኞችን እያስተናገደች መሆኑን አንስተው፤ ስምምነቱ ሴቶችን፣ ወጣቶችን ጨምሮ ስደተኞችንና የተገለሉ ቡድኖች የበይነ መረብ ተደራሽ ለማድረግ እንደሚያስችል ገልጸዋል።

የዲጂታል መሠረተ ልማትና ትስስር ለአካታች የዲጂታል ኢኮኖሚ ያለው ጠቀሜታ የጎላ መሆኑን ጠቅሰው፤ የመግባቢያ ስምምነቱ ስደተኞችና ሌሎች ማኅበረሰቦችን በዲጂታል ኢኮኖሚ ለማካተት የሚያስችል መሆኑን ተናግረዋል።

ስምምነቱ የዲጂታል ክህሎት አካታች ስትራቴጂ ጥናት፣ በዘርፉ የቴክኒክ ሥልጠና ለማከናወንና በዲጂታል ኢኖቬሽን ማዕከል ግንባታ ዙሪያ በጋራ መሥራት የሚያስችል መሆኑ ተመላክቷል።


ፎቶ፡ በሐዱሽ አብርሃ

ኮሚሽነር ልዕልቲ ግደይ

# በኅብረት ሥራ ማኅበራት ተጠያቂነት የሚፈጥር አሠራር ባለመኖሩ በርካታ ሀብት እየባከነ ነው

**ሞገስ ተስፋና ሙሉቀን ታደገ**

<u>አዲስ አበባ</u>፡- በኅብረት ሥራ ማኅበራት ተጠያቂነት እንዲኖር የሚያስችል የአሠራር ሥርዓት ባለመኖሩ በርካታ ሀብት እየባከነ መሆኑን የአዲስ አበባ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን ገለጸ፡፡

በኅብረት ስራ ማኅበራት ላይ ተጠያቂነትን ለማስፈን የሚያስችል አሠራር እየተዘረጋ መሆኑ ተጠቁሟል።

የአዲስ አበባ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን ኮሚሽነር ልዕልቲ ግደይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የኅብረት ሥራ ማኅበራት ከተቋቋሙ በርካታ ዓመታትን ቢያስቆጥሩም በማኅበራቱ ላይ ተጠያቂነት እንዲኖር የሚያስችል የአሠራር ሥርዓት ባለመኖሩ በዕድሜያቸው ልክ ውጤታማ አይደሉም፡፡

ከዚህ በፊት ባለው አሠራር ኅብረት ሥራ ማኅበራት ተጠሪነታቸው ለንግድ ቢሮ በመሆኑ ከማኅበር ይልቅ የነጋዴነት ባሕሪ በመላበሳቸው ለበርካታ የሀብት ብክነትና የአሠራር ብልሽት ተዳርገው ቆይተዋል ብለዋል፡፡

ሸማች ማኅበራት ሥርዓት ሳይበጅላቸው ወደ ሥራ በመግባታቸው ኪሳራና ምዝበራ ደርሶባቸዋል ሲሉ አስረድተው፤ ለመግለጽ የሚያዳግት በርካታ ሀብት በመባከኑ ሲጠቀሙባቸው የነበሩ አባሉ ሳይሆን ግለሰቦች እንደነበሩ አንስተዋል።

የኅብረት ሥራ ማኅበራት የተቋቋሙበትን ዓላማ ይዘው እንዲቀጥሉ በአሠራር፤ በአደረጃጀት በሕግና አሠራር ተደግፈው እንዲሠሩ ደንቦችና መመሪያዎች እየተዘጋጁ መሆኑን አስታውቀዋል።

በዘርፉ ሪፎርም ከተጀመረ በኋላ በፍጥነት ከተከናወኑ ጉዳዮች መካከል ሸማቾችንና ዩኒየኖችን ኦዲትና ኢንስፔክሽን የማድረግ ሥራ ይገኝበታል ብለዋል።

ኢንስፔክሽን ተደርጎ የተገኘውን ግኝት ሲታይ በገንዘብና በንብረት ብክነቶች እንዲሁም ብልሹ አሠራሮች መገኘታቸውን አመላክተዋል፤ በቂርቆስ፤ በጉለሌና በተለያዩ ክፍለ ከተሞች አሠራሩ ከሚፈቅደው ውጪ ሲሠሩ መገኘታቸውን ጠቁመዋል፡፡

በዚህም በሚሊዮኖች የሚቆጠር ገንዘብ ግብይት መፈጸሙንና ተጠያቂነትን ለማስፈን በተወሰደው ርምጃ ከዩኒየን አመራር እስከ ቦርድ አመራር በየደረጃው ከሥራ የማገድ፤ የገንዘብ ቅጣትና በሕግ የመጠየቅ ርምጃ ተወስዷል ሲሉ አስረድተዋል። ፡፡

ዩኒየኖችና የኅብረት ሥራ ማኅበራት አመራሮች በኢንስፔክሽን ግኝት መሠረት ቢፈተሹ አንድም አካል ከተጠያቂነት አይተርፉም ያሉት ወይዘሮ ልዕልቲ፤ ቢያንስ የችግሩን መጠንና ደረጃ ለማወቅ የኢንስፔክሽን ሥራ ተሠርቷል ብለዋል፡፡

የዩኒየኖች እና ኅብረት ሥራ ማኅበራቱን ኢንስፔክሽን ተሠርቶ ሲታይ አስደንጋጭ ነው፡፡ ስለሆነም ይህን የኢንስፔክሽን ግኝት ቢያንስ ለሪፎርም ሥራ እንደ ግብዓት በመውሰድ ቀጣይ እንዳይደገም እየተሠራ ነው ሲሉ ተናግረዋል።

እንደ ወይዘሮ ልዕልቲ ገለጻ፤ የከፋ ችግር ባለባቸው ላይ በቀጣይ አባላቱ እንዲያውቁት በማድረግ ዩኒየኖቹም ሆነ ማኅበራቱ ሥራቸውን እንዳይቀጥሉ ይደረጋል፡፡

ሕጋዊው አሠራር ተግባራዊ ሲደረግ ከዚህ በፊት የነበረው ችግር ይቀረፋል፤ ለዚህ ደግሞ በቴክኖሎጂ የታገዙ ለማድረግ በትኩረት እየተሠራ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

በዚህና ሌሎች ጉዳዮች ዙሪያ ከወይዘሮ ልዕልቲ ግደይ ጋር ያደረግነው ሙሉ ቃለ ምልልስ በተጠየቅ ዓምዳችን ላይ ያገኙታል፡፡

# በማዕድናት ሀብቶች የሚስተዋለው ሕገ-ወጥ ንግድ ዘርፉን እየፈተነው ይገኛል

## - 3 ነጥብ 51 ሚሊዮን ቶን ሲሚንቶ ተመርቷል

**ሄለን ወንድምነው**


ፎቶ ገበየሁ ገብሬ

ኢንጅነር ሀብታሙ ተገኝ

<u>ሱሉልታ</u>፡- በማዕድን ሀብቶች የሚስተዋለው ሕገ-ወጥ ንግድና በአንዳንድ አካባቢዎች የሚፈጠሩ የፀጥታ ችግሮች ዘርፉን እየፈተነው መሆኑን የማዕድን ሚኒስቴር አስታወቀ።

በ2016 በጀት ዓመት ስድስት ወራት ሦስት ነጥብ 51 ሚሊዮን ቶን ሲሚንቶ መመረቱንና በማዕድን ዘርፍ ለ95 ሺህ ዜጎች የሥራ ዕድል እንደተፈጠሩ ተመላክቷል።

ማዕድን ሚኒስቴር የ2016 በጀት ዓመት የስድስት ወር የዕቅድ አፈጻጸምን ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ትናንት ገምግሟል።

የማዕድን ሚኒስትር ሀብታሙ ተገኝ (ኢ/ር) በወቅቱ እንደገለጹት፤ ኢትዮጵያ የበርካታ ማዕድን ሀብቶች ባለቤት ብትሆንም ከዘርፉ በሚፈለገው ደረጃ ተጠቃሚ መሆን አልቻለችም።

ሕገ-ወጥ ንግድ፣ በሀገሪቱ አንዳንድ አካባቢዎች የሚፈጠሩ የፀጥታ መደፍረሶች እንዲሁም ለማዕድን ሃብት ያለው የግንዛቤ ማነስ፣ በቂ የሰው ኃይል እጥረት፣ በቂ የልማት በጀትና ቴክኖሎጂ አለመኖሩ ሀገሪቱ በማዕድን ሀብቱ በተሻለ ተጠቃሚ መሆን እንዳትችል አድርጓታል ሲሉ አስረድተዋል።

ከፍተኛ የሆነ የማዕድን ምርት ያላቸው አካባቢዎች በሕገወጥ መልኩ ለገበያ የሚያቀርቡ አካላት በመኖራቸው የሚፈለገውን ገቢ እንዳይገኝ ማድረጉን ገልጸው፤ ሕገወጥነትን ለመከላከል ሁሉም ባለድርሻ አካላት ርብርብ ሊያደርጉ ይገባል ብለዋል።

በዘርፉ የሚስተዋሉትን ችግሮች ለመፍታት ሁሉንም ባለድርሻ አካላት ያካተተ ብሔራዊ ካውንስል ተቋቁሞ እየተሠራ መሆኑን ጠቁመው፤ በቀጣይ በሚፈለገው ደረጃ ተጠቃሚ ለመሆን ዓለም አቀፍ ኢንቨስተሮችን የማሳተፍ ሥራና ሕገወጥነትን የመከላከል ሥራ ተጠናክሮ እንደሚቀጥል አመላክተዋል።

በ2016 በጀት ዓመት ሥራ ላይ ያሉት 11 የሲሚንቶ ፋብሪካዎች መሆናቸውን ገልጸው፤ ፋብሪካዎች በዓመት 14 ሚሊዮን ቶን ሲሚንቶ የማምረት አቅም እንዳላቸው ተናግረዋል።

ዓመታዊ የሀገር ውስጥ ሲሚንቶ ፍላጎት 36 ሚሊዮን ቶን ነው ያሉት ሚኒስትሩ፤ በበጀት ዓመቱ ስድስት ወራት ሦስት ነጥብ 51 ሚሊዮን ቶን ሲሚንቶ ተመርቷል ብለዋል።

በበጀት ዓመቱ ስድስት ወራት የማዕድን ኢንዱስትሪ ምርትን ለማሳደግ በተሠራው ሥራ 143 ሺህ 458 ቶን ብረት፣ 273 ሺህ የድንጋይ ከሰል መገኘቱን አስታውቀዋል።

የግንባታ ግብዓት እጥረቶችን ለመፍታት ምርት ያቆሙ የሲሚንቶ ፋብሪካዎችን ወደሥራ የማስገባት ሥራ እየተሠራ መሆኑን ተናግረዋል።

በኩባንያዎችና በኢንዱስትሪዎች አማካኝነት ለ145 ዜጎች እንዲሁም በባሕላዊ አምራች ኢንተርፕራይዞች ለ94 ሺህ 997 ዜጎች የሥራ ዕድል መፈጠሩን ጨምረው ገልጸዋል።

በሌላ በኩል በስድስት ወራት ለውጪ ገበያ ከቀረቡ የማዕድናት ምርቶች 243 ነጥብ 24 ሚሊዮን ዶላር ለማግኘት ታቅዶ 142 ነጥብ 978 ሚሊዮን ዶላር ገቢ መገኘቱን አመላክተዋል።

ገቢው የተገኘው በዋናነት ከወርቅ፣ ከታንታለም፣ ከሊቲየም ኦር፣ ከጌጣጌጥና የኢንዱስትሪ ማዕድናትን መሆኑን አስታውቀዋል።

# ሚኒስቴሩ በከተሞች የቤት አቅርቦት ችግርን ለመቅረፍ በትኩረት እንዲሠራ ምክር ቤቱ አሳሰበ

**ማርቆስ በላይ**

<u>አዲስ አበባ</u>፡- የከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስቴር በከተሞች የቤት አቅርቦት ችግርን ለመቅረፍ የጀመራቸውን ሥራዎች በትኩረት እንዲሠራ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አሳሰበ፡፡

ስድስተኛው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሦስተኛ ዓመት የሥራ ዘመን በ12ኛ መደበኛ ስብሰባው የከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስቴርን የግማሽ ዓመት እቅድ አፈጻጸም ገምግሟል፡፡

በወቅቱ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የከተማ መሠረተ ልማትና ትራንስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ ወይዘሮ ሸዊት ሻንካ፤ በከተሞች እየጨመረ የመጣውን የሕዝብ ቁጥር ታሳቢ በማድረግ የቤት አቅርቦት ችግርን ለመቅረፍ የተጀመሩ ሥራዎች ተጠናክረው ሊቀጥሉ እንደሚገባ አመላክተዋል።

በከተሞች ዘመናዊ የማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት ሥርዓት ተግባራዊ ሊደረግ እንደሚገባም የምክር ቤት አባላት አንስተዋል። አዲስ አበባን ጨምሮ የተለያዩ ከተሞችን ለነዋሪዎች ምቹና ሳቢ ለማድረግ የተጀመሩ ሥራዎች ተጠናክረው መቀጠል እንዳለባቸው ጠቁመዋል።

የፕሮጀክቶች መጓተትና የመንገድ ግንባታዎች በወቅቱ ያለማከናወን ችግር ሊቀረፍ እንደሚገባም የምክር ቤቱ አባላት ተናግረዋል።

የከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስትር ወይዘሮ ጫልቱ ሳኒ በበኩላቸው የተቋማቸውን የስድስት ወር አፈጻጸም ባቀረቡበት ወቅት እንደገለጹት፤ በከተሞች የአገልግሎት አሰጣጥ ከነዋሪዎች የሚነሱ ቅሬታዎችን በመፍታት የተገልጋዩን እርካታ ለማረጋገጥ እየተሠራ ነው፡፡



በግማሽ ዓመቱ በመንግሥት አስተባባሪነት ደረጃቸውን የጠበቁ ሦስት ሺህ 647 የመንግሥት የኪራይ ቤቶች ግንባታ ተከናውኗል ያሉት ሚኒስትሯ፤ በግሉ ዘርፍ 75 ሺህ ቤቶችን መገንባት ተችሏል ብለዋል፡፡

በአዲስ አበባ በመንግሥትና በግል አጋርነት የ60 ሺህ ቤቶች ግንባታን ለመጀመር የቅድመ ዝግጅት ሥራ መሠራቱን ገልጸው፤ በፕሮግራሙ መንግሥት መሬት የሚያቀርብና ባለሀብቱ ፋይናንስና ቴክኖሎጂ በማቅረብ ግንባታቸው የሚከናወን መሆኑን አስረድተዋል።

በአዲስ አበባ 654 ሺህ የመሬት ፋይሎችን በዘመናዊ ሥርዓት በመመዝገብ አገልግሎቱን በዲጂታል ሲስተም ለመያዝ እየተሠራ መሆኑን ጠቅሰው፤ በአዳማ ከተማ ተመሳሳይ የዲጂታላይዜሽን ሥራ ለማከናወን ዝግጅት መደረጉን ገልጸዋል፡፡

በሚኒስትር መሥሪያ ቤቱ የከተሞችን ማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎትን ዘመናዊና ውጤታማ ለማድረግ እየተሠራ ነው ያሉት ወይዘሮ ጫልቱ፤ በከተሞች አገልግሎት አሰጣጥ ላይ የሚነሱ ቅሬታዎችን ለመፍታት የሚያስችሉ ሥራዎች በመሠራት ላይ ይገኛሉ ብለዋል፡፡

በከተሞች የማዘጋጃ ቤታዊ ገቢ 17 ነጥብ ሦስት ቢሊየን ብር ለመሰብሰብ ታቅዶ 18 ነጥብ 28 ቢሊዮን ብር ተሰብስቧል ያሉት ወይዘሮ ጫልቱ፤ በከተሞች የምግብ ዋስትና ፕሮግራም አንድ ነጥብ 74 ቢሊየን ብር ለተጠቃሚዎች ማስተላለፍ እንደተቻለ አስታውቀዋል፡፡

በተጨማሪ ከወሰን ማስከበርና ከካሣ ክፍያ ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን በመለየት 45 ነጥብ 39 በመቶ ቅሬታዎችን መፍታት መቻሉን ገልጸው፤ በመንገዶች ግንባታ፣ ዕድሳት፣ ደረጃ ማሻሻልና በፍጥነት መንገድ 380 ኪሎ ሜትር ግንባታ መከናወኑን አስረድተዋል።

በተጨማሪም የተለያዩ ፕሮጀክቶች በፀጥታ ችግር፣ በሲሚንቶ አቅርቦት እጥረት የተነሳ መቆማቸውንና መጓተታቸውን ጠቅሰው፤ የሥራ ተቋራጮችና አማካሪ ድርጅቶች የመፈጸም አቅም ማነስና የውጭ ምንዛሪ እጥረቱን ለመፍታት ከባለድርሻ አካላት ጋር በትብብር እየተሠራ መሆኑንም አመላክተዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## እንኳን ደስ ያለዎት፤ ያለን!

የአንድ መሪ ስኬታማነት መመዘኛው ለሚመራው ሕዝብና ሀገር የሚጨበጥ ለውጥ በማምጣት የተሻለ ተጠቃሚነትን ማስፈን ነው። ለዚህም ነው በምርጫ ሰሞን የተፎካካሪ ፓርቲዎች የምረጡኝ ቅስቀሳ በአብዛኛው ብትመርጡኝ ይህን እና ይህን አደርጋለሁ! ፤ ይህን እና ይህን እለውጣለሁ ! .. ወዘተ በሚሉ ንግግሮች የተሞሉ የሚሆኑት ።

ምርጫ አማራጮችን መሠረት አድርጎ የሚከናወን ከመሆኑ አንጻር በሂደቱ የሚደረጉ የምረጡኝ ቅስቀሳዎች ልብ አማላይና በተስፋዎች የተሞሉ መሆናቸው የሚጠበቅ ነው። መራጩም ሕዝብ የምርጫ ካርዱን የሚጥለው ተስፋው ተጨባጭ ነው ብሎ ላመነበት ብቻ ሳይሆን፤ ቃሉን የመፈጸም አቅም አለው ብሎ ለሚያምነውም ጭምር ነው።

በእኛም ሀገር የዛሬ ሦስት ዓመት ከምርጫ ጋር በተያያዘ አዲስ ታሪክ መፍጠር ያስቻለ ክስተት ተፈጥሯል። የለውጥ ኃይሉ ራሱን የለውጥ መንግሥት አድርጎ ለማስቀጠል ባደረጋቸው የምረጡኝ ቅስቀሳዎች ብዙ ሀገር አሻጋሪ ተግባራትን በመሥራት ሀገርና ሕዝብን ተጠቃሚ ለማድረግ ቃል ገብቷል። የገባቸው ቃሎችም በአብዛኛው ኢትዮጵያዊ ልብ ውስጥ ስፍራ በማግኘታቸው በምርጫው አሸንፎ ወደ ሥልጣን መጥቷል።

ለውጡ እንደ አንድ ሀገራዊ ትርክት ለዋጭ ለውጥ፤ በብዙ ፈተናዎች ውስጥ ለማለፍ የተገደደበት ሁኔታ ተፈጥሯል ፤ ፈተናው ለውጡን ብቻ ሳይሆን ሀገርን እንደሀገር የሕልውና ፈተና ውስጥ እስከ መክተት የደረሰ አደጋ ሆኖ የተከሰተበትም እውነታ የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው ።

ይህን አደጋ ለመቀልበስ የተደረጉ ጥረቶች ከፍ ያለ ቁርጠኝነትና የዓላማ ጽናትን የጠየቁ፤ የለውጥ ኃይሉን በሁለንተናዊ መንገድ የፈተኑ ናቸው፤ ከውጪም ከውስጥም የተፈጠሩ ጫናዎች ለታሪካዊ ጠላቶቻችን ሳይቀር እንደ አንድ ትልቅ ታሪካዊ አጋጣሚ ተወስደው ከፍ ያለ ርብርቦሽ የተደረገባቸው ናቸው።

የለውጥ ኃይሉ ይህንን በብዙ መልኩ ከተገማችነት ያለፈ ፈተና ለመሻገር በአንድ በኩል ለራሱ፤ በሌላ በኩል ለሕዝብ የገባውን ቃል ተጨባጭ ለማድረግ ብዙ የተጎረባበጡ መንገዶችን፤ ለጉዞ የማይመቹ ኮረብታዎችን ለመጓዝ ተገድዷል። ጉዞው ከሚፈጥራቸው ፈተናዎች በመማርም ራሱን እያበቃ ዛሬ ላይ ደርሷል ።

ለዚህም የለውጡ አርክቴክት የሆኑት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) የአመራር ብቃት መተኪያ የሌለው እንደሆነ፤ የለውጥ ኃይሉ ከቃል ባለፈ በየወቅቱ እያስመዘገበ ካለው ሀገራዊ ስኬትና ስኬቱ እንደ ሀገር እየፈጠረ ካለው ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ብዙ የሚከብድ አይደለም። አብዛኛው ዜጋ የሚስማማበት ከዚያም ባለፈ ዓለም አቀፍ እውቅና እየተቸረው ያለ ነው ።

ለዚህ ከሁሉም በላይ ሀገርን ከሕልውና ስጋት መታደግ፣ ጠንካራ የመከላከያና የፀጥታ ተቋማትን የመገንባት ተስፋ ሰጭ ጅማሬ፤ የዓባይ ግድብን ከነበረበት ተስፋ አስቆራጭ ምዕራፍ አውጥቶ ዛሬ የደረሰበት ከፍያለ የተስፋ ምዕራፍ ላይ ማድረስ ፣ የገበታ ፕሮጀክቶች፤ አማራጭ አስተማማኝና ቀልጣፋ የወደብ አገልግሎት ለማግኘት እየተሄደበት ያለው መንገድ፤ በምግብ እህል ራስን ለመቻል እየተደረጉ ያሉ ጥረቶች እና አሁናዊ ስኬቶቻችውን ወዘተ ማንሳት ይቻላል።

እነዚህ ስኬቶች ሀገር እንደሀገር በብዙ ፈተናዎች ውስጥ ሆና የተገኙ ብቻ ሳይሆኑ፤ ፋታ እና ዕረፍት በሌለው የአመራር ቁርጠኝነት የተገኙ ናቸው። ስኬታማነታቸውን ስናስብም ብዙ ተደክሞባቸው፤ ተለፍቶባቸው፤ ዋጋ ተከፍሎባቸው መሆንን በአግባቡ በመገንዘብ ተገቢውን እውቅና በመስጠት ሊሆን ይገባል ።

ከዚህ አንጻር ጠቅላይ ሚኒስትሩ በምግብ ዋስትና እና በተመጣጠነ የምግብ አቅርቦት ላሳዩት ራዕይ፣ አመራር እና ቁርጠኝነት፣ ብሎም ፈጣን፣ ተለዋዋጭ እና ፈታኝ በሆነው ከባቢያዊ ሁኔታ በስንዴ ምርት ራስን ለመቻል በተከተሉት ፈጠራዊ መፍትሔ ዕውቅና በመስጠት የተባበሩት መንግሥታት የምግብ እና የእርሻ ድርጅት የአግሪኮላ ሜዳሊያ በመሸለማቸው እንኳን ደስ ያለዎት ለማለት እንወዳለን።

ሽልማቱ ሀገርና ሕዝብ ዳግም በዓለም አቀፍ መድረክ ደምቀው የታዩበትን ታሪካዊ አጋጣሚ የፈጠረ፤ ጠቅላይ ሚኒስትሩና በአጠቃላይ የለውጥ ኃይሉ ለሕዝባችን የገቧቸውን ቃሎች ተጨባጭ በማድረግ ለሀገርና ለሕዝብ የበለጠ የሚያገለግሉበትን አቅም የሚያሳድግ ትልቅ ዓለም አቀፍ ምስክርነት ነው!

**አዲስ ዘመን**
ኢፕድ
ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ያለ አግባብ እየባከነ ያለው ሀብታችን!

ጋሹ ይግዛው (ከወሎ ሰፈር)

ድሮ በእርሻና በጂኦግራፊ ክፍለ ጊዜ አስተማሪዎቻችን ሲያስተምሩ ኢትዮጵያ በእንስሳት ሀብቷ ከአፍሪካ አንደኛ፣ ከዓለም አሥረኛ ናት ሲባል ከአስተማሪዎቻችን የሰማሁትን አሁንም ድረስ አስታውሳለሁ፡፡ እንደዛሬው የቆዳና የሌጦ ዋጋ ባልወደቀበት ዘመን እንኳን ሀገራችን በቁጥር ብዙ እንስሳት ቢኖራትም ከእንስሳት ሀብቷ የሚገባትን ያህል ጥቅም እያገኘች አይደለም ብለው ምሑራን ይተቹ ነበር፡፡

የምሑራኑ ትችት የሚያጠነጥነው ሀገሪቱ ከእንስሳት ሀብቷ በቂ ሥጋ፣ ወተትና የወተት ተዋፅዖ አምርታ ለውጭ ገበያ ባለማቅረቧ ነበር፡፡ አሁን ግን “በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ” እንዲሉ ኢትዮጵያ የቆዳና ሌጦ ተጠቃሚነቷ አሽቆልቁሎ፤ ቆዳና ሌጦ በየቆሻሻ መጣያው ተጥሎ ውሻ ሲጎትትው ማየት የተለመደ ነው፤ ከውሻ የተረፈውም ለጤና ጠንቅ እየሆነ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ደግሞ ለአንድ ሀገሩን ለሚወድ ዜጋ ትልቅ የራስ ምታት ነው፡፡

በአለፉት ጊዜያት እንደ ሀገር ለቆዳና ሌጦ ልዩ ትኩረት ይሰጠው ስለነበር፤ ሀብቱ ከቡና ቀጥሎ የውጭ ምንዛሪ ከሚያስገኙ ሸቀጦች አንዱ ነበር። ከዚህ የተነሳም የሚያመርቱትና የሚሰበስቡት አካላት ለሀብቱ ከፍተኛ ጥንቃቄ ያደርጉ ነበር። ሀብቱን በማልማት ሆነ ወደገበያ በማቅረብ ሂደት ውስጥም የሚመለከታቸው አካላት ተናበው ይሠሩ ነበር።

ዛሬ ዛሬ ቆሻሻ በአግባቡ ተሰብስቦ ጥቅም ላይ ከዋለ የሀብት ምንጭ ነው በሚባልበት ዘመን ለውጭ ምንዛሪ መሠረት የነበረው ቆዳና ሌጦ እንዳልባሌ ዕቃ በየቆሻሻ መጣያው ተጥሎ ማየት፤ ለምን በዚህ ልክ ወደቀ የሚለውን ጥያቄ መጫሩ አይቀርም፡፡ የሚመለከታቸው አካላት በጉዳዩ ዙሪያ ዝምታን መምረጣቸውም ተመሳሳይ ጥያቄ ማስነሳቱ አይቀርም ፡፡

**አሁን ላይ እንደ ሀገር በውጪ ምንዛሪ ዙሪያ ያጋጠመንን ችግር በመፍታት ሂደት ውስጥ ለቆዳና ሌጦ ተገቢውን ጥንቃቄ በማድረግ የውጭ ምንዛሪው ገቢያችንን ማሳደግ የሚያስችል የተጠናከረ ሥራ መሥራት ያስፈልጋል**

ቢያንስ ቢያንስ የየከተሞች ማዘጋጃ ቤቶች ይህንን ትልቅ የሀገር ሀብት አግባብ ባለው መንገድ በመሰብሰብ መሰብሰብ ባይችሉ እንኳን፤ ከቆዳና ሌጦው የሚፈጠረውን የአካባቢ ብክለት ለማስወገድ ኃላፊነት ወስደው አለመንቀሳቀሳቸው ለብዙ ትዝብት የሚዳርጋቸው ነው፡፡

እዛሬ ላይ ትዝታ ሆነ እንጂ፤ ከጥቂት ዓመታት በፊት ለዓመት በዓላት የሚታረድ በሬ፣ ላም፣ በግና ፍየል ተገዝቶ በየግቢው ሲታሰር የቆዳና ሌጦ ነጋዴዎች በቂ ብር ካላቸው ሙሉውን ከፍለው፤ በቂ ብር ከሌላቸው ቀብድ ሰጥተው በዕለቱ በሚውለው ዋጋ ሊገዙ ተስማምተው ይሄዱ ነበር፡፡

ሌላው የበዓሉ ታዳሚዎች ከቤተሰቡና ከጎረቤቱ ጋር እየተጫወተና እየተዝናና ሲያከብር የቆዳና ሌጦ ነጋዴዎች ለራሳቸው ተገቢውን ትርፍ አግኝተው፤ በተዘዋዋሪም ለሀገራቸው የውጭ ምንዛሪ ምንጭ የሆነውን ቆዳና ሌጦ በመሰብሰብ ሀገራቸው የሚያበረክቱት አስተዋፅዖ ቀላል አልነበረም፡፡

ከዚህም ባለፈ ምናልባት አድራሻውን ያላገኙት የበሬ ቆዳ፣ የፍየልና የበግ ሌጦ እንዳያመልጣቸው ከላይ ታች ሲባዝኑ መዋላቸው የተለመደ ተግባራቸው ነበር፡፡ እነዚህ ነጋዴዎች ለአካባቢው ወጣቶችም ኮሚሽን በመክፈል ገንዘብ ሰጥተው ሀብቱን በመሰብሰብ ለሥራ ዕድል ፈጠራም አስተዋፅዖ ነበራቸው፡፡

ዜጎችም ከገዟቸው እንስሳት ቆዳና ሌጦ ጠቀም ያለ ዋጋ ያገኙ ስለነበር ቆዳና ሌጦ እንዳይቀደድ ጥንቃቄ ያደርጉ ነበር። ለዚህም ለአራጁ ከፍተኛ ማስጠንቀቂያ መስጠት የተለመደ ነበር፡፡ አራጁም ቆዳውን ወይም ሌጦውን ካበላሸ ሊከፈለው የነበረው ገንዘብ ስለሚቀንስበት እጅግ በጣም ጥንቃቄ ያደርግ ነበር፡፡

የሚገርመው ይህ ሁሉ ትዝታ በሆነበት ሁኔታ፤ በበዓላት ሰሞን እንስሳቱን ስታርዱ ለቆዳና ሌጦው ጥንቃቄ አድርጉ የሚለው የይስሙላ መልዕክት አለመቅረቱ ነው። ከቆዳና ሌጦ ጥቅም ካልተገኘ /ጥቅም ላይ ካልዋለ/ በምን መስፈርት እና ለምንድን ነው ጥንቃቄ የሚያደርገው ?፡፡

ቆዳና ሌጦው ጠቀም ያለ ዋጋ ሊያገኝ ቀርቶ፤ የበዓል ሰሞን ቆሻሻ እየሆነ ባለበት ሁኔታ የመልእክቱ አስፈላጊነት እስከምን ድረስ ነው። ይህ ችግር ሁላችንንም ሊያሳስበን የሚገባ ነው፡፡ እያንዳንዳችንን የመፍትሔው አካል እንድንሆን በኃላፊነት መንፈስ እንድንቀሳቀስ ሊገፋፋን የሚገባ ነው ፡፡

አሁን ላይ ሀገራችን እያስመዘገበችው ባለው የኢኮኖሚ ዕድገት ከሌላው ጊዜ በተለየ ሁኔታ ከውጭ ለምታስገባው ሸቀጦች ከፍያለ የውጭ ምንዛሪ እንደሚያስፈልጋት ግልፅ ነው፡፡ በዓለም አቀፍ ደረጃ ከተፈጠረው የኢኮኖሚ ቀውስ ጋር ተዳምሮ በሀገሪቱ የውጭ ምንዛሪ እጥረት ተፈጥሯል። በዚህም ግንባታዎች ሲጓተቱ፣ በአንዳንድ ምርቶች ላይ እጥረት ሲፈጠር ይስተዋላል፡፡

አሁን ላይ እንደ ሀገር በውጪ ምንዛሪ ዙሪያ ያጋጠመንን ችግር በመፍታት ሂደት ውስጥ ለቆዳና ሌጦ ተገቢውን ጥንቃቄ በማድረግ የውጭ ምንዛሪው ገቢያችንን ማሳደግ የሚያስችል የተጠናከረ ሥራ መሥራት ያስፈልጋል። በየሰፈሩ የሚመነጨው ቆዳና ሌጦ የውሻ መጫወቻ እንዳይሆን የሚመለከታቸው አካላት በትኩረት መሥራት ይጠበቅባቸዋል፡፡

ከተቻለም ቆዳና ሌጦን በጥሬው ከመላክ ይልቅ እሴት ጨምሮ ለውጭ ገበያ ማቅረብ ቢቻል ከዘርፉ የሚገኘውን የውጭ ምንዛሪ በአንድ ደረጃ ከፍ ማድረግ ይቻላል፡፡ ይህ እንኳን ባይቻል ለውጭ ገበያ በጥሬው የሚላከውን ቆዳና ሌጦ በአግባቡ ሰብስቦ ለገበያ ማቅረብ እንዲቻል የሚመለከታቸው አካላት ፈጥነው ሊንቀሳቀሱ ይገባል፡፡

ይህንን ያለ አግባብ እየባከነ ያለ ሀብት ከብክነት ለመታደግ፤ በዘርፉ የተሰማሩ ባለሙያዎች፣ ቆዳ ነጋዴዎች፣ ባለሀብቶችና የሚመለከታችሁ የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች ሐሳባችሁን በማዋጣት የራሳችሁን ጠጠር መጣል ይጠበቅባችኋል። “ልብ ያለው ልብ ይበል” ። አበቃሁ፤ ቸር እንሰንብት፡፡

# ተጠየቅ

## " የዩኒየኖች እና የኅብረት ሥራ ማህበራት አመራሮች በኢንስፔክሽን ግኝቱ መሠረት ቢፈተሹ አንዳቸውም ከተጠያቂነት አይተርፉም"

- ልዕልቲ ግደይ
የአዲስ አበባ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን ኮሚሽነር


ፎቶ ሐዲስ አብርሃ

**ሞገስ ተስፋና ሙሉቀን ታደገ**

በከተማ አስተዳደሩ በአዋጅ ቁጥር ተቋቁመው ለህዝብ አገልግሎት እየሰጡ ከሚገኙ ተቋማት አንዱ የአዲስ አበባ የህብረት ስራ ኮሚሽን ነው:: ዋና ዓላማውም የህብረት ስራ ማህበራትን በማደራጀት ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮችን መፍታት እንዲችሉ ሙያዊና ቴክኒካዊ ድጋፎችን ለማድረግ ነው::

ማህበራቱ ዋና አላማቸው ይህ ይሁን እንጂ በተጨባጭ ያለው እውነታ ግን ከዚህ በብዙ የተለየ እንደሆነ በስፋት ይነገራል ፤ በተለያዩ ከአሰራር መዛነፎች፤ ከሙስናና ከብልሹ አሰራሮች ጋር በተያያዘ ፤ በህብረተሰቡ ዘንድ ከፍተኛ ቅሬታ ይነሳባቸዋል:: የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርም ጸረ ሙስና ኮሚሽን ባስጠናው ጥናትም የአዲስ አበባ ህብረት ስራ ኮሚሽን ከፍተኛ የአሰራር ብልሽት እንዳለበት አመላክቷል::

የኢፕድ መልካም አስተዳደርና ስነ ምግባር ዝግጅት ክፍል የኮሚሽኑ የአሰራር ስርዓት በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ፤ማህበራት ከተቋቋሙበት አላማ አንጻር ለምን ውጤታማ እንዳልሆኑና ከጊዜ ወደ ጊዜ እየናረ የመጣውን የኑሮ ውድነት መቀነስ ለምን ተሳናቸው በሚሉትና መሰል ተያያዥ ጉዳዮች ላይ ከኮሚሽኑ ዋና ኮሚሽነር ወይዘሮ ልዕልቲ ግደይ ጋር ቆይታ አድርጓል:: መልካም ምንባብ!::

**አዲስ ዘመን፡- የአዲስ አበባ የህብረት ሥራ ኤጀንሲ ወደ ኮሚሽን የመሰወጡ ፋይዳ ምንድን ነው? ከስም ባሻገር በተግባር ምን ለመስራት ታስቧል?**

**ወይዘሮ ልዕልቲ፡-** ተቋሙ የስም ለውጥ ብቻ አይደለም ያደረገው፤ ዓላማውም የስም ለውጥ ማድረግ አይደለም:: ከዚህ በፊት ኤጀንሲ ሆኖ ሲሰራ በነበረበት ወቅት ተጠሪነቱ ለንግድ ቢሮ ነበር:: በዚህ ወቅት ተቋሙ በአዋጅ ከተሰጠው ስልጣን አንጻር በስትራቴጂ እየተመራ አልነበርም:: ማህበረሰቡ ተቋሙን የሚያውቀው በአንዷ የስራ ዘርፍ በሸማቾች ማህበራት ብቻ ነው:: ስራው ግን ከዚህ የተሻገረ ነው ። ወደ ስምንት ሺ የሚደርሱ ማህበራት በውስጡ የያዘ ነው:: ከነዚህ ውስጥ 154ቱ የሸማች ማህበራት ብቻ ንግድ ላይ ትኩረት አድርገው እየሰሩ ነው::

ማህበራት እንደየተደራጁበት ዓላማ ትኩረት ይፍልጋሉ:: ለንግድ ቢሮ ተጠሪ ሆኖ እያለ ትኩረት የሚደረግበት ግብይት የሚያከናውኑት ሸማች ማህበር ብቻ ነው:: በመሆኑም ማህበራት መለወጥ ባለባቸው ልክ እንዳይለወጡ እና እንዲዘነጉ አድርጓቸዋል::

በዚህም በርካታ ማህበራት ለሀብት ብክነትና ለብልሹ አሰራር ተዳርገዋል:: የስም ለውጡ ከስያሜ ባሻገር ከዚህ በፊት በተለያዩ አካላት የሚነሱ ቅሬታዎችን እና ጥያቄዎችን የሚመልስ ነው:: ከተጠሪነት ወጥቶ ተቋሙ በአዋጅ የተሰጠውን ተልዕኮና ስልጣን ሳይሸራረፍ ተግባራዊ ማድረግ ያስችለዋል በሚል ነው ።

ንግድ ቢሮ ትርፍን መሰረት አድርጎ የሚሰራ ነው:: ህብረት ስራ ማህበራት ደግሞ ከትርፍ ይልቅ አገልግሎትን የሚያስቅድሙ ተቋማት በመሆናቸው በንግድ ህጉ አይተዳደሩም:: በመሆኑም ንግድ ቢሮ ሸማቾችን የሚመራበት ህግና ሌሎች የንግድ ሥራዎችን የሚመራበት ህግ አንድ አይደለም::

በዚህ ሳቢያ ሸማች ማህበራት ከጊዜ ወደ ጊዜ ማህበራት ማገልገል የሚለውን ሀሳብ በመርሳት የነጋዴነት ባህሪ እየያዙ መጥተዋል:: እነዚህን እና መሰል ችግሮችን ለመፍታት በመሳብ የተቋሙን ስያሜ እና አሰራር እንዲቀየር የከተማዋ ካቢኔ ካጸደቀው በኋላ ለከተማ አስተዳደሩ ምክር ቤት ቀርቦ ተጠሪነቱ ለከንቲባ በመሆን ስያሜው ኮሚሽን እንዲሆን ተወስኗል::

**አዲስ ዘመን፡- ኮሚሽኑ ኤጀንሲ በነበረበት ወቅት ከተጠሪነቱ ባሻገር የአሰራር ክፍተቶች አልነበሩበትም?**

**ወይዘሮ ልዕልቲ፡-** ከአሰራርና ከአደረጃጀት አንጻር ክፍተት ነበር:: አሰራሮች ይጣሳሉ፤ ሸማቾችና ዩኔኖች ላይ ህገ ወጥ ግብይቶች ይከናወናሉ:: ይህም ከመመሪያ ጥሰት፤ ከሌብነትና ብልሹ አሰራር ጋር ከፍተኛ ችግር ነበር:: ለምን ተደረገ? ተብለው ሲጠየቁም "ከንግድ ቢሮ ታዘን ነው" የሚል ምላሽ የሚሰጡ አካላት ነበሩ:: አዛዦች መብዛትም ለመልካም አስተዳደርና ለብልሹ አሰራር ዳርጓቸው ቆይቷል::

ሸማቾች ነጻ ማህበሮች ናቸው:: አሰራር ከተዘረጋላቸው በኋላ ነጻ ሆነው የመሸጥ መብት አላቸው:: ክትትልና ቁጥጥሩ ህግ መጣሳቸውን አለመጣሳቸውን ማየት ነው:: ለንግድ ቢሮ ተጠሪ ሆነው በቆዩበት ጊዜ ግን ለብልሹ ለአሰራር በር ከፍቶ ነበር::

**አዲስ ዘመን፡- ኮሚሽን ከሆነ በኋላ ቀደም ሲል የነበሩ ጣልቃ ገብነቶችና ብልሹ አሰራሮች እየተቀረፉ ነው ለማለት የሚያስደፍር ነገር አለ ?**

**ወይዘሮ ልዕልቲ፡-** ኮሚሽን ከሆነ በኋላ አሰራሮች ተጠብቀው የአመራር ቅንጅቱም ወጥ ነው:: አማረም ከፋም ሰበብ የሚደረግበት ነገር አይኖርም:: የነበሩ ብልሽቶችን በተገቢው መንገድ ለመቆጣጠር የተጠያቂነት ስርዓትን ለማስፈን ሁሉንም ማህበራት በእኩል ሚዛን በመገምገም አመራር እየተሰጡ ክፍተቶችን እያረሙ ለመስራት ሰፊ እድል ፈጥሯል::

ከዚህ ቀደም ማህበራትም ከይዞታ አንጻር የመብት ጥያቄ ነበራቸው:: ነገር ግን ጥያቄአቸው በቀጥታ ለተገቢው አካል ይደረስ ስላልነበር ጥያቄዎቻቸው ምላሽ ሊያገኙ አልቻሉም ነበር ። አሁን ላይ ቀጥታ ለኮሚሽኑ ተጠየቂ በመሆናቸው ከይዞታ እና መስል ጉዳዮች ጋር የተያዙ ጥያቄዎች ለከንቲባዋ በማቅረብ ምላሽ እንዲገኝበት ተደርጓል::

ይህም ወደ ከሚሽን ማደጉ ከስም ለውጥ ባሻገር አሰራሮችን በማስጠበቅ ጥራት ያለውና ወቅቱን የጠበቀ አገልግሎት መስጠት የሚቻልበት ፤ሸማቾችም የተሻለ ግብይት እንዲፈጥሩ ዕድል ፈጥሯል:: ወደ ከንቲባዋ የምንቀርበው በሦስተኛ ወገን ሳይሆን ቀጥታ ስለሆነ ብዙ ጥያቄዎች ምላሽ እንዲያገኙ እየተደረገ ነው::

**አዲስ ዘመን፡- ሪፎርሙ በማህበራቱ ሳይ የሚነሱ የአደረጃጀትና የመዋቅር ችግሮችን መፍታት የሚያስችል ነው?**

**ወይዘሮ ልዕልቲ፡-** ኤጀንሲው ኮሚሽን ከሆነ ስድስት ወሩ ነው:: ላለፉት ስድስት ወራት በጥናት ላይ የተመሰረተ የሪፎርም ስራዎን ሲሰራ ቆይቷል:: ሪፎርሙ ከማህበራት ጀምሮ እስከ ታች ያሉትን ሸማች ማህበራት ያካተተ ነው ።

ከብልሽት የጸዳ አገልግሎት ከመስጠት አንጻር ማህበረሰቡ ከፍተኛ ቅሬታ በሚያነሳባቸው ጉዳዮች ላይ መልስ መስጠት አስፈላጊ ነው:: ጥናቱ ከላይ እስከ ታች ድረስ በሰው ኃይልና በአደረጃጀት መልስ ሊሰጥ በሚችል ሁኔታ ሪፎርም እየተደረገ ነው:: በዚህም ተገቢውን ግብዓት በማሟላት እስከ ወረዳ ድረስ ያሉ አንድ ሺ 437 የሚሆኑ የኮሚሽኑ ሰራተኞች ፈተና እንዲወስዱ ተደርጓል::

ሪፎርሙ ማዕከል የሚያደርገው ይህን ብቻ አይደለም:: ዘጠኝ የሚደርሱ አገልግሎቶች እንዲዘምኑ ለማድረግ በጥናቱ ተለይተው እየተሰራባቸው ነው:: የግብይት ስርዓት፤ የማህበር ቤት አደረጃጀትና አያያዝ፤ የመዝናኛ ማዕከላት አያያዝ በህግና በአሰራር ማድረግ ይገኝበታል::

የመዝናኛ ማዕከላት በህግና በአሰራር የተደገፉ አልነበሩም:: ገቢ የሚደረጉ ሂሳባቸው በተቀናጀ መንገድ እየተያዘ አይደለም:: የተቋሙን የሰው ኃይል መልሶ ከተደራጀ ፤ 154ቱ ሸማች ማኅበራት የሰው ኃይላቸውን እንዲያደራጁ ከተደረገ በኋላ መዝናኛ ማዕከላት በአንድ የአመራርና የአሰራር ስርዓት ውስጥ እንዲገቡ ይደረጋል:: የቤት ማህበራት አደረጃጀት ሲታይም ከተደራጁ በኋላ እንዴት እንደሚመሩ መመሪያ የለውም:: በዚህ ሳቢያ በየቦታው ከፍተኛ ቅሬታ አለ:: ይህን መመለስ የሚያስችል መመሪያና ተግባራዊ ይደረጋል::

**አዲስ ዘመን፡- ከጊዜ ወደ ጊዜ የኑሮ ውድነቱ የከተማዋን ነዋሪ እየተፈታተነ ነው:: ይሁን እንጂ ማህበራትም ገበያውን በማረጋጋት በኩል ሚናቸው ዝቅተኛ ነው የሚል ቅሬታ ይነሳል:: ይህን እንዴት ይገመግሙታል?**

**ወይዘሮ ልዕልቲ፡-** የሸማች ማህበራት በመደበኛው ስራቸው ለማህበረሰቡ ተመጣጣኝ በሆነ ዋጋ አስፈላጊውን ምርት ማቅረብ ነው:: ከዚህ አኳያ ከአዲስ ዓመት ጀምሮ በሸማች የህብረት ስራ ማህበራት በቂ ምርት አቅርቦት እንዲቀርቡ ተደርጓል:: ከሁሉም ክልሎች ጋር በተለይ ከኦሮሚያ፤ አማራና ደቡብ ክልል ከሚገኙ ዩኒየኖች ጋር ምን አይነት ምርት እንደሚያቀርቡና ውጤታማ የምርት አቅርቦት ትስስር እንዲኖር ተደርጓል::

አቅርቦቱ በዓልን መሰረት ያደረገ ሳይሆን በየጊዜው ሸማች አለ፤ በየሳምንቱ የእሁድ ገበያ ስላለ ምርት ያለምንም እጥረት ይዘው እንዲቀርቡ የማድረጉ ስራ ተጠናክሮ ይቀጥላል:: ስጋ ቤቶች ከዚህ በፊት የነበራቸው የዋጋ ተመን ወጥ ስላልነበር ከስድስት መቶ እስከ አንድ ሺ ብር ድረስ የሚሸጡበት ሁኔታ ነበር:: ዝቅተኛ ገቢን ማዕከል አድርጎ ለመስራት አዲስ ዓመት ሳይገባ ጥናት በማካሄድ አንድ ኪሎ ስጋ ከ400 እስከ 460 ብር ድረስ እንዲሸጡ ተድርጓል:: ከዚህ በላይ መሸጥ አይችሉም::

**አዲስ ዘመን፡- በኮሚሽኑ ከተቀመጠው ዋጋ በላይ ሲሸጡ በተገኙ ስጋ አቅራቢዎች ላይ የተወሰደ እርምጃ አለ ?**

**ወይዘሮ ልዕልቲ፡-** ከተቀመጠው ዋጋ በላይ የሚሸጥ የሸማች ስጋ ቤት እርምጃ ይወሰድበታል:: በአዲስ ዓመት በጉለሌ ክፍለ ከተማ ከተቀመጠው ዋጋ በላይ ሲሸጥ ተገኝቶ እርምጃ ተወስዶበታል:: በሌሎች ላይም ክትትል ይደረጋል:: በገና በዓልም ከላይ የተጠቀሰውን ዋጋ እንዲያስቀጥሉ ተደርጓል::

ይህ ሲሆን ግን የእርድ ከብት ዋጋ ስለሚጨምር ይቸገራሉ:: በከፍተኛ ዋጋ በሬ ገዝተው በ400 እና በ460 ብር ኪሎ ስጋ መሸጥ አያዋጣም የሚል ቅሬታ ያቀርባሉ:: ለዚህ እንደ መፍትሔ የቀረበው የአንድ ወር የቤት ኪራ እንዳይከፍሉ ነው:: ለምሳሌ የሱቁ ኪራይ ከ10 ሺ እስከ 20 ሺ ከሆነ ሸማቾች እንዳይቀበሉ ይደረጋል::

**አዲስ ዘመን፡- በእሁድ ገበያ ሳይ ሸማቾች ተገደው በጫና ኪሰራ ውስጥ ገብተው እየሸጡ እንደሆነ ቅሬታ ይነሳል:: በዚህ ሳይ የእርስዎ ምላሽ ምንድን ነው?**

**ወይዘሮ ልዕልቲ፡-** ይከስራሉ የሚለውን መውሰድ አልችልም:: ትርፍን ብቻ ታሳቢ አድርገው አይሰሩም:: ትርፍን መሰረት አድርገው እንዳይሰሩ ጫና ይደረጋል:: መጫን ብቻ ሳይሆን ከተማ አስተዳደሩ አንድ ነጥብ 5 ቢሊዮን ብር ተዘዋዋሪ ፈንድ ድጎማ አድርጎላቸዋል:: ድጎማውን ወለድ አይከፍሉበትም፤ በነጻ ተጠቅመው የተሰጣቸውን ብር ብቻ ነው የሚመልሱት::

ለምሳሌ ለአንድ ዩኒየን መቶ ሚሊዮን ብር ተሰጥቶ ከሆነ መጨረሻ መመለስ የሚጠበቅበት መቶ ሚሊዮን ብሩን ብቻ ነው:: ብሩ በልዩ ሁኔታ ድጎማ የሚደረግላቸው በቀላሉ ሳይቸገሩ ምርት ገዝተው ለህብረተሰቡ እንዲያቀርቡ ነው:: ሲሸጡ ግን እንደ ማንኛውም የግል ነጋዴ ትርፍን ብቻ ታሳቢ አድርገው አይደለም::

በዓል ሲመጣ አልፎ አልፎም ትርፍን ግምት ውስጥ ሳያስገቡ እንዲሸጡ የሚደረግበት ሁኔታ አለ:: እንደ እቁላልና ዶሮ ሳያተርፉም ሳይከስሩም እንዲሸጡ ይደረጋል:: ስለዚህ የራሳቸው የአያያዝ ስርዓት ካልሆነ በስተቀር ከኮሚሽኑ የሚመነጭ ሸማቾችን እንዲከስሩ የሚያደርግ አሰራሩም አይፈቅድም፤ አይደረግም::

**አዲስ ዘመን፡- በከተማ አስተዳደሩ ለህብረት ስራ ማህበራት የተመደበውን የተዘዋዋሪ ፈንድ በአግባቡ ስታስመስት አላማ እየዋለ አይደለም ይባላል:: እርስዎ በዚህ ላይ ምን ይላሉ?**

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

# ተጠየቅ

## “ የዩኒየኖች እና የኅብረት ሥራ ማህበራት ...

ከገጽ 6 የዞረ

**ወይዘሮ ልዕልቲ፡-** በከተማ አስተዳደሩ የተዘዋዋሪ ፈንድ አንድ ነጥብ አራት ቢሊዮን ብር መድቧል። ከዚህ በፊት የተዘዋዋሪ ፈንድ ብር ለዩኒየኖች ሲሰጥ የአሰራር መመሪያ አልነበረውም። ለአንድ ዩኒየን እስከ መቶ ሚሊዮን ብር ይሰጣል። ነገር ግን አጠቃቀሙ ላይ ሰፊ ክፍተት ነበር። አንዳንድ ዩኔኖች በወለድ ጭምር ብሩን ያበድሩ ነበር። ከዓላማ ውጭ በሆነ መንገድ ህንጻ ገዝተው ይሸጡበት ነበር። ሌላ አካውንት በማስቀመጥ ወለድ ለማግኘት ተጠቅመውበታል።

የብሩ ዓላማ ዩኒየኖች ምርት እንዲገዙበትና ለመሰረታዊ የህብረት ስራ ማህበራት ማቅረበ ነው። ሪፎርሙ ካስተካከላቸው አሰራሮች የተዘዋዋሪ ብድር ብር ማን ምን ስለሰራ እንዴት ይሰጠዋል? የሚለው አንደኛው ነው ። የብር አሰጣጥና አመላለስ መመሪያ እንዲኖረው መመሪያው ለፍትህ ቢሮ ተሰትቷል።

ጸድቆ ስራ ላይ ሲውል ማን መውሰድ እንዳበትና እንዴት መመለስ እንደሚገባው ቸግር አይሆንም። መመሪያው ስራ ላይ እስከሚውል ድረስ ግን የተዘዋዋሪ ፈንዱን በተመለከተ ኦዲት ተሰርቶ ዩኔኖች የተዘዋዋሪ ብርና መደበኛ ብራቸውን የሚያስቀምጡበት አካውንት ኦዲት ተደርጓል። ተዘዋዋሪ ፈንዱ ምን ላይ እደዋለ በቦታው በመሄድ በትክክልም ለተገቢው ምርት ግዥ መዋሉን የማረጋገጥ ስራ እየተሰራ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- አሁን ላይ ተዘዋዋሪ ብድሩ በትክክል ሥራ ላይ እንዲውል ምን እየተሰራ ነው፤ በተገቢው መንገድ ሥራ ላይ ካልዋለስ ምን እርምጃ ይወሰዳል?**

**ወይዘሮ ልዕልቲ፡-** የተዘዋዋሪ ብድር ገንዘብ የሚወስዱ ዩኒየኑ እንደ ጤፍ፤ ዱቄት፤ ፓስታና መኮረኒ ምርቶ እንዲገዙበትና በተመጣጣኝ ዋጋ ለሸማች ማህበራት እንዲያሰራጩ ለማድረግ ነው። በከማው 11 ዩኒየኖችና 154 ሸማች ህብረት ስራ ማህበራት አሉ፤ ተዘዋዋሪ ፈንዱን በአግባቡ ያልተጠቀሙ ዩኔኖች በኢንስፔክሽን ከተገኙ አመራሮች ከሥራ ማገድ እስከ ህግ መጠየቅ ድረስ የሚደርስ እርምጃ ይወሰድባቸዋል። በትክክል በመጠቀም ምንም አይነት የኦዲት ችግር ያልተገኘበት ንፋስ ስልክ ላፍቶ ዩኔን ነው።

**አዲስ ዘመን፤- የከተማ አስተዳደሩ ጸረ ሙስና ኮሚሽን በኮሚሽኑ አሰራሮች ላይ ያስጠናው ጥናት በርካታ ክፍተቶችን ያመላከተ ነበር። ጥናቱን ምን ያህል ተቀበሉታላችሁ?**

**ወይዘሮ ልዕልቲ፡-** እውነት ለመናገር በኮሚሽኑ የተጠናው ጥናት የተቋሙን ችግሮች የሚገልጽ ነው። ጥናቱ ቀርቦ የጋራ ሲደረግ ግን በጥናቱ የቀረቡ ችግሮች በአጋጣሚ በሪፎርሙ ተለይተው ለማስተካከል እየተሰሩ ያሉ ናቸው።

ሌብነትና የተዘዋዋሪ ብድር ላይ ብልሽቶቾች ስለመኖራቸው ፤ በየቀበሌው የገቢ ማስገኛ የሆኑ የቀበሌ መዝናኛ፤ ሻውር ቤቶች፤ ካራንቡላ ቤቶችና መሰል የገቢ ማስገኛ ተቋማት ገቢያቸው እንዴት ይሰበሰባል? የሰው ኃይላቸው እንዴት እንደሚቀጥሩ መመሪያ ስለመኖሩ፤ በዚህ ሳቢያም የግለሰቦች መጠቀሚያ መሆናቸውን ያመላከተ ነው።

አንድ የመዝናኛ ማዕከል የሰው ኃይል ሲቀጥር በምን አግባብ እንደሚቀጥር፤ ገንዘቡ እንዴት እንደሚመራ፤ በሸማች ስር ሆነው ገንዘቡ ግን በተለየ አካውንት እንደሚገባ ኮሚሽኑ አረጋግጧል። ስለዚህ ይህን ስርዓት ለማስያዝ በመመሪያ ሊመራ እንደሚገባ ታምኖበት በርካታ ስራዎች እየተሰሩ ነው ።

**አዲስ ዘመን፡- ያለመመሪያ የባከነው የህዝብ ገንዘብ ምን ያህል እንደሆነ ኮሚሽኑ የሚያውቀው ነገር አለ?**

**ወይዘሮ ልዕልቲ፡-** በዚያ ልክ የለየነው የለም። ሸማች ማህበራት ከተቋቋሙ ብዙ አስርት ዓመታትን ያሳለፉ ናቸው። ስርዓት ሳይበጅላቸው ኪሳራ እና ምዝበራ ቢደርስባቸው አያስደንቅም። አሰራር ሳይበጅላቸው ስለኪሳራቸው ለማውራት መሰረት የለውም። አሰራር ባለመኖሩ በርካታ ሀብት እንዲባክን ሆኗል። ሲጠቀምባቸው የነበረው አባሉ ሳይሆን ግለሰቦ ናቸው።

አንድ ሸማች ማህበር በስሩ ስጋ ቤቶች፤ መዝናኛ ማዕከላት፤ ሻውር ቤት፤ ክሊኒክ፤ ትህርት ቤት ይኖሩታል። ይህ ቢኖም አባላቱ ምን የተጠቀሙት ነገር የለም ። ኪሳራ ጭምር የሚከፋፈሉ አሉ።

**አዲስ ዘመን ፡- ኮሚሽኑ ወጥ የሆነ መመሪያ በማዘጋጀት እስከመቼ ወደ ሥራ ይገባል?**

**ወይዘሮ ልዕልቲ፡-** እውነት ለመናገር ከችግሩ አሳሳቢነት አንጻር ቀጠሮ የሚሰጠቀው ጉዳይ አይደለም።



የዚህ ዓመት ስራችን ነው። ፍትህ ቢሮ መመሪያውን አጽድቆ ሲሰጠን እኛ ወደ ሥራ እንገባለን።

**አዲስ ዘመን ፡- የከተማዋ ከፍተኛው ችግር ቤት መሆኑ ይታወቃል። ከቤት ማህበር ጋር ተያይዞ የሚነሱ ችግሮችን በመፍታት የቤት ችግር ለማቃለል የሚያስችል በተጨባጭ በሪፎርሙ ምን ተሰርቷል?**

**ወይዘሮ ልዕልቲ፡-** ለማህበራት ህጋዊ ሰውነት ከመስጠት አንጻር በሪፎርማችን መመሪያ አውጥተናል። ከዚህ በፊት ግን ይህ አልነበረም። ከተማ አስተዳደሩ ሲጠቀም የነበረው የፌዴራልን መንግሥቱን ነበር። ምክንያቱም የፌዴራል መመሪያ በየትኛውም የሀገሪቱ ክፍል ስለሚሰራ።

በፌዴራል መመሪያ በቤት ማህበራት መደራጀት የሚፈልጉትን ህጋዊ ሰውነት መስጠት ይቻላል። ነገር ግን እንደከተማዋ ተጨባጭ ሁኔታ ደግሞ የራሳችንን መመሪያ አውጥተን በኮሚሽኑ መመሪያ መመራት አለብን ብለን መመሪያ አውጥተናል። በመመሪያው አንድ ሰው በቤት ማህበራት ለመደራጀት ምን ምን ማሟላት ይጠበቅበታል የሚለው ተካቷል።

**አዲስ ዘመን ፡- በሸማቾች ስር ጤና ጣቢያዎች እና ትምህርት ቤቶች ይገኛሉ። እየተመሩ ያሉት እንዴት ነው ? ትምህርት ቤቶችን በስርዓት ለመምራት ከትምህርት ቢሮ ጋር ተቀናጅቶ ከመስራት አንጻር ውስንነት የለም? ያለው ሁኔታ ምን መስላል ?**

**ወይዘሮ ልዕልቲ፡-** በእኛ ማህበራት የሚተዳደሩ 19 ትምህርት ቤቶች አሉ። እነዚህ ትምህርት ቤቶች ከ2004 ዓ.ም ጀምሮ አገልግሎት ሲሰጡ ነበር። በእነዚህ ትምህርት ቤቶች የሚማሩ ተማሪዎች ለትምህርት ክፍያ ይከፍላሉ። ነገር ግን የሚከፍሉት ክፍያ የግል ትምህርት ቤቶች ከሚከፈሉት ክፍያ በጣም ያነሰ ነው። ነገር ግን ወቅቱ ከሚጠብቀው አንጻር ትምህርት ቤቶች የሚሰጡት አገልግሎት በቂ ነው? ከተባለ መልሱ በቂ አይደለም ነው።

**አዲስ ዘመን ፡- በሸማች ስር የሚተዳደሩ ትምህርት ቤቶች ሆን ተብሎ ከደረጃ በተቻ እንዲሆኑ በማድረግ እየተዘጉ ወደ መጠጥ ቤት ሲቀየሩ ይስተዋላል። ይህን እንዴት ያዩታል?**

**ወይዘሮ ልዕልቲ፡-** ሆን ተብሎ ሲባል ማህበራት ይህ ትምህርት እንዲዘጋ እንፈልጋለን ይላሉ ማለት አይደለም። ነገር ግን አፈጻጸማቸው ይዘጋ ወደሚለው ውሳኔ የሚያመጣ ሆኖ ይገኛል። የተዘጉም ይኖራሉ። ትምህርት ቤቶች ለህብረተሰብ አገልግሎት እና ለሀገር እድገት ወሳኝ መሆናቸውን ተረድቶ እንዲሻሻሉ የሚሰሩ የትምህርት ቤት አመራሮች አሉ። በአንጻሩ ለግል ጥቅማቸው ብቻ ብለው የሚሰሩ አሉ።

በእነዚህ ማህበራት ስር ያሉ ትምህርት ቤቶች ውጤታማ ሊሆኑ አይችሉም። በዚህም ትምህርት ቤቶች እንዲዘጉ በማድረግ ትምህርት አላዋጣንም መጠጥ ቤት ይሁኑ የሚሉ ማህበራት በተጨባጭ አግኝተናል። ስለሆነም የተነሳው ቅሬታ በተግባር የሚታይ ነው። ትምህርት ቤቶች ተዘግተዋል። ከተዘጉ በኋላ ደግሞ ዘርፍ ቀይረው መጠጥ ቤት ሆነው የሚታዩ አሉ።

**አዲስ ዘመን ፡- ትምህርት ቤቶችን ሸማቾች እንዲያስተዳድሩት የሚፈቀድ መመሪያ አለ?**

**ወይዘሮ ልዕልቲ፡-** ትምህርት ቤቶች ለሸማች ማህበራት ሲሰጡ እና የሸማች ማህበራት እንዲያስተዳድሯቸው ሲደረግ በመመሪያ ሳይሆን በአደራ መልክ ተሰጥተው ነው። ትምህርት ቤት ብቻ ሳይሆን መዝናኛ ማዕከላትም በአደራ ነው የተሰጡት። ትምህርት ቤቶች በአደራ የተሰጡትም በካቢኔ ውሳኔ ነው።

በአደራ የተሰጡት ተቋማት ውጤታማ ናቸው ወይ ? ከተባለ ውጤታማ የሆኑም አሉ ፤ ውጤት ማምጣት ያልቻሉም አሉ። ውጤታማ ባልሆኑ ተቋማት ላይ ወደ ተጠያቂነት እንዳንሄድ ደግሞ ተጠያቂነት እንዲኖር የሚያስችል የአሰራር ስርዓት የለም። በሪፎርሙ ከለየው አንዱ ችግር በአደራ የተሰጠው አካል አደራውን ቢያጎድል እንዲጠየቅ የሚያደርግ ነው። በዚህም መመሪያ ተዘጋጅቶ ለፍትህ ቢሮ ተሰጥቷል።

**አዲስ ዘመን ፡- ያልተገባ አሰራር በሚሰሩ ግለሰቦች እና ቡድኖች ላይ ተጠያቂ የሚያደርግ እርምጃ ከመውሰድ አንጻር ክፍተቶች እንደነበሩበት የከተማ አስተዳደሩ ጸረ ሙስና ኮሚሽን ባጠናው ጥናት ተመላክቶ ነበር። ከሪፎርሙ በኋላ ባሉት ስድስት ወራቶች ምን አይነት ተጨባጭ እርምጃዎች ተወሰዱ?**

**ወይዘሮ ልዕልቲ፡-** ከተጠያቂነት አንጻር እንደኮሚሽን ከተሰጠን ስልጣን አንጻር እኛ ልንተገብረው የምንችለው ነገር አለ። ከኮሚሽኑ በላይ ከሆነ ደግሞ ወደ ክስ የሚሄድበት አግባብ አለ።

ሪፎርሙ ከተጀመረ ጀምሮ ባልተለመደ መልኩ በከፍተኛ ፍጥነት እና ጫና የተሰሩ ስራዎች አሉ። ከእነዚህም መካከል ሸማቾችን እና ዩኒየኖችን ኦዲት እና ኢንስፔክሽን ማድረግ ነው። ምክንያቱም ዝም ብሎ ተጠያቂ አይደረግም። ኢንስፔክሽን አድርጎ የሚገኝ ግኝት አለ። በዚህ በመነሳት በገንዘብም እና በማቴሪያል የሚታያዩ ብክነቶች እና ብልሽቶች ይኖራሉ። እሱን መነሻ በማድረግ የወሰድናቸው እርምጃዎች አሉ።

ለምሳሌ በቂርቆስ ክፍለ ከተማ የፖለቲካ አመራሮች እና የህብረት ሥራ ጽህፍት ቤት አሰራሩ ከሚፈቅደው ውጪ በመንቀሳቀስ ግብይት ፈጽመዋል። ይህም በብዙ ሚሊዮን ብር ነው። ይህንን ግብይት የሚፈጽሙት ከዩኒየን አመራር ጋር በመተባባር ነው። ይህንን በኢንስፔክሽን ካረጋገጥን በኋላ ወዲያውኑ የኢንስፔክሽን ግኝቱን የማህበሩ ጉባዔተኛ ተጠርቶ ለጉባዔው ቀርቧል።

በዚህም የቦርድ አመራሩና ዩኒየን አመራሮች ሙሉ በሙሉ እንዲታገዱ ተደርጎ ሌላ አዲስ አመራር ተተክቷል። ነገር ግን የቦርድ አመራሮች ማንሳት ብቻ ግብ አይደለም ። በገንዘብ የሚቀጣው ገንዘብ እንዲቀጣ፤ በህግ መጠየቅ ያለበትም በህግ እንዲጠየቅ የተለያዩ ተግባራት እየተከናወኑ ነው።

ሁለተኛው የኢንስፔክሽን ግኝት የተገኘበት ጉለሌ ነው። በኢንስፔክሽኑ ግኝት መሰረት ሙሉ በሙሉ አመራር ተቀይሯል። መቀየር ብቻ ሳይሆን እንደጥፋታቸው መጠን በገንዘብ እና በህግ እንዲጠየቁ አድርገናል። በጉለሌ የቦርድ አመራሩ ዩኒየኑ ከሚያተርፈው ትርፍ ሁለት በመቶ ለመውሰድ የውስጥ ደንብ አውጥተው ሲካፈሉ ነበር። በእነዚህም ላይ አስተማሪ እርምጃ እንዲወሰድ በህግ እየታየ ነው።

ሌላው የኢንስፔክሽን ግኝት የተገኘበት ደግሞ የምዕራብ ዩኒየን ኮልፌ ላይ ነው። በዚህ ዩኔን ከአባሉ በተለየ አመራሩ አምስት በመቶ ትርፍ እንዲከፋፈል የራሳቸውን የውስጥ ደንብ አውጥተው ሲካፈፈሉ ተደርሶባቸዋል። አምስት በመቶ ማለት ቀላለ ብር አይደለም። በእነዚህ አካላትም ላይ ህጋዊ አርምጃ እርምጃ ወስደናል።

ነገር ግን ዩኒየኖች እና የህብረት ስራ ማህበራት አመራሮች በኢንስፔክሽን ግኝት መሰረት ቢፈተሹ አንዳቸውም ከተጠያቂነት አይተርፉም። ቢያንስ የችግራችንን መጠን እንተው ብለን ነው ኢንስፔክሽን ሥራ ያስጀመርነው።

እውነት ለመናገር የዩኒየኖች እና ህብረት ሥራ ማህበራቱን ኢንስፔክሽን አሰርተን ስናየው ያስደነግጣል። በኢንስፔክሽኑ መሰረት ተጠያቂ እናድርግ ቢባል ከተጠያቂነት የሚተርፍ ሰው አይኖርም። ስለሆነም ይህን የኢንስፔክሽን ግኝት ቢያንስ ለሪፎርም ስራችን መጠቀም አለብን በሚል ለሪፎርም ስራችን እንደ ግብዓት እየተጠቀምን ነው።

የከፋ ችግር ባለባቸው በቀጣይ ሪፎርም ስራችን አባሉ እንዲያውቀው ተደርጎ እንዳይቀጥሉ ይደረጋል። አዲስ የሚመረጠውም አመራር መጠየቅ እንዳለ እንዲያውቅ የሚያደርግ ነው። አሁን አሁን በተለይ ግዥ ላይ ዩኒየኖች ትንሽ እጃቸውን ሰብሰብ አድርገዋል። መጠየቅን እንዳለ እየተገነዘቡ መጥተዋል። በፊት ግን ትጠየቃላችሁ የሚላቸው ሰው አልነበረም።

**አዲስ ዘመን ፡- ቴክኖሎጂዎችን ከመጠቀም አንጻር የነበራችሁ ልምድ ምን ይመስላል? ወደፊትስ የተሻሻሉ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም የማህበራቱን አሰራር ከማዘመን አንጻር ምን እየተሰራ ነው ?**

**ወይዘሮ ልዕልቲ፡-** በሪፎርማችን ከለየናቸው ወደ ዘጠኝ የሚደርሱ አገልግሎቶች መካከል ህብረት ሥራ ማህበራቱ በቴክኖሎጂ ተደግፈው መስራት እንዳለባቸው ነው ። ምክንያቱም ማህበራቱ የተበታኑ ስለሆኑ በቀላሉ መቆጣጠር አይቻልም።

በቴክኖሎጂ መደገፍ አለበት ብልን የለየነው አገልግሎት መካከል የግብይት ስርዓታችንን ነው። ዩኔኖች ምን ገዙ ፣ መጋዘናቸው ውስጥ ምን ገባ ፣ምን ሸጡ የሚለውን በሲስተም ማዕከል ላይ ሆነን እግር ለእግር ሄደን መቆጣጠር ካልቻልን ከብልሹ አሰራር መውጣት አይቻልም። ለህብረተሰቡም በተፈለገው ልክ ማገልግል አይቻልም።

የኢንስፔክሽን ስራችን በቴክኖሎጂ ቢሆን ብለን በቴክኖሎጂ የተደገፈ ኢንስፔክሽን ለማካሄድ እየሰራን ነው። ዘጠኝ ለሚደርሱ አገልግሎቶች በቴክኖሎጂ መደገፍ አለባቸው ብለን ለይተን ለሳይንስ እና ቴክኖሎጂ ቢሮ እንዲያለማ ሰጥተናል። በአዋጅ ስልጣን የተሰጠው ሳይንስ እና ቴክኖሎጂ ቢሮ ስለሆነ በጨረታ ወደ ውጪ ለማውጣት አልፈልግንም።

ከዘጠኝ ዓመት በፊት ተቋሙን በቴክኖሎጂ የማስተሳሰር ስራ በ15 ሚሊዮን ብር ወጪ ተጀምሮ ነበር። ነገር ግን ስራው በተግባር ሳይታይ የወጣው ገንዘብ ለብልሽት ተዳርጓል።

አሁን ለተጀመረው የቴክኖሎጂ ማስጀመሪያ 40 ሚሊዮን ብር ገደማ በጀት ተመድቧል። በዚህ ዓመት በቴክኖሎጂ የማስተሳሰር ሥራ አልቆ ሥራ እንጀምራለን።

**አዲስ ዘመን፡- ስነበርን ቆይታ እናመሰግናለን።**

**ወይዘሮ ልዕልቲ፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

ዜና

# የአማራ ክልል ሠላም ወደ ተሻለ ደረጃ መሸጋገሩን አስታወቀ

**ፋንታነሽ ክንዴ**

አዲስ አበባ፡- በአማራ ክልል በተሠራው የሕግ ማስከበር ሥራ የሠላም ሁኔታው ወደ ተሻለ ደረጃ መሸጋገሩን የክልሉ ኮሙኒኬሽን ቢሮ አስታወቀ።

የአማራ ክልል ኮሙኒኬሽን ቢሮ ኃላፊ መንገሻ ፈንታው (ዶ/ር) ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በክልሉ ተከስቶ ነበረውን የሠላም መደፍረስ ወደነበረበት ለመመለስ ሰፊ የሕግ ማስከበር ሥራ ሲሠራ ቆይቷል።

በሂደቱም በየደረጃው ያለው የፀጥታ ኃይልና ሕዝቡ በንቃት ተሳትፏል፤ በዚህም ክልሉ ላይ ያለው ሠላም ወደ ተሻለ ደረጃ ተሸጋግሯል ብለዋል።

በተከናወነው የሕግ ማስከበር ሥራ አሁን ላይ በሁሉም አካባቢዎች በሚባል ደረጃ አንጻራዊ ሠላም ሰፍኗል ያሉት የቢሮ ኃላፊው፤ የገና፣ የከተራና የጥምቀት በዓላት የሀገር ውስጥና የውጪ ጎብኝዎች በተገኙበት በድምቀት ማክበር መቻሉን አስታውሰዋል።

ይህም የሠላሙ ሁኔታ በከፍተኛ ደረጃ እየተሻሻለ መምጣቱንና ፀረ-ሠላም ኃይሉ እዚህ ግባ የሚባል ተፅዕኖ እየፈጠረ እንዳልሆነ የሚያሳይ ነው ሲሉ ተናግረዋል።

በዓላት እንዳይከበሩ ሕዝቡን የማስፈራራት ሥራ ሲከናወን እንደነበር አስታውሰው፤ ሕዝቡ ከፀጥታ አካላት ጋር ተባብሮ በመሥራት በዓላት ያለምንም የፀጥታ ችግር እንዲከበሩ አድርጓል፤ ለዚህም የክልሉ መንግሥት ምስጋናውን ያቀርባል ብለዋል።

የፀጥታ ሥራውን ከማስከበር ጎን ለጎን የልማት ሥራዎች በአግባቡ እየተከናወኑ መሆኑን የጠቀሱት ዶክተር መንገሻ፤ በዚህም የትምህርት፣ በጤና፣ በኢንቨስትመንትና በመሠረተ ልማት ግንባታ ሥራዎች በጥሩ ሁኔታ እየተሠሩ ነው ሲሉ ተናግረዋል።

ኃላፊው እንደገለጹት፤ በአሁኑ ወቅት የተፋሰስ ልማትና የበጋ መስኖ ስንዴ ልማቶች በጥሩ ሁኔታ እየተከናወኑ መሆኑን ጠቅሰው፤ ሕዝቡም በከፍተኛ መነሳሳት እየተሳተፈ ነው።

መከላከያ ሠራዊትና የክልሉ የፀጥታ ኃይልም በየቦታው ያለውን የሠላም ሁኔታ የማጥራትና ሕግ የማስከበር ሥራቸውን እያከናወኑ መሆኑን አመላክተዋል።

ዶክተር መንገሻ እንደተናገሩት፤ የሠላም ሁኔታው መስተካከሉን ተከትሎ በክልሉ ሁሉም ዩኒቨርሲቲዎች ለተማሪዎች ጥሪ አስተላልፈዋል፤ የተወሰኑትም ተማሪዎቻቸውን ተቀብለዋል።

የአካባቢው ማኅበረሰብም ተማሪዎችን ተቀብሎ ወደ ዩኒቨርሲቲው እንዲገቡ እያደረገ ሲሆን፤ ሌሎቹም በተቀመጠው ጊዜ ሰሌዳ መሠረት ተማሪዎችን ይቀበላሉ ብለዋል።

በፀረ-ሠላም ኃይሎች ሲደረጉ የነበሩ ማስፈራሪያዎችን ባለመቀበል መንግሥትን አምነው ተማሪዎችን ወደ ትምህርት ገበታቸው በመመለስ ጉልህ ሚና የነበራቸውን ዩኒቨርሲቲዎች፣ የተማሪ ወላጆችና የየአካባቢውን ማኅበረሰብ አመስግነዋል።

# ስደተኞች የዲጂታል ቴክኖሎጂ ተጠቃሚ የሚሆኑበት ሥርዓት ለመፍጠር እየተሠራ ነው

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡-ስደተኞች የዲጂታል ቴክኖሎጂና የሥራ ዕድል ተጠቃሚ የሚሆኑበት ሥርዓት ለመፍጠር እየተሠራ መሆኑን የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር አስታወቀ።

የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር፣ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ፓርክ ኮርፖሬሽንና የሶማሌ ክልል ኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ቢሮ ከዓለም አቀፍ የሠራተኞች ድርጅት (ILO)ጋር በጋራ መሥራት የሚያስችላቸውን ስምምነት አድርገዋል።

በወቅቱ የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስትር በለጠ ሞላ (ዶ/ር) እንደገለጹት፤ ስደተኞች የዲጂታል ቴክኖሎጂና የሥራ ዕድል ተጠቃሚ የሚሆኑበት ሥርዓት ለመፍጠር እየተሠራ ነው።

ኢትዮጵያ በ2025 ስትራቴጂ የተቀመጠውን የቴክኖሎጂ የለውጥ ኃይል ለመገንባት እየሠራች ይገኛል



ያሉት ሚኒስትሩ፤ ስደተኞችና ተጋላጭ ወጣቶችን የዲጂታል ቴክኖሎጂ ተጠቃሚ የሚሆኑበት ሥርዓት ለመፍጠር ጥረት እየተደረገ ነው ብለዋል።

ኢትዮጵያ ስደተኞችን በመቀበል በዓለም አቀፍ መድረክ ልዩ ቦታ እንዳላት ጠቅሰው፤ በግጭትና ችግር ምክንያት ለሚሰደዱ ሰዎች መጠጊያ በመሆን ስደተኞችን ከሚያስተናግዱ የዓለም ሀገራት መካከል ዋነኛዋ መሆኗን ገልጸዋል።

ዲጂታል ኢትዮጵያ 2025 ስትራቴጂ የቴክኖሎጂ ዕድገት ፍኖተ ካርታ ብቻ ሳይሆን የዲጂታል አብዮቱ ዕውነተኛ አቅም የሚታይበት በመሆኑ ሁሉንም ሰው የሚያሳትፍ ዕድል እንዳለው አስገንዝበዋል።

የዲጂታል ኢትዮጵያን ዕውን ለማድረግ የሚቻለው ስደተኞችን፣ ተጋላጭ ማኅበረሰቦችንና ሁሉንም የማኅበረሰብ አካላት በማሳተፍ መሆኑን አመላክተው፤ ስደተኞች የዲጂታል ቴክኖሎጂ ተጠቃሚ የሚሆኑበት ምቹ ምሕዳር መመቻቸቱን ተናግረዋል።

የዓለም አቀፍ የሠራተኞች ድርጅት(ILO) በኢትዮጵያ፣ ጅቡቲ፣ ሶማሊያ፣ ሱዳንና ደቡብ ሱዳን

ስደተኞች የዲጂታል... ወደ ገጽ 2 ዞሯል

# መገናኛ ብዙኃን...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

እንዳለባቸው ጠቁመው፤ በተለይም አንድነትንና መተባበርን በሚያጠናክሩ ጉዳዮች ላይ ማተኮር ይገባቸዋል። መገናኛ ብዙኃን የኢትዮጵያ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች አንድነት የሚያጠናክሩ ዘገባዎችን በከፍተኛ ኃላፊነት መሥራት ይጠበቅባቸዋል ነው ያሉት።

እንደ አፈጉባኤው ገለጻ፤ ኢዜአ የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ባሉባቸው አካባቢዎች ሁሉ መዋቅሩን በመዘርጋት ኅብረተሰቡንና መረጃን በማገናኘት አሻራውን ያኖረ አንጋፋ ተቋም ነው። ተቋሙ ባለው ተደራሽነት የሕዝቦች ድምፅ እንዲሰማ በማድረግ በሀገሪቱ የመገናኛ ብዙኃን ታሪክ ውስጥ ጉልህ ሚና ተጫውቷል።

እስካሁን በመጣበት ረጅም የአገልግሎት ዘመን ውስጥ በሀገሪቱ ውስጥ ለተመዘገቡ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ስኬቶች የራሱን አሻራ አሳርፏል ብለዋል።

የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎትም በሕዝቦች መካከል መቀራረብ እንዲኖር ብሔራዊ መግባባት እንዲፈጠርና የሀገራችን ገጽታ እንዲገነባ የተጣለበትን ሀገራዊ ተልዕኮ እየተወጣ መሆኑን አስታውሰው፤ ከኢትዮጵያ አልፎ አፍሪካውያን በቅኝ ግዛት ውስጥ በነበሩበት ጊዜ ድምፅ ሆኖ አገልግሏል። አሁን የፈጠረውን አቅም በመጠቀም ብሔራዊ መግባባትና ገጽታ ግንባታ ላይ ትኩረት አድርጎ እንዲሠራ አሳስበዋል።

የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ሚኒስትር ለገሰ ቱሉ(ዶ/ር) በበኩላቸው፤ ኢዜአ በኢትዮጵያ በኅብረ-ብሔራዊ አንድነትና የጋራ ትርክትን በመገንባት ሂደት የራሱን ሚና መጫወቱን ገልጸዋል።

ኢትዮጵያ ቀደምት ናት ስንል ቀደምት ተቋማትን በመገንባትም ነው ያሉት ሚኒስትሩ፤ ኢዜአ ከሀገሪቷ ሁሉም አካባቢዎችና ዓለም አቀፍ መረጃዎችን ለመገናኛ ብዙኃን በማድረስ ትልቅ ሥራ የሠራ አንጋፋ ተቋም መሆኑን አስገንዝበዋል።

አዲስ ያስገነባው የሚዲያ ኮምፕሌክስም ዘመናዊ ቴክኖሎጂና መሠረተ-ልማቶችን ያሟላ፣ የኢትዮጵያን የሚዲያ አቅምና የመረጃ ተደራሽነት ከፍ የሚያደርግ መሆኑን ገልጸው፤ ሥራውም እንደ ሀገር እየተከናወነ የሚገኘው ተቋማትንና መገናኛ ብዙኃንን ሪፎርም የማድረግ ሥራዎች አካል መሆኑንም ጠቁመዋል።

የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ ሰይፈ ደርቤ፤ የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት በአዲስ ምዕራፍ የኢትዮጵያን ገጽታ ለዓለም ለማሳወቅና ብሔራዊ መግባባትን ለመፍጠር ትኩረት ሰጥቶ እንደሚሠራ ገልጸዋል።

ኢዜአ በሀገር ውስጥ ከሚገኙ የመገናኛ ብዙኃን ባለፈ ከውጭ ሀገራት መገናኛ ብዙኃን ጋርም በቅንጅት እየሠራ መሆኑን ጠቅሰው፤ ኢዜአ ላለፉት 82 ዓመታት የሀገርን ገፅታ በመገንባትና መረጃን ለዓለም ተደራሽ በማድረግ ላይ የሚገኝ መሆኑን ጠቁመዋል።

የኢትዮጵያን እውነት፣ የለውጥ ጉዞና ስኬቶች ለዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ለማሳወቅም ሲሠራ መቆየቱን አስታውሰው፤ በአዲስ ምዕራፍ ሀገራዊና አህጉራዊ ተቋም በመሆን የኢትዮጵያን ገፅታ በላቀ ደረጃ ለመገንባት እንደሚሠራ ገልጸዋል።

ሀገራዊ ትርክትና ብሔራዊ መግባባትን ለማጠናከር የሥራ ቋንቋዎቹን ቁጥር እየጨመረ መምጣቱን አስታውቀው፤ ከኢትዮጵያ አልፎ በአህጉሪቱም አስተማማኝ የዜና ወኪል ለመሆን በኬንያና ጂቡቲ ቢሮ ለመክፈት እየሠራ ነው ብለዋል።

በትናንትናው ዕለት ለምረቃ የበቃው የኢዜአ የሚዲያ ኮምፕሌክስ ዘመኑ የደረሰበትን የሚዲያ ቴክኖሎጂ ያሟሉ ሦስት የቴሌቪዥንና አራት የሬዲዮ ስቱዲዮዎችን ያካተተ ሲሆን፣ የመዝናኛ ማዕከልና ዘመናዊ ጂምናዚየምን ያሟላ መሆኑ ተመላክቷል።

# አውቶብሶች ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የከተማ መሠረተ ልማትና የትራንስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴርን የ2016 ዓ.ም የስድስት ወራት እቅድ አፈጻጸም በገመገመበት ወቅት በአዲስ አበባ የሚስተዋለውን የትራንስፖርት እጥረትና ከዜጎች እንግልት ለመቀነስ እየተሠሩ ስለሚገኙ ክንውኖች ማብራሪያ ተሰጥቷል።

በወቅቱ የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ሚኒስትር አለሙ ስሜ (ዶ/ር) እንደገለፁት፤ በአዲስ አበባ ከተማ በተሽከርካሪ እጥረት፣ በሥራ መግቢያና መውጫ ሰዓቶች ላይ የግል ተሽከርካሪዎችን ገድቦ መንገዶች ክፍት በማድረግ የሕዝብ አገልግሎት ሰጪ አውቶብሶች በፍጥነት ተመላልሰው እንዲሠሩ የሚያስችል ጥናት ተጠናቆ በቅርቡ ወደሥራ ይገባል።

በመንገድ መዘጋጋትና በሌሎች ምክንያቶች ትራንስፖርት በማጣት በየፌርማታው ተሰልፎ የሚቆመውን ሕዝብ ባሉት ተሽከርካሪ አማካኝነት ይበልጥ አገልግሎት እንዲያገኝ አሠራሩ ያግዛል ሲሉ አስረድተዋል።

አሠራሩ ለሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪዎች የትራፊክ ፍሰቱን ቀልጣፋ በማድረግ፣ በመንገድ መዘጋት ምክንያት የሚከሰተውን የነዳጅ ፍጆታ በመቀነስና የአየር ንብረት ብክለትን በመከላከል ረገድ በጎ ሚና ይኖረዋል ብለዋል።

የተሽከርካሪ መንገዶች ማነስና ሀገሪቷ ያላት አብዛኞቹ ተሽከርካሪዎች የሚገኙት በአዲስ አበባ መሆኑን ተከትሎ የሚፈጠረውን የመንገድ መዘጋጋት ችግር ለመቅረፍ የተለያዩ የመፍትሔ ሥራዎች እየተሠሩ መሆኑን ጠቁመዋል።

ለሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪ ተሽከርካሪዎች የተለየ መንገድ ተበጅቶ እየተሠራበት ቢሆንም በቂ ባለመሆኑ የግል ተሽከርካሪዎችን ሰዓት በሥራ መግቢያ መውጪያ ላይ መገደብ አስፈላጊ መሆኑን አመላክተዋል።

የከተማው የትራንስፖርት ተጠቃሚ ሕዝብ አገልግሎቱን በአግባቡ የማያገኝበትና ባሰበበት ሰዓት ተነስቶ የፈለገበት ቦታ እንዳይደርስ የሚያደርጉ ምክንያቶችን በጋራ መቀነስ እንደሚገባ ጠቅሰው፤ የሕዝብ ትራንስፖርት ተሽከርካሪዎች እጥረት፣ የመንገድ መዘጋጋት፣ የስምሪትና የተሽከርካሪ አስተዳደር አለመዘመን ላይ በትኩረት እየተሠራ መሆኑን ሚኒስትሩ ተናግረዋል።

እንደ ሚኒስቴሩ ገለጻ፤ በአዲስ አበባ ከተማ የተሽከርካሪ ቁጥርን ለመጨመር በየዓመቱ ብዛት ያላቸውን ዜጎች መጫን የሚችሉ ዘመናዊ ተሽከርካሪዎች ተገዝተው ወደአገልግሎት እየገቡ ነው።

በዘንድሮ ዓመትም በዓለም ባንክ በኩል የሚቀርቡ የሕዝብ ትራንስፖርት ሰጪ ተሽከርካሪዎች ተገዝተው እንደሚቀርቡ ይጠበቃል ብለዋል።

በተጨማሪ ያሉትም አውቶብሶች የፌርማታ መነሻና መድረሻ ሰዓታቸውን ተገልጋዮች እንዲያውቁ የሚረዳ ቴክኖሎጂ ተግባራዊ ለማድረግ ከዓለም ባንክ ጋር እየተሰራ መሆኑን አስታውቀዋል።

አሠራሩ በአዲስ አበባ ከተማ ተሞክሮ ትልቅ ውጤት የሚያመጣ ከሆነ በሌሎች በማደግ ላይ ባሉ የክልል ከተሞች እንደሚስፋፋ ሚኒስትሩ አመላክተዋል።

# የበጋ መስኖ ስንዴ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ምርታማ ሆኖ ደረሰላቸው። ይህን ያስተዋሉት አርሶ አደሩ በሁለተኛው ዓመት ሁለት ሄክታር የበጋ መስኖ ስንዴ ዘሩ እና ጎተራቸውን ሞሉ። ምርታማ መሆኑን እማኝ ናቸው እና በዘንድሮው ዓመት አራት ሄክታር የበጋ መስኖ ስንዴ እያመረቱ ነው።

የሰሙትን በመሞከር፤ የሞከሩትን በማስፋት የሚታወቁት አርሶ አደር ወራቦ፤ ሞክረው ያገኙትን የስንዴ ምርት ለጓደኞቻቸው በመንገር ብዙዎችን አሳምነዋል። እንዴት ተደርጎ ያሉ አርሶ አደሮችን ወትውተው በማሳመን ከመንግሥት አካላትም፤ ከግብርና ባለሙያዎች እና ከሙያ አጋሮቻቸው ምሥጋና ተችሯቸዋል።

ከዚህ በፊት በበጋ ወቅት ሥራ ፈትቼ የምኖር እና በችግር የማሳልፍ ብሆንም አሁን በራሴ ጥረት እና በባለሙያዎች ድጋፍ ከችግር ለመላቀቅ እና የቤተሰቤን ፍላጎት ለማሟላት በቅቻለሁ ይላሉ እርሳቸውም።

የወረዳውና የዞን መንግሥት እርሳቸውንና ሌሎችን ለማበረታታት የበጋ መስኖ ስንዴ ዘርፍ ላይ ድጋፍ በማድረጉም ያመሰግናሉ።

የበጋ መስኖ ስንዴ አይቸው እና ሞክሬው የገባሁበት ሥራ ነው የሚሉት አርሶ አደሩ፤ ከስንዴ በተጨማሪ እንደ ቲማቲም፣ ስኳር ድንች፣ ሽንኩርት እና ሌሎች የሥራስር ተክሎችን እንደሚያለሙ ይናገራሉ።

የበጋ መስኖ ስንዴ በተለይ ለእኛ አካባቢ ምቹ ነው የሚሉት አቶ ወራቦ፤ ስንዴው የሚደርስበት ጊዜ በቆሎ ከሚዘራበት ወቅት ቀደም ብሎ መሆኑ ምቹ ሁኔታን ፈጥሯል ይላሉ። በዓመት ሦስትና አራት ጊዜ ለማምረት እንደታደሉም ነው የሚናገሩት።

ከዚህ በፊት ባለው ጊዜ በሄክታር 18 ኩንታል የሚያገኙ እንደነበር ጠቅሰው፤ ዘንድሮ ከሁሉም ጊዜ የተሻለ ምርት እንደሚያገኙ ተስፋ ማድረጋቸውን ይናገራሉ። የወቅቱ ጥሩነት፣ የውኃ እንደልብ መገኘት እና አስፈላጊ የምርት ግብዓቶች መጨመራቸውና አረም በጊዜው መከናወኑ ምርቱን ከፍ ያደርጋል ብለዋል።

በአሁኑ ወቅት ከአንድ ሄክታር ከ25 እስከ 30 እያመረቱ መሆኑን ተናግረው፤ ዘንድሮ ካመረቱት የበጋ መስኖ ስንዴ ከ100 ኩንታል በላይ ምርት እንደሚጠብቁ ነው የጠቆሙት።

በሚገኘው ምርት ልጆቼን አጥግቤ አበላለሁ፤ አስተምራለሁ፤ ለገበያም ምርቴን አቀርባለሁ ሲሉ ይናገራሉ። በተደጋጋሚ የበጋ ስንዴ እንዲያመርቱ ተነግሯቸው ፈቃደኛ ያልሆኑ አርሶደሮች እኔን ሲያዩ ይቀናሉ ይላሉ አርሶ አደር ወራቦ።

የበጋ ስንዴ በማልማቴ የመንግሥት ግብር ያለምንም ችግር እንድከፍል አስችሎኛል። ማኅበራዊ ጉዳይ ላይ ያለምንም ችግር ገንዘብ አወጣለሁ። ማልማት ያልቻሉት አርሶ አደሮች ግን ዓመቱን የሚዘልቁት በብድር ነው ሲሉ ይናገራሉ።

አሁን አሁን እኛን እያዩ የተቀየሩ አርሶ አደሮች አሉ የሚሉት አቶ ወራቦ፤ በአካባቢያቸው የሚገኙ ውኃማ አካላትን ተጠቅመው በትንሹም ቢሆን የጀመሩ አርሶ አደሮች እንዳሉ ይጠቅሳሉ። ወደዚህ ልማት ያልገቡ አርሶ አደሮችን እየመከርን ነው። ጠቃሚ መሆኑን እኔ ያረጋገጥኩ ስለሆነ ላገኘሁት ሁሉ እያስረዳሁ ነው ሲሉም ያስረዳሉ።

በደቦ፣ በዕድር እና በለቅሶ ሲገናኙ በተለይ የበጋ መስኖ ስንዴ እንዲያለሙ ሰዎችን እንደሚመክሩ ነው የሚናገሩት።

የግብርና ባለሙያዎች ድጋፍ የሚያደርጉት ለሁሉም አርሶ አደሮች ቢሆንም የበጋ መስኖ ስንዴ አምራች አርሶ አደሮች በልዩነት ድጋፍ እያገኙ ነው የሚሉት አቶ ወራቦ፤ ይህም ይበልጥ እንዲበረቱ እንዳደረጋቸው ነው የሚገልጹት።

ግብርና ባለሙያዎች ውኃ ስናጠጣ እንኳን አይለዩንም፤ የተለያዩ በሽታዎች ሲከሰቱም የኬሚካል አቅርቦት ፈጥኖ እንዲደርስ ያደርጋሉ ሲሉ ምስክርነታቸውን ይሰጣሉ።

ባጠገባቸው የምታልፈዋ ጅረት ለግድብ የማትመች በመሆኗ ለተጨማሪ ወጪ እየተዳረጉ መሆናቸውን እንደ ችግር በማንሳት፤ ሆኖም ተስፋ ባለመቁረጥ በተሰጣቸው የውኃ መሳቢያ ከወንዟ ውኃ እየሳቡ የበጋ መስኖ ምርታቸውን ማምረት እንደማያቆሙ ይናገራሉ።

የግብዓት አቅርቦት በዘንድሮ ዓመት ሥራ ምንም ችግር እንዳልገጠማቸው የሚናገሩት አርሶአደሩ፤ የውኃ መሳቢያ ጉዳይ ብቻ እንደሚያሳስባቸው ነው የሚጠቅሱት። የመስኖ ማልሚያ የውኃ መሳቢያው ከመንግሥት ያገኙት ቢሆንም የሚሠራው በነዳጅ ስለሆነ ወጪው አይቻልም ይላሉ።

አቶ ወራቦ ዲማ ከማንም ቀድመው በቀበሌያቸው የበጋ መስኖ ስንዴን ጀምረው ያስጀመሩ የበጋ መስኖ ስንዴ ፊታውራሪ መሆናቸውን የወረዳና የዞን አመራሮች እንዲሁም የግብርና ባለሙያዎች ምስክርነት ይሰጡላቸዋል።

ኢኮኖሚ

# ንግድና ግብይት





በፕሮጀክቱ የአቮካዶ፣የአኩሪ አተር እና ሽንኩርት ምርታማነትን ለማሳደግና የግብይት ሠንሰለቱንም ለማሳለጥ ይሰራል

# ምርታማነትንና የግብይት ሠንሰለትን ውጤታማ የሚያደርግ ፕሮጀክት

**በኃይሉ አበረ**

በኢትዮጵያ የግብርና ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ በተከናወኑ ተግባሮች ምርትና ምርታማነት እያደገ መጥቷል። ምርትና ምርታማነቱን ከዚህም በላይ ሊያድግ እንደሚችል ታምኖበት እየተሰራ ይገኛል።

የምርትና ምርታማነት ማደግ ብቻውን ግን አርሶ አደሩንም ሀገርንም ተጠቃሚ ሊያደርግ አይችልም። ከዚሁ ጎን ለጎን ግብይት ላይ መስራት ወሳኝ ነው። ግብይት ላይ በሚፈለገው ልክ አለመሰራቱን ተከትሎ ከምርቶቹ የበለጠ ተጠቃሚ እየሆነ ያለው አርሶ አደሩ ሳይሆን ነጋዴውና ደላላ መሆኑ ይታወቃል። ይህን ችግር ለመፍታት ምርታማነትን በማሳደግ እና ምርት ተገቢውን የገበያ እሴት ሰንሰለት ጠብቆ ለግብይት እንዲቀርብ በማድረግ የአርሶ አደሩን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ጥረቶች ሲደረጉ ይታያል።

በቅርቡም በኢትዮጵያ እና በጀርመን መካከል እንዲሁም በፈጻሚነት ደግሞ የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ከጂአይዜድ ጋር በመተባበር ምርትና ምርታማነት ማሳደግና የግብይት እሴት ሰንሰለትን በጠበቀ መልኩ ለገበያ የማቅረብ ሂደት እንዲኖር ማድረግ የሚስችል አሰራር የሚተገበርበት ፕሮጀክት በቅርቡ ይፋ ተደርጓል። ይህ በአቮካዶ፣ ሽንኩርትና አኩሪ አተር ምርቶች ላይ የሚተገበር ፕሮጀክት በሙከራ ደረጃ የሚተገበር ሲሆን፣ የእነዚህን ምርቶች የእሴት ሰንሰለት ማሳደግ ላይ ያለመ ነው፤ ለ14 ወራት የሚተገበር ፕሮጀክት ሲሆን፣ በሌሎች ምርቶች ላይም በቀጣይ እንደሚተገበር ተጠቁሟል።

የኢትዮጵያ የንግድና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ዋና ፀሐፊ አቶ ውቤ መንግስቱ በኢትዮጵያ እና በጀርመን መካከል የተደረገው የዚህ ፕሮጀክት ስምምነት በቅርቡ በተካሄደበት ወቅት እንዳስታወቁት ፤ ፕሮጀክቱ በአማራ፣ በኦሮሚያና ሲዳማ ክልሎች ላይ ያተገበራል። ክልሎቹ የተመረጡትም ምርቱን በማምረት ባላቸው አቅም መሰረት ነው።

በተወሰኑ ምርቶች፣ ለተወሰኑ ወራት እና በተወሰኑ ክልሎች የሚከናወን ሲሆን፣ እየሰፋ ሊሄድ የሚችልም ነው። ከፍተኛ መጠን ያለው የአኩሪ አተር ምርት በአማራ እና በኦሮሚያ ክልሎች ይመረታል፤ በሲዳማ ክልል ደግሞ ከፍተኛ መጠን ያለው አቮካዶ ይመረታል። አማራ ክልል እና በኦሮሚያ ክልሎች ሽንኩርት በስፋት ይመረታል። ስለሆነም ክልሎቹ ለምርቶቹ ያላቸው የማምረት አቅም ታይቶ ለፕሮጀክቱ በሙከራነት የተመረጡ መሆናቸውን ዋና ጸሐፊው ይናገራሉ።

ፕሮጀክቱ ከፕሮጀክቱ ለጋሽ ጋር በመነጋገር የሚከናወን መሆኑን አቶ ውቤ ጠቅሰው፣ የምክር ቤቱን አቅም በማሳደግ፣ በእርሻና ንግድ ስራዎች ላይ የማማከር ስራዎች እንዲሁም በፖሊሲ መፍትሄዎች ላይ በጋራ ለመስራት እንደሚያስችልም አስታውቀዋል። የሽንኩርት፣ አቮካዶ እና አኩሪ አተር ምርታማነትን ለማሳደግና የገበያ ሰንሰለትን ለመፍጠር ያለመው ይህ ፕሮጀክት በሶስቱ ክልሎች ለሚገኙ አንድ ሺህ ያህል የግል አምራቾች ዘርፈ ብዙና ተከታታይ ድጋፍ የሚደረግበት መሆኑንም አመላክተዋል።

እሳቸው እንዳሉት፤ ፕሮጀክቱ በኦሮሚያ፣ በሲዳማ እና በአማራ ክለሎች ላይ በአቮካዶ፣ አኩሪ አተር (ሶያ ቢን) እና ሽንኩርት ማምረት ስራ ላይ ከተሰማሩ አምራቾች አንስቶ ከታች ወደ ላይ ወይም ከማምረት እስከ ግብይት ድረስ ያለውን የእሴት ሰንሰለት በመደገፍ ምርታማነታቸውን ለማሻሻል ያግዛል። የማምረቻ ቴክኖሎጂ አጠቃቀማቸውን ለመሻሻል፣ የገበያ መዳረሻቸውን ለማስፋት እና ተደራሽነታቸውን ለመጨመር ታስቦ የሚከናወን ነው።

ለፕሮጀክቱ ማከናወኛ የተያዘው የገንዘብ መጠንም 553 ሺህ ዩሮ መሆኑን ዋና ጸሐፊው ተናግረዋል። ይህም በአቮካዶ፣ በአኩሪ አተር እና በሽንኩርት ንግድ ላይ የተሰማሩትን ሴቶችና ወጣቶችን ጨምሮ የተለያዩ የንግድ ማህበረሰብ አባላትን የንግድ ትርኢት ተሳትፎ በማሳደግ የገበያ ይዘትን መማር እንዲችሉ እንዲሁም ከአቻዎቻቸው ጋር በመወያየት እውቀት መለዋወጥ የሚያስችላቸውን ሥልጠና ለመስጠት የሚያስችሉ ሰፊ ስራዎች ይሰሩበታል።

በተለይም በማምረት ስራና በአመራር ላይ የሚገኙት ልምዳቸውን የሚያጋሩበትና ልምድ የሚቀስሙበት፣ ልምድ በመቀመር የተሻለ ምርታማ እንዲሆኑ የሚታገዙበት የውጭ እድል ጭምር የተካተተበት ፕሮጀክት መሆኑን ይናገራሉ። በፕሮጀክቱ ተፈጻሚነት ሂደትም በተለይ በአማራ እና በኦሮሚያ ክልል አካባቢዎች ያሉ የፀጥታ ችግሮች እየተወገዱ ሲሄዱ ፕሮጀክቱ ተግባራዊ ይደረጋል የሚል ተስፋ እንዳላቸውም አስታውቀዋል።

እንደ አቶ ውቤ ገለጻ፤ ፕሮጀክቱ ለ14 ወራት ይካሄዳል። እንደ ኢትዮጵያ ንግድና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ባሉት አስራ አንድ የስራ ዘርፎች ውስጥ ሁሉም የስራ ዘርፎች የየራሳቸው ሥራ እንዲኖራቸው በማድረግ ይደራጃል። ምርታማነትን እንዲሁም የምርት ውጤታማነትን በማሻሻል ረገድ ፕሮጀክቱ እንደ አንድ መነሻ ሥራ ሊታይ ይችላል። ከዚህ ፕሮጀክት በመቀጠልም እየሰፋ በመሄድ ወደ ሁሉም አምራች ለመድረስ የሚኬድበት አሰራር ይቀጥላል።

ፕሮጀክቱን በዘለቄታዊነት ለማስቀጠልም ይሰራል ያሉት አቶ ውቤ ፤ የኢትዮጵያ የንግድና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ፕሮጀክቱ ሲጠናቀቅ ተረክቦ እየደገፈ የሚሄድበት አሰራር ሊኖር እንደሚችልም ጠቁመዋል።

የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ፕሬዚዳንት መላኩ አዘዘው (ኢ/ር) በበኩላቸው እንደገለጹት፣ የግሉ ዘርፍ ከሌሎች ባለድርሻዎች ጋር በመቀናጀት ባለፉት ዓመታት በእርሻ ምርታማነት ዘርፈ-በዙ ስራዎችን ተግባራዊ ሲያደርግ ቆይቷል፤ የሌሎችን ተሞክሮ ከመውሰድ ጀምሮ የእርሻ ሥራዎችን ዘመናዊ ማድረግ በሚያስችሉ ጥናቶች እና ቴክኖሎጂዎች ላይ ኢንቨስት አድርጓል፤ እነዚህ ጥረቶችም በዘርፉ የተሰማሩ ተዋናዮችን አቅም ለማጠናከር፣ ምርታማነትን ለማሳደግ፣ እና የገበያ አቅርቦትን እና የዘርፉን አጠቃላይ እድገት ለማረጋገጥ አቅም የሚፈጥሩ እንቅስቃሴዎች ነበሩ።

በዚህ ፕሮጀክት በሙከራ ደረጃ ተመርጠው ተግባራዊ የሚደረጉት የአቮካዶ፣ የአኩሪ አተር እና የሽንኩርት ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ እንዲሁም በገበያ ሰንሰለት ላይ መሆኑን ጠቅሰው፣ በሌላ በኩል ደግሞ የገበያ ሰንሰለቶችን በመዘርጋት የሀገር ውስጥ ገበያው እንዲረጋጋ እገዛ እንደሚያደርግም ተናግረዋል። ምርቶቹ በዓለም ገበያ ያላቸው ተፈላጊነት እንዲጨምር ያደርጋል ሲሉም አስታውቀዋል። ፕሮጀክቱ የምክር ቤቱ ዕቅድ ውጤታማ እንዲሆን እንደሚያግዝ ጠቅሰው፤ ለተግባራዊነቱ እና ለውጤታማነቱ ምክር ቤቱ የበኩሉን እንደሚወጣ አረጋግጠዋል።

ከማህበረሰቡ እና ከግሉ ዘርፎች እንዲሁም እንደ ጂአይዜድና ከመሳሰሉት ጋር በዓለምአቀፍ ደረጃ የሚከናወኑ ስራዎች የተቋማት አደረጃጀቶችን አቅም ማሳደግ፣ የአሰራር ሂደቶችን ማሻሻል እና የገበያ ሰንሰለቱን ውጤታማ ማድረግ እንደሚያስችሉም ተናግረዋል።

የእሴት ሰንሰለት እውቀትን በማሻሻል እና የፈጠራ ስራዎችን በማስፋፋት፣ ፖሊሲዎችን በሚገባ ተገንዝቦ ተግባራዊ በማድረግ፣ ዘላቂ ስራዎችን ቅድሚያ በመስጠት በሙከራ ደረጃ ተግባራዊ ለማድረግ የተመረጡትን የአቮካዶ፣ የአኩሪ አተር እና የሽንኩርት ምርቶችን ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ማሳደግ እንደሚቻል ያመላከታሉ።

የፕሮጀክቱ ቀዳሚ ዓላማም በአቮካዶ፣ አኩሪ አተር እና ሽንኩርት ምርታማነት እና የገበያ ሰንሰለት ጋር የተያያዙ ሥልጠናዎችን ከተገቢ ክህሎት እና እውቀት ጋር መስጠት መሆኑንም አስታውቀዋል። የኢትዮጵያ የንግድና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ይህን ትልቅ ቅንጅታዊ ሥራ በኃላፊነት በመቀበል እና ተግባራዊ በማድረግ ኃላፊነቱን በቁርጠኝነት እንደሚወጣም ገልጸዋል።

ፕሬዚዳንቱ እንዳብራሩት ፤ ቀደም ሲልም ምክር ቤቱ ከልማት ባንክ ጋር በመተባበር ለ110 ሺህ ነጋዴዎች በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ስልጠናዎችን ተደራሽ ለማድረግ ችሏል። ከእነዚህም በንግዱ ዘርፍ ለመሰማራት ለሚፈልጉ አካላት ንግድ በምን መልኩ መጀመር እንደሚገባቸው፣ በገቢ ማስቀመጥ እና የንግድ ፕላን አዘገጃጀት፤ የሰው ሀብት፣ የገበያ አስተዳደር እና የፋይናንስ አስተዳደር ላይ ስልጠናዎችን ሰጥቷል፤ ይህንን ስልጠና የሰጠውም 228 አሰልጣኞችን በመላ ሀገሪቱ በማሰማራት ነው። አሁንም ከጂአይዜድ ጋር በመተባበር በሚሰራው በዚህ ፕሮጀክት ምክር ቤቱ ለወደፊቱ በጋራ የሚያከናውነውን ሥራ ለማሳካት የሚያስችል አቅም ይፈጠራል።

ጂአይዜድ ባለሙያዎች እና ግብአቶችን በማቅረብ ለምክር ቤቱ የሚያደርገው ድጋፍ ምክር ቤቱ ለኢትዮጵያ ዘላቂ ኢኮኖሚያዊ እድገት ለሚያከናውናቸው ተግባሮች ፋይዳ እንዳላቸው አመላክተዋል። ፕሮጀክቱ ለታለመለት አላማ እንዲውልና ውጤታማ እንዲሆን ለማስቻልም የክልል መንግሥታት፣ የንግድ ምክር ቤቶች፣ ማህበራት እና በተመረጡት የምርት ዘርፎች የተሰማሩ አካላት በኩል የሚኖረው ትብብር የራሱ ሚና እንደሚጫወትም ገልጸዋል።

የጂአይዜድ ተወካይ ፕሮፌሰር ፍቅሬ ለሚሳ እንደተናገሩትም፣ ፕሮጀክቱ በሽንኩርት፣ በአኩሪ አተር እና በአቮካዶ ምርታማነት እና የገበያ እሴት ሰንሰለት ላይ ማሻሻሎች እንዲታዩ ያግዛል። የእነዚህን ምርቶች ምርታማነት ለማሳደግ ፕሮጀክቱ በሙከራ ደረጃ ተግባራዊ በሚደረግባቸው የኦሮሚያ፣ አማራ እና ሲዳማ ክልሎች አቅም የሚያጎለብቱ ውጤታማ የግንዛቤ ማስጨበጥ ስራዎችን በመስራት እና ከክልሎቹ ጋር የፖሊሲ ምክክር በማድረግ አዎንታዊ ለወጦችን ለማምጣት ያስችላል።

ጂአይዜድ የግሉን ዘርፍ አቅምና ምርታማነት የሚያሳድጉ የቴክኒክ እና ሌሎች ድጋፎችን ለማድረግ የሚያስችለውን ይህን ፕሮጀክት ከኢትዮጵያ የንግድ ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ጋር በመተግበር አነስተኛ ማሳ ያላቸው አርሶ አደሮች ምርታማነታቸውን የሚያሳድጉ ስራዎችን እንዲሰሩና ኑሯቸውን እንዲያሻሽሉ እንዲሁም በኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ውስጥ የበኩሉን አስተዋጽኦ እያደረገ ያለውን የግሉ ዘርፍንም በመደገፍ ለማበረታታት እንደሚሰራ አስታውቀዋል።

የኢትዮጵያ የንግድና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት የኮሙኒኬሽን እና የህዝብ ግንኙነት ዳይሬክተር አቶ ደበበ አበበ እንደሚገልጹት፤ በዋነኛነት ፕሮጀክቱ የሚያተኩረው የግብርና የእሴት ሰንሰለትን ማጠናከር በሚለው ላይ ነው፤ ፕሮጀክቱ በአቮካዶ፣ በአኩሪ አተር እና በሽንኩርት ምርት ላይ ያሉ መሰረታዊ አቅሞችን በመለየት እና ምርቶቹን ለውጭ ገበያ ጭምር ካላቸው ተፈላጊነት አንፃር መሰራት ያለባቸው ስራዎች የሚለይበት ነው። የእሴት ሰንሰለቱም ከማምረት ጀምሮ ለገበያ ቀርቦ ለተጠቃሚው እስከሚቀርብ ድረስ ከጥራትና ከምርት ብዛት አንፃር እንዲሁም ምርቱ በአግባቡ ተመርቶ የገበያ ትስስር ተፈጥሮ ተጠቃሚው ዘንድ እስከሚደርስ ድረስ ተገቢ የአሰራር ሥርዓት የሚፈጠርበት ነው።

እነዚህ ምርቶች በሙከራ ደረጃ ለፕሮጀክቱ ሥራ የተመረጡበትም ምክንያት በሀገሪቱ በስፋት በመመረታቸው መሆኑን ጠቅሰው፣ ለውጭ ገበያ ሊቀርቡ የሚችሉ መሆናቸውም ሌላው ምክንያት መሆኑን አስታውቀዋል።

ከዚህ አንፃር በሶስቱም ምርቶች ምርታማነት ላይ የሚስተዋሉ ተግዳሮቶችን ለመፍታት የሚያስችሉ የመንግሥት የፖሊሲ ስትራቴጂ አቅጣጫዎች የሚወጡበትን ሁኔታ ሊያመቻቹ የሚችሉ ጥናቶችን ለማከናወን እንደሚያስችል አስታውቀዋል።

ከፖሊሲ ግንዛቤ ጀምሮ የሚከናወኑ ተግባሮችን የመደገፍ፣ የምርምር እና የንግድ አካባቢዎችን የማጥናት እና በመንግሥት እና በግሉ ዘርፎች ምክክር የሚካሄድባቸውን ሰነዶችና መድረኩን እንዲሁም ሥልጠናዎችንና የአቅም ግንባታ ስራዎችን ማዘጋጀት በስፋት የሚከናወኑበት መሆኑንም ገልጸዋል።

እሳቸው እንዳብራሩት፤ በፕሮጀክቱ የተመረጡት እነዚህ ምርቶች በዋነኛነት ያሉባቸው ማነቆዎች ከተፈቱ፣ ምርቶቹን በጥራት እና በብዛት ለማምረት እና በተሻለ ሁኔታ ለውጭ ገበያ ለማቅረብ በሚያስችል ደረጃ /ስታንዳርድ/ ማምረት ከተቻለ፣ ትልቁ ሥራ የሚሆነው እነዚህን ምርቶች ለዓለም ገበያ የማስተዋወቅ ሥራ ይሆናል።

ከዚህ አንፃርም በዓለም አቀፍ የንግድ ትርኢቶች ላይ በመሳተፍ ምርቶቹ እንዲታወቁ የማድረግ ስራዎችን ይሰራሉ ያሉት አቶ ደበበ ከዚህ አንጻር በሶስቱ ክልሎች 900 የምርቶቹ አምራቾች ተጠቃሚ የሚሆኑበት የፕሮጀክት እቅድ ተዘጋጅቷል ብለዋል። ከሥልጠና ጋር በተያያዘም በዋነኛነት በግዢ ዘርፉ ላይ የተሰማሩ እና ውሳኔ የሚሰጡ አካላት የስልጠና አቅማቸው እንዲጠነክር የማድረግ ሥራዎች እንደሚከናወኑም አስታውቀዋል።

መዝናኛ

# ማረፊያ/ትዝብት

## ከአፍ ከወጣ አፋፍ

**መልካምሥራ አፈወርቅ**

ሰውዬው ታክሲው ውስጥ ከገባ አንስቶ የስልክ ጨዋታው አልተቋረጠም:: አንዱን ስልክ በስንብት ዘግቶ አፍታ ሳይቆይ በሌላ ወሬ ይጠመዳል:: እሱን ጨርሶ ደቂቃዎች ሳይቆጠሩ እጆቹ ሌላውን ጥሪ ለማንሳት ይፈጥናሉ::

አጋጣሚ ሆኖ ከሰውዬው ንግግር በቀር የሚሰማ አንዳች ቃል የለም:: በታክሲው ሬዲዮም ሆነ ቴፕ አልተከፈተም :: መንገደኞቹም ቢሆን እርስበርስ እያወሩ አይደለም:: የሚሰማው የመኪናው ሞተርና የሰውዬው እረፍት አልባ ንግግር ብቻ ነው::

ይህ ሰው አሁንም ያወራል:: ተሳፋሪው እሱን ያዳምጥ ይመስል በዝምታ ተደምሟል:: እኔ ከንግግሩ እንደተረዳሁት የያዘው ጉዳይ የባልና ሚስትን እርቅ ይመለከታል:: የንግግሩ ሂደት ደግሞ ልክ እንደ ተከታታይ ፊልም ከአንዱ የስልክ መልዕክት ወደ ሌላኛው የሚያልፈው ያለ አንዳች ማቋረጥ ነው::

ነጥቦቹ ሲገጣጠሙ ሙሉ ታሪኩን ለማወቅ የሚቸግር አይደለም:: ተናጋሪው ከወዲያኛው ጫፍ የሚመጣለትን ቃል መልሶ በራሱ አንደበት እየደገመ ያወራዋል:: የያዘውን ስልክ ጨርሶ ወደሚቀጥለው ሲሻገርም የሰማውን ጉዳይ እየደገመ፣ መልሶ እየተናገረ ነው ::

አስገራሚው ጉዳይ ይህ መሆኑ ብቻ አይደለም:: እሱ ብቻ የሚያውቀውን የሰዎች ምስጢር እየዘረገፈ ሲተነትን ይሉኝታን አያውቅም:: በታሪኩ መሐል አንድ ሁለት ብሎ፣ ስሞችን ይጠቅሳል:: የአንዱን ታሪክ ለሌላው እያሳጣ ያማል። ከሚያናግረው ሰው የሚሰማውን ሌላ ሐሜት እየተነተነ ለሌሎች ያብራራል::

በአጠቃላይ ሰውዬው የት እንዳለና፣ ምን እያወራ እንደሆነ ደንታ የሰጠው አይመስልም:: እንዳሻው የሰዎችን ስም እየጠራ፣ የፈለገውን የወሬ ኮሮጆ እየፈታ ነው:: አስታራቂ መስሎ፣ ማጣላቱን፣ ደግ መስሎ መክፋቱን በንግግሩ ማወቅ ለማንም አድማጭ ግልጽ ነበር::

የመንገዱ መዘጋጋትና የመኪናው ዝግታ የሰውየውን ማንነት ለማወቅ ጊዜ ሰጥቷል:: ከአንዱ ስልክ ወደ ሌላው በሚያደርገው ንግግር ‹‹ሰው ምን ይለኛል››ን እያስበውም:: ያለገደብ የሚነዛው ወሬ የሌሎችን ጆሮ ቢያግልም ለእሱ ይህ ስሜት ምንም አልነበረም::

ሰውዬው አሁንም ያለፋታ፣ ያለአንዳች ይሉኝታ ድምፁን ከፍ አድርጎ ማውራቱን ይዟል:: ያለማቋረጥ ጭርታውን እየጣሰ የሚሰማው ወሬ በአብዛኞች ዘንድ ትዝብት ላይ እንደጣለው መገመት ችያለሁ:: አብዛኛው ተሳፋሪ ፊቱን አኮሳትሮ፣ እጁን በአፉ ጭኖ በግርምታ እያዳመጠው ነው::

የሚገርመው ሰውየው የያዘው ጉዳይ ሽምግልና ቢመስልም ውጤቱ ግን ማጣላት ማጋጨት መሆኑ ነው:: በንግግሩ መሐል የሚያነሳቸው ጉዳዮች አንድም ቁም ነገር የሌላቸው፣ ምክንያታዊ ያልሆኑና የሚያበሽቁ ጭምር ናቸው:: እሱ ግን ምንም ሳይሳቀቅ ያሻውን እያነሳ ይጥላል::

ይህ ሰው ሚስትዬው ዘንድ ደውሎ አንድ ጉዳይ ያነሳና ባልየው ስልክ ላይ ተቃራኒውን ሀሳብ ጭሮ እሳት ያቀጣጥላል:: ይህን ጉዳይ በወጉ ሳይቋጭም ወደሌሎች ስልክ እጁን ያነሳል:: በሚያስገርም ፍጥነት ነገሮችን ገጣጥሞ ድንቅ ታሪክ አድርጎ ይሰፋቸዋል::

ይህ ሁሉ ጉዳይ እየሆነ ያለው በታክሲ ውስጥ በነበረው የአፍታ ጉዞ ነበር:: እውነት ለመናገር የሰውየው የነገር ቅንብር የሚያስገርም ነው:: ለዚህ ክፉ ልምዱ ዕውቅና መስጠቱ ደግሞ በእጅጉ ያሳፍራል:: እኔና ሌሎች እንዲህ ይሰማን እንጂ በእሱ ዘንድ ያስከተለው አንዳች መሳቀቅ አልነበረም:: ይህ ግለሰብ በኖረበት ልምዱ በየአፍታው የሌሎችን ምስጢር እየዘራ፣ መሄድን ተክኖበታል::

አሁን ዕድሜ ለሰውዬው ይሁንና ሳናስበውና ውስጣችን ሳይፈቅድ የሰማነውን የሰዎች ታሪክ እንደያዝን ከታክሲው መውረድ ጀምረናል:: እሱ ግን አሁንም ወሬው የተቋጨ አይመስልም:: ከታክሲው ወርዶ አስፓልቱን ተሻግሮ እስኪሄድ ስልኩ ከጆሮው አልተነሳም:: ‹‹ወይ ጉድ !›› ብሎ ከመታዘብ በቀር ሌላ ምን ይባላል::

አንዳንዴ አንዳንዶች የት እንዳሉ የሚረሱ ይመስላል:: ስልክ አንስተው የሚያወሩትን አያውቁም:: ‹‹ወሬ›› ብለው ሲጀምሩ ንግግራቸው ሌሎች ሰዎች ዘንድ ይደርሳል ብለው አይገምቱም:: እንዳሻቸው የፈለጉትን ይናገራሉ:: ማማት ያለባቸውን ሰው ስሙን እያነሱ ይዘረጥጣሉ:: ሰዎች ሚስጥር ብለው ያወጓቸውን ሁሉ የአደባባይ ጨዋታ ያደርጉታል::

ብዙ ግዜ ይህ አይነቱ ልማድ ስልክ ንግግር ላይ ብቻ የሚከሰት አይደለም:: በሰዎች መካከል በሚኖር የግል ጨዋታም በግልጽ ይስተዋላል:: ሁለት አልያም ከዛም በላይ የሆኑ ሰዎች በትራንስፖርት ጉዞና በሌሎች መሐል ሆነው የሚያወጉት ጉዳይ ሳይታስብ የጋራ የሚሆንበት አጋጣሚ ይኖራል ::

እንዲህ አይነቶቹ ወገኞች የሚነጋገሩት በተለይ ስለመሥሪያቤታቸው ከሆነ ሥራና ሠራተኛ ይሉት፣ ጉዳይ የባቄላ ወፍጮ መሆኑ አይቀሬ ነው:: ሰዎቹ ስለ አለቆቻቸው ባሕርይ፣ ስለ ሠራተኞች ምደባ፣ ስለሥራ አፈጻጸም ውጤትና ሌላም ጉዳይ እየመዘዙ ሲተነትኑ የሌሎችን በዙሪያ መኖር ልብ አይሉትም:: አልገባቸውም እንጂ እየዘረገፉት ያለው እውነት የመሥሪያ ቤታቸውን ጥብቅ ሚስጥር ነው::

እነሱ ቦታና ግዜ አልመረጡምና የሚያወሩትን በሙሉ የስፍራው አድማጭ በእኩል ይጋራዋል:: የጉዳዩን መነሳት እንጂ ‹‹ማን ምን ይለኛል? የሚሉ ባለመሆናቸውም ትናንት ያወሩትን፣ ማግስቱን ከሌሎች አፍ ይሰሙታል:: እንዲህ መሆኑ ሌሎችን ጨምሮ ስለራሳቸው ክብር የሌላቸው መሆኑን አመላካች ነው::

አሁን ባለንበት የቴክኖሎጂ ዘመን የወሬ ቅብብሎሹን ለማስፋት ይህ አይነቱ አጋጣሚ ሰፊ ድልድይ ይሆናል:: አንዳንዶች ወሬን ፈጥረው ‹‹በሬ ወለደ›› በሚሉበት ሁኔታ እንዲህ አይነቱ ወሳኝ ምንጭ ከታማኝነት በላይ ነው:: ጥቂት ጫፍ ይዞ ሀገር ያህል አሉባልታን ለሚሰፉ ቀላጤዎች አጋጣሚው በበሶ ላይ ቅቤን እንደማፍሰስ ይሆናል::

እንዲህ አይነቶቹ ወሬ አነፍናፊዎች ‹‹አሉ፤ ተባለን›› ለማናፈስ ሩቅ መሄድ አያሻቸውም:: በተለይ የሚፈልጉት ጉዳይ የመሥሪያ ቤቶች ወሳኝ ሰነድ ከሆነ የሰሙትን፣ ካልሰሙት አቀናብረው ሰፊ የነገር ስልቻን ለመዘርገፍ ያመቻቸዋል::

ሰዎች ባለመጠንቀቅ የሚያወሩት ጉዳይ የብዙዎችን መሠረት ያናጋል:: ማንነታቸውን አቅልሎም ክብራቸውን ዝቅ ያደረጋል:: ከምንም በላይ ደግሞ በወሬው መሐል ያለ በቂ መረጃ የሚነሱ ጉዳዮች መርዛምነታቸው አይሽሬ ሊሆን ይችላል::

‹‹ከአፍ ከወጣ አፋፍ›› እንዲሉ ወሬ አንዴ ከምላስ ካመለጠ መመለሻው ከባድ ነው:: ጉዳዩ ብዙ ከተባለለት በኋላ በአንድ ጀንበር ማስተባበያ ልስጥበት ቢሉ የሚቻል አይደለም:: ምንግዜም ምላስን የሚያዝ፣ የሚገዛው ታላቁ አዕምሮ ነውና ቆም ብሎ ማሰቡ ግድ ይላል::

በሆነ አጋጣሚና ከመናገራችን በፊት አንድም ከራሳችን፣ አንድም ከአካባቢያችን በአስተውሎት ብንተዋወቅ እናተርፋለን እንጂ አንከሰርም:: ‹‹ታሞ ከመማቀቅ›› አስቀድሞ መጠንቀቅ ይሉትን ብሂል ለዚህም ልማድ ብንጠቀምበት ይበጃል:: ‹‹ዝም ባለበት አፍ ዝምብ አይገባም›› እንዲሉ ነውና::

# ዓለም አቀፍ

## ኢላን መስክ በሰው አንጎል ውስጥ የሚገጠም ‘ኒውራሊንክ ቺፕ’ ይፋ አደረገ




የቢሊየነሩ የቴክኖሎጂ ሰው ኢላን መስክ፤ ኒውራሊንክ የተባለው ኩባንያው ሰዎች አንጎል ውስጥ የሚገጠም ገመድ አልባ ቺፕ መሥራቱን ይፋ አድርጓል። መስክ እንዳለው ይህ ቺፕ ለመጀመሪያ ጊዜ ሰው ላይ ሙከራ ተደርጎበታል። የመጀመሪያ ዙር ውጤቶች እንደሚያሳዩት የኒውሮን መጠንን እና የነርቭ ‘ኢምፐልስ’ ከፍ ማለት የተስተዋለ ሲሆን ታካሚው እያገገመ ይገኛል።

የኩባንያው ዓላማ የሰው ልጅን አእምሮ ከኮምፒውተር ማስተሳሰር ነው። ይህን በማድረግ ውስብስብ የሆኑ ከነርቭ ጋር የተያያዙ (ኒውሮሎጂካል) የጤና ችግሮችን ለመፍታት ያስባል። ሌሎች ተመሳሳይ ምርት የሚያመርቱ ድርጅቶችም ይህን ቺፕ የሰው ልጆች አንጎል ውስጥ መግጠም ጀምረዋል። ከኒውራሊንክ እና ከአሜሪካው የምግብ እና መድኃኒት ተቆጣጣሪ ባለሥልጣናት ምላሽ ለማግኘት ሞክሯል።

የምግብ እና መድኃኒት ቁጥጥር ባለሥልጣን (ኤፍዲኤ) ኢላን መስክ ቴክኖሎጂውን ሰዎች ላይ እንዲሞክር ይሁንታ የሰጠው ባለፈው ግንቦት ነው። ከዚያ ቀደም ሌሎች ኩባንያዎች ይህን ፈቃድ ለማግኘት ብዙ ቢጥሩም አልተሳካላቸውም ነበር።

ኒውራሊንክ እንደሚለው ፈቃዱን ተከትሎ ስድስት ዓመታት የሚፈጅ ጥናት ጀምሯል። ለዚህ ሥራ የተመደበው ሮቦት 64 ከፀጉር ዘለላ የቀጠኑ ገመዶችን ጭንቅላት ውስጥ በመግጠም “የእንቅስቃሴ ሂደትን” መቆጣጠር ይጀምራል። ኩባንያው እንደሚለው እነዚህ ቀጫጭን ዘለላዎች ቻርጅ የሚደረጉት ገመድ አልባ በሆነ ቴክኖሎጂ ነው።

64ቱ ዘለላዎች ምንም ገመድ ሳይጠቀሙ የአእምሮ የሚገኙ መረጃዎችን (ሲግናል) ወደ አንድ መተግበሪያ ይልካሉ። መተግበሪያው ደግሞ አንድ ሰው ምን ዓይነት እንቅስቃሴ ለማድረግ እንዳሰበ መረዳት ይችላል። በቀድሞው ስሙ ትዊተር በአሁኑ ኤክስ ገፁ ላይ መልዕክት ያሰፈረው ኢላን መስክ፣ አዲሱ ቴክኖሎጂ መጠሪያው ቴሌፓቲ ነው ብሏል።

ቴሌፓቲ የተሰኘው ስም የተሰጠው ቴክኖሎጂ “ስልካችሁን አሊያም ኮምፒውተራችሁን ይቆጣጠራል፤ ከዚያ በማሰብ ብቻ የትኛውንም ነገር ማድረግ ትችላላችሁ” ይላል መስክ። “መጀመሪያ ይህን ቴክኖሎጂ መጠቀም የሚችሉት እጅግ እና እግራቸውን ያጡ ሰዎች ናቸው” ሲል አክሏል ቢሊየነሩ። በቅርቡ አሜሪካ ውስጥ የተደረጉ ምርምሮች እንደሚያሳዩት የሰዎች ጭንቅላት ውስጥ የሚገጠሙ ቴክኖሎጂዎች ሰዎች ማውራት የፈለጉትን ነገር ቀድመው ማወቅ ችለዋል ሲል ቢቢሲ ዘግቧል።

## ቶዮታ 50 ሺህ በአሜሪካ የሚገኙ ተሽከርካሪዎቹ እንዳይነዱ አስጠነቀቀ




የተሠሩ የአደጋ መከላከያ ከረጢቶች (ኤር ባግ) ፈንድተው ሊገድሏቸው ስለሚችሉ በአሜሪካ የሚገኙ 50 ሺህ የአሮጌ ተሽከርካሪ ባለቤቶች አፋጣኝ ጥገና እንዲያደርጉ ቶዮታ አሳስቧል። "እንዳይነዳ" የሚለው ማሳሰቢያ ከ2003 እስከ 2005 የተሠሩትን አንዳንድ የመኪና ሞዴሎችን ያካትታል።

እአአ ከ2009 ወዲህ በታካታ በተመረተው የአደጋ መከላከያ ከረጢት ምክንያት ከ30 በላይ ሰዎች ሕይወታቸው አልፏል። “ከረጢቱ ከተዘረጋ በውስጡ ያለው ክፍል ፈንድቶ ስለታማ የብረት ቁርጥራጮችን የመተኮስ ዕድሉ ከፍተኛ ነው” ሲል ቶዮታ ገልጿል።

ይህ ችግር የገጠማቸው ተሽከርካሪዎች የ2003-2004 ሞዴል ኮሮላ፣ 2003-2004 ኮሮላ ማትሪክስ እና 2004-2005 ራቭ4 ናቸው። በታካታ የአደጋ መከላከያ ከረጢቶች ችግር ምክንያት ከ100 ሚሊዮን በላይ መኪናዎች እና ከ20 በላይ መኪና አምራቾች ተሽከርካሪዎቻቸውን ለጥገና እንዲጠሩ አስገድዷቸዋል።

ከአስር ዓመት ተኩል በላይ በውጣ ውረድ እና አሜሪካ ውስጥ በወንጀል ምርመራ ያሳለፈው ታካታ በ2017 ኪሳራ እንደገጠመው አሳውቋል። ንብረቶቹም በቻይናዊ ባለቤትነት ለተያዘው ኪይ ሴፍቲ ሲስተምስ በ1.6 ቢሊዮን ዶላር ሸጧል። ቶዮታ ባለፉት ወራት የገጠመው ጉዳይ ይህ ብቻ አይደለም። በዚህ ሳምንት የጃፓኑ ግዙፍ መኪና አምራች ቶዮታ በናፍታ ሞተሮች ላይ በተደረገው የማረጋገጫ ሙከራ ስህተት ምክንያት የአንዳንድ ተሽከርካሪዎችን ማስረከብ አቁሟል።

በተደረገው ምርመራ የቶዮታ ኢንዱስትሪ ሠራተኞች የፈረስ ጉልበት ሙከራዎችን ውጤት አሳስተዋል። ችግር የገጠማቸው ሞተሮች ሂስ ቫን እና ላንድክሩዘር ስፖርት መኪናን ጨምሮ በዓለም አቀፍ ደረጃ በሚሸጡ 10 የመኪና ሞዴሎች ጥቅም ላይ ይውላሉ ሲል ቶዮታ ተናግሯል።

ቶዮታ ከሦስት አስርተ ዓመታት በላይ የቆዩ የደህንነት ሙከራዎችን ማጭበርበሩን ካመነ በኋላ በዳይሃትሱ ላይ የደረሰውን የሥነምግባር ጉድለት ለመፍታት ጥረት እያደረገ ነው። ባለፈው ዓመት መገባደጃ ላይ የዳይሃትሱ ዋና መሥሪያ ቤት በጃፓን የትራንስፖርት ሚኒስቴር ምርመራ የተከናወነበት ሲሆን የተሽከርካሪዎቹን ለዓለም ገበያ ማቅረብ አቋርጧል። መንግሥት የሦስት የዳይሃትሱ ሞዴሎችን የምስክር ወረቀት ሰርዟል።

በቶዮታ ቅርንጫፎች ውስጥ ስላሉት ችግሮች የተጠየቁት ፕሬዚዳንቱ ኮጂ ሳቶ ሠራተኞቹ በጣም ፉክክር ባለበት ኢንዱስትሪ ውስጥ በፍጥነት ለመሥራት ግፊት እንደነበረባቸው አምነዋል። "በጥራት ማረጋገጫ ቦታ ላይ ያሉ ሠራተኞች ብቻ ሳይሆኑ አመራሮቹም ስለጥራት ማረጋገጫ ትክክለኛ ግንዛቤ እንዳልነበራቸው እንገነዘባለን" ማለታቸው ቢቢሲ ዘግቧል።

# ነፃ ሃሳብ

# ፕሮጀክቶቹ የሰላሙ ቀጣይነት መግለጫዎች ናቸው !

ሰላም የልማት ሁሉ መሰረት ነው:: ዘላቂ ልማት ያለ ዘላቂ ሰላም እውን ሊሆን አይችልም:: በሰላም ወቅት የሚካሄድ ልማት በጽኑ መሰረት ላይ እንደ ተገነባ መሰረተ ልማት ይቆጠራል፤ ይህ መሰረተ ልማት በየትኛውም ርደትም ሆነ ርጥበት አይናድም፤አይሰነጠቅ፣ አይዘምም:: ሰላሙ የጠበቀው ልማትም የትኛውም ኃይል ከጠበቀው ልማት ይልቅ ደህንነቱ አስተማማኝ ይሆናል::

የሰላምን ዋጋ ከዚህም ሻገር ብሎ መመልከት ይቻላል:: በግጭትና ጦርነት ሳቢያ ከፈረሰ እንዲሁም ሳይገነባ ከቀረ መሰረተ ልማት የሰላምን ዋጋ መረዳት ይቻላል:: እነዚህ መሰረተ ልማቶች ባለመኖራቸው ሳቢያ የሚጎዳውን ህዝብ ማሰብ ይቻላልና:: ከጠፋው የሰው ሕይወት፣ ከሞቀ ቤቱ ተፈናቅሎ በመጠለያ ከሚገኝ ህዝብ ስቃይ፣ ለስደት ከተዳረገ ወገን ፈተና፣ ከወደመው ጥሪትና ሀብት፣ ከተንሰራፋው አለመረጋጋት ሁሉ የሰላምን ዋጋ በሚገባ መረዳት ይቻላል::

በሰላም እጦት ሳቢያ በቀረ፣ በተጓተተ እንዲሁም በወደመ ፕሮጀክት ሳቢያ ህዝብና ሀገር ያጡት ተጠቃሚነትና ምን ያህል ወደኋላ እንደተመለሱ ሲታሰብም እንዲሁ ሰላም ለልማት ያለውን ፋይዳ ለመረዳት የሚቸግር አይሆንም ::

ኢትዮጵያውያን የሰላም ዋጋ ሲገልጹ ‹‹እየዬም ሲዳላ ነው›› ይላሉ:: አዎን፣ ሰላም በታጣ ወቅት ሰው ቢሞት በስርአቱ በቆየው ልማድ፣ ወግና ስርአት መቅበር አይቻልም፤ እንደ ፊቱ ተጎጂን ማስተዛዘንም አይቻልም:: ይህም ሌላው የሰላም ዋጋ ማሳያ ነው::

ሰላም ባለመኖሩ ሳቢያ ብዙ የሚጎል ሊኖር ቢችልም፣ ከመሆን የማይቀር እንዳለም መገንዘብም ይገባል:: ሰላም የለም ተብሎ ከመብላት ከመጠጣት መታቀብ አይቻልም፤ በስሱም ቢሆን ይበላል፤ ይጠጣል፤ እንኳን ሰው ጀንያም በእህል ነው የሚቆመው ይባል አይደል::

ለእዚህ ደግሞ ለክፉ ቀን ተብሎ ከተቀመጠው በተጨማሪ መስራትም የግድ ሊሆን ይችላል:: ከዚህም በሰላም አለመኖር ሳቢያ ከመሰራት የማይቀር እንዳለም እንረዳለን:: የሆነውን ያህል ከመስራት መታቀብ አይቻልም:: በአስቸጋሪ ወቅት፣ ሰላም በሌለበትም ወቅት ቢሆን እንደልብ ተንቀሳቅሶ መስራት ባይቻልም፣ መስራት ግን የግድ ይሆናል:: ካልተሰራ መኖር አይቻልምና::

ሰፋ ወዳለው የሥራ አይነት ወደ ልማቱም ሲገባ እንደዚሁ ነው፤ የልማቱ ልክ ይለያይ ይሆናል እንጂ በሰላም ጊዜ ያለውን ያህል ባይሆንም በልማቱ መንቀሳቀሱ አይቀርም:: ጦርነት ተግ ሲል ግጭት ጋብ ሲል በሬ መጠመዱ፣ ማሳ በዘር መሸፈኑ፣ ዶማ አካፋ መነሳቱ ያለ ነው:: ለሸቀጥ ፈላጊው ለሸማቹ የኢንዱስትሪውንም የግብርናውም ምርት ማቅረቡም አለ::

ይህን ሁሉ ስል ሰላም ከሌለ የለማው ሊወድም፣ እቅዱ ሊሰረዝ አይችልም ማለቴ አይደለም፤ ይህ ብቻም አይደለም፤ ማሰብም ሊያዳግት አይችልም ማለቴም አይደለም:: ይህ ሁኔታ ጦርነትና ግጭት በነበረባቸው አካባቢዎች በሚገባ የታየ እውነታ ስለሆነ እሱን ወደማብራራት አልገባም፤ ጦርነትና ግጭት በሌለበት አካባቢ ያሉ ሰዎችም ጭምር ጦርነት እና ግጭት ሊያደርሱ የሚችሉትን ምስቅልቅል በሚገባ ያውቁታል:: ለዚያም ለእኛ ሀገር አንባቢ:: እናም የሰላም እጦት የብዙ ነገር ጸር ነው::

ሰላም ባለመኖሩ ሳቢያ የቆመ፣ ሰላም መመለስ ሲጀምር መንቀሳቀስ ይጀመራል፤ ደረጃው ሊለያይ ይችላል እንጂ ቀደም ሲል እንደጠቀስኩት ለመኖር ሲባል ወደ መስራት ይገባል:: አንድ አንድ እየተባለም ወደ ልማት ይገባል:: የሰላም እጦትና የሰላም እጦት ጠበሳዎች ከልማት ጨርሶ አያቅቡም፤ የልማቱ ልክ ላይ ልዩነት ሊኖር ይችል ይሆናል እንጂ የልማት ጠረኑ ጨርሶ አይጠፋም::

እርግጥ ነው ብዙ ሚሊዮን እና ቢሊዮን በር የወጣባቸውና በርካቶችን እንጀራ እያበሉ የነበሩ የኢንቨስትመንት ተቋማት፣ እንደ ትምህርት ቤት የጤና ተቋማት ያሉ የማህበራዊ አገልግሎት መስጫ ማእከላት በሰላም እጦት ሳቢያ ወድመው የተመለከተ፣ ስለጉዳዩ የሰማ፣ ሌላ ተመሳሳይ ተቋም በአካባቢው ለእዚያውም ሰላም በሌለበት ሁኔታ መገንባት ሊከብደው ብቻ ሳይሆን ላያስበውም ጭምር ይችላል:: እነዚህ የሰላም እጦቱ ያስከተላቸው ውድመቶች ፊት ለፊት በሚታዩበት ስፍራ አይደለም በብዙ ርቀት ላይ ሆኖም ተመሳሳይ ተቋማትን መገንባት አይደለም ማሰብ ሊከብድ ይችላል::

ይሁንና ተቋማቱን የሚፈልጋቸው ህዝብ አለና መገንባቱ የግድ ሊሆን እንደሚችል መገመት

> **መንግሥት** ይህን ውብ ስራውን በአዲስ አበባ ላይ ብቻ አካሂዶ አላበቃም፤ በገበታ ለሀገር ወደ ክልሎች ይዞ ወጥቷል

አይከብድም:: የግብርና ፣ የንግድ ፣ የህክምና ሥራ ሊያስፈልጉ ይችላሉና ተቋማቱ ፈርሰውም ከሆነ መልሰው መገንባታቸው ወይም አዳዲስ መሰረታቸው ሊያስፈልግ እንደሚችል መጠራጠር የሚያስፈልግ አይመስለኝም:: ግንባታው በልማቱ አይነትና ለልማቱ በሚያስፈልገው ፋይናንስ አቅርቦት የሚወሰን ይሆናል፤ የጦርነትና ግጭት ስጋት እያለም በእነዚህ ላይ መሰራቱ አይቀሬ ነው::

በቅርቡ ከአንድ ግጭት ላይ ከቆየ የክልል ቢሮ ኃላፊ ጋር ባደረግነው ቃለ ምልልስ ኃላፊው በክልሉ እየተካሄደ ስለነበረው የመኸር አዝመራ ስብሰባ ሲያብራሩ የመኸር አዝመራ ስብሳበውን አስፈላጊነት ከቀይ መስቀል ስራ ጋር አመሳስለውታል፤ ክልሉ በግብርናው ላይ አልሰራም ማለት በክልሉ ያለውን ችግር ይበልጥ ያወሳስበዋል ሲሉ ኃላፊው ገልጸው፣ የአዝመራ ስብሰባ ሥራ ለክልሉ የቀይ መስቀል ሥራ ያህል ተደርጎ ተወስዶ እንደተሰራበት ገልጸውልኛል:: ይህም የሰላም እጦት እያለም ልማትን ማስቀጠል ወሳኝ ለመሆኑ አንድ ማሳያ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል::

የልማቱ አስፈላጊነት ከዚህም ከፍ ያለ ሊሆን ይችላል:: ኢትዮጵያ ባለፉት ጥቂት አመታት በሰሜኑ አካባቢ ጦርነትና በተለያዩ አካባቢዎች በተፈጠሩ ግጭቶች ተወጥራ በነበረበት ወቅት ታላላቅ ፕሮጀክቶች ተገንብተውባታል፤ የተገነቡ ፕሮጀክቶች ተመርቀው ወደ ሥራ እንዲገቡም ተደርገውበታል:: ለፕሮጀክቶቹ አያሌ ሀብት ወጪ ተደርጓል::

እነዚህ ፕሮጀክቶች ከጦርነትና ግጭት ቀጣና ብዙ ርቀት ላይ ያሉ ናቸው፤ ይህን ሥራ በጦርነት ቀጣና ውስጥ የተሰራ አርጎ መቁጠር አይቻልም ብሎ የሚሞግት ሊገጥም ይችላል:: ለእዚህም በቂ መልስ መስጠት ይቻላል:: ከእነዚህ ፕሮጀክቶች አንዳንዶቹ ግጭት ይታይባቸው በነበሩ አካባቢዎች የተካሄዱ ናቸው ፤ በውጭው ዓለም ለሀገሪቱ የተሰጣት ገጽታ የጦርነትና ግጭት ሆኖ እያለም ነው እነዚህ ፕሮጀክቶች እየተገነቡ ያሉት::

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ በቅርቡ በአንድ የልማት ተቋም ምረቃ ይሁን ጉብኝት ላይ ሰላም የለም ተብሎ ልማት እንደማይቆም ያስገነዘቡበት ሁኔታም ለእዚህ አንድ ማጠናከሪያ ይሆናል:: በፌዴራል መንግሥትና በክልሎች በተለይ በጠቅላይ ሚኒስትሩ አነሳሽነት ሀገሪቱ በጦርነትና በግጭት ውስጥ በቆየችባቸው ባለፉት አመታት በተለያዩ አካባቢዎች የተገነቡት የቱሪዝምና የመሳሰሉት መሰረተ ልማቶች መረዳት የሚቻለውም ይህንኑ ነው::

ባለፉት አመታት የተገነቡት እነዚህ በርካታ ፕሮጀክቶች በሰላም እጦት ወቅትም እጅን አጣጥፎ መቀመጥ እንደማይገባ አስገንዝበዋል:: የገበታ ለሀገር ፕሮጀክት የወንጪ ደንዲ የኤኮ ቱሪዝም መሰረተ ልማት ሲገነባ ነገሮች አልጋ ባልጋ እንዳልነበሩ ይታወቃል፤ ሸኔ ጉዳት ያደረሰበት ሁኔታም ነበር፤ እንዲያም ሆኖ መንግሥት ግንባታውን ከማካሄድ አልተቆጠበም:: ፕሮጀክቱም ተገንብቶ በቅርቡ ተመርቋል:: በሌሎች በክልል መንግሥታትም ሆነ በከተማ አስተዳደሮች እና ዜጎች በርካታ ፕሮጀክቶች የተገነቡት ከኮሽታም በላይ የሆኑ የጸጥታ ችግሮችና ያንን ተከትሎ የተከሰቱ አስቸጋሪ ሁኔታዎች ባሉበት ነው::

አስቸጋሪነቱ ደግሞ የልማት ፋይናንስ ማግኘት በመቸገር የተወሳሰበ ነው፤ ሰላም በታጣበት፣ ኮሽታ በኮሽታ በተሆነበት ሁኔታ የሚያበድር የፋይናንስ ተቋም አይኖርም:: የፋይናንስ ተቋማት ማበደር አይደለም ሰዎች ካስቀመጡት ገንዘብ ለልማቱ የሚያስፈልጋቸውን ያህል ገንዘብ ለመስጠት የማይችሉበት ሁኔታም ጭምር የሚያጋጥምበት ሆኔታ ይኖራል::

ተቋራጮች ፣ ሰራተኞች በሰላም እጦቱ ሳቢያ በአካባቢው መቆየት የማይችሉበት፣ የግንባታ ግብአት አቅራቢዎችም እንዲሁ ግብአት ለማግኘት፣ ለማጓጓዝ የሚቸገሩበት ሁኔታ ሊያጋጥማቸው ይችላል::

ከዚህ ሁሉ አልፎም ሀገር በጦርነት ቀጣና ውስጥ ሆናም ልማቷን እየሰራች መሆኗ እየታወቀ ጠላቶቿ በሚያነፍሱት አፍራሽ ፕሮፓጋንዳ አልሚዎች አይደሉም እርዳታ ሰጪዎች ወደ ሀገሪቱ እንዳይመጡ እየተደረገ ባለበት ሁኔታ ልማቱ እየተካሄደ ያለው::

መንግሥትን ጨምሮ ሌሎች የልማቱ ተዋንያን የሰላም እጦት ሊያስከትል የሚችለውን ጉዳት ሳይረዱ ቀርተውም አይደለም ግንባታዎችን የሚያካሂዱት:: አሳምረው ያውቃሉ፤ ሕይወት ይቀጥላል፤ ነገም ሌላ ቀን ብለው በማሰባቸው፣ ባለራእይ በመሆናቸው ነው::

ባለፉት አመታት በክልሎች የተለያዩ አካባቢዎች በተቀሰቀሱ ግጭቶች በርካታ ዜጎች ህይወታቸውን ተነጥቀዋል፤ ሌሎች በርካታ ዜጎች አካላቸውን ተስፋቸውን ተነጥቀዋል:: ሀብትና ንብረታቸውን ያጡትንም ቤት ይቁጠራቸው::

በርካታ ሰዎች ከሞቀ ቤታቸው ከእነቤተሰባቸው ተፈናቅለው በጊዜያዊ መጠለያ ካምፕ ውስጥ ኖረዋል:: የደረሱት መፈናቀሎች በአንድ ወቅት ሀገሪቱን በተፈናቃይ ብዛት ከፊት ለፊት ከነበሩት የዓለም ሀገሮች ተርታ እንድትሰለፍ ያደረጉበት ሁኔታም ነበር::

ይህ ምስቅልቅል ደርሶባቸው አካባቢውን ለአንዴም ለመጨረሻ ጊዜም የለቀቁም ጥቂት አይደሉም፤ ይህ ብቻም አይደለም፤ ፊታቸውን ወደለቀቁት አካባቢ መመለስ የማይፈልጉ በርካታ ናቸው:: እነሱ ብቻም አይደሉም ዜናውን የሰሙትን ጨምሮ ጥቂት የማይባሉ ሰዎችም ይህ ችግር ባለባት ሀገር አልኖርም ብለው ሀገር ጥለው የወጡም አሉ::

በአንጻሩ በጦርነቱ ወይም በግጭቱ የወደመባቸውን ሀብት በፍጥነት በመተካት ወደ ስራቸው የተመለሱም ጥቂት የማይባሉ ናቸው:: በቀድሞው ደቡብ ክልል አንድ ከተማ በግጭት የተነሳ የሆቴላቸው ዋና ዋና ቁሳቁስ የወደመባቸው አንድ አባት/እሳቸው ድርጊቱ ሲፈጸም በጤና ይሁን በሌላ ምክንያት በአካባቢው አልነበሩም/ ፤ ግጭቱ ከቆመ በኋላ ወደ አካባቢው ደውለው ያሉት ቀልቤን ስለገዛው ነው እሳቸውን ማንሳቴ:: እኚህ ባለሆቴል ወደ አካባቢው ይደውሉና ምን ጠፋ፣ ወደመ ሲሉ ይጠይቃሉ:: በግጭቱ የተዘረፉት፣ የወደሙት ቁሳቁስ ዝርዝር ተነገራቸው::

እሳቸውም ሰሞኑን እልከላችኋለሁ ፤ ስራውን ለመጀመር ተዘጋጁ ሲሉ ይመልሳሉ:: ይህን የሰሙት በስፍራው ያሉ ቤተሰቦች እንዴ ጋሼ ... ሲሉ እርምጃቸው ትክክል እንዳልሆነ አርገው ሲመልሱላቸው እሳቸው የሰጡት ምላሽ የሚገርም ነበር:: ‹‹ እሱን ተውት ፤ የሆነው ነገር ጎርፍ ነው፣ አሁን ስለወደፊቱ አስቡ :: ነበር ያሉት::

አዎን የግጭትና የጦርነት ዳፋ ከበድ ነው፤ ግን ችግሩን እንደ ድንገተኛ አደጋ እንደ ጎርፍ ተመልክቶ ወደ ልማቱ መመለስ ትክክለኛ እርምጃ ነው፤ የሆነውን ክፉ ነገር እየመላለሱ ማዳመጥና መተረክ የሚፈይደው የለም:: የህይወትን፣ የሀገርን ቀጣይነት ለማረጋገጥ መስራት እንጂ ሌላ አማራጭ የለም::

በጦርነት ፣ በግጭት ውስጥ የኖሩ ሀገሮች ታሪክም የሚያስገነዝበው ይህንኑ ይመስለኛል:: ጦርነት ያኖረው ጠበሳ ከልማት የሚያቅብ ቢሆን ጦርነት ክፉኛ በልቷቸው የነበሩና ዛሬ እድገትን አሳምረው እያጣጣሙ ያሉት ሀገሮች ለእዚህ እድገት ባልበቁ ነበር:: ከዚያ ትቢያ ወጥተው ነው እዚህ የደረሱት:: ከጦርነት የተረፉቸውን ሀብትና ህዝብ ይዘው እንደ እባብ አፈር ልሰው ተነስተው ነው ለታላቅ ቁም ነገር የበቁት::

ጦርነትና ግጭት ጉዳት አደርሷል፤ ያደርሳል ተብሎ ከመልማት መታቀብ የሚባል ነገር መኖር የለበትም:: እርግጥ ነው፤ የደረሰው ጉዳት መጀመሪያ ላይ ብዙ ሊያስብል ይችላል፤ የመጨረሻው ውሳኔ ግን ፊትን ወደ ልማት መመለስ ነው፤ ህይወት ይቀጥላል፤ ሀገር ትቀጥላለች:: ስለዚህ ይህን የሚመጥን ሥራ መስራት ያስፈልጋል::

የኢትዮጵያ ጠላቶች ሀገሪቱን የጦርነት ቀጣና የግጭት ቀጣና አርገው በሳሉበት ሁኔታ፣ ሀገሪቱ ከእዚህ ማጥ መውጣት አትችልም ባለቡት ሁኔታ በሀገሪቱ በተለይ በመንግሥት እየተካሄዱ የሚገኙ የልማት ፕሮጀክቶች፣ ጦርነትና ግጭቶች ያደረሱትን ጉዳት አስመልክተው የጠቀስኳቸው አባት እንዳሉት እንደ ጎርፍ በመቁጠር እየተካሄዱ ያሉ ፕሮጀክቶች ናቸው::

የፌዴራል መንግሥት በገበታዎቹ ያከናወናቸው ፕሮጀክቶች ሀገር በጦርነትና ግጭት ቀጣና በተፈረጀችበት ወቅት የተካሄዱና እየተካሄዱ የሚገኙ ናቸው:: ፕሮጀክቶቹ ደግሞ በአዲስ አበባ ብቻ የተወሰኑ አይደሉም፤ በክልሎች ለእዚያውም የመንገድና የመሳሰሉት መሰረተ ልማቶች ፍጹም በሌሉባቸው የሀገሪቱ ገጠር አካባቢዎች ጭምር የሚከናወኑ ናቸው::

እነዚህ ፕሮጀክቶች ጦርነትና ግጭት እዚህም እዚያም አለ ተብሎ እጅ አጣጥፎ መቀመጥ እንደማያስፈልግ፣ ልማቱ መቀጠል እንዳለበት የሚያስገነዝቡ፣ የሀገርና የህይወት ቀጣይነት ማሳያዎች ናቸው::

መንግሥት ገና ብዙ ይሰራል:: በገበታ ለሸገር የአዲስ አበባ ፈርጥ መሆን የቻሉ የህዝብ መዝናኛ፣ የሀገር ገጽታ መገንቢያ ፓርኮችን ገንብቶ ወደ ሥራ አስገብቷል፤ በተደጋጋሚ እንዳስታወቀውም ፓርኮቹ የህዝብ መዝናኛ ስፍራ፣ የቱሪስቶች ቆይታ ማርዘሚያ፣ የከተማ ውበት መሆን ችለዋል:: ይህም በህዝብ ጭምር ተመስክሮለታል::

መንግሥት ይህን ውብ ስራውን በአዲስ አበባ ላይ ብቻ አካሂዶ አላበቃም፤ በገበታ ለሀገር ወደ ክልሎች ይዞ ወጥቷል:: በእዚህም የገበታ ለሀገር የኮይሻ ፕሮጀክት ሁለት አካላት ግንባታቸው ተጠናቋል፤ አንዱ ወደ ሥራ ገብቷል፤ ሌላውም ይቀጥላል:: የወንጪ ፕሮጀክት አካል የሆነው የኤኮ ቱሪዝም መንደርም በቅርቡ ተመርቋል:: የጎርጎራ ፕሮጀክትም እየተጠናቀቀ ይገኛል::

የመንግሥት የልማት ቁርጠኝነት በእነዚህ ሁለት ፕሮጀክቶች ብቻ አላበቃም:: በገበታ ለትውልድም ይቀጥላል:: ለእዚህም በተለያዩ የሀገሪቱ ክልሎች ፕሮጀክቶች እየተጀመሩ ናቸው::

መንግሥት በተደጋጋሚ እንደገለጸው በተለይ እነዚህን የቱሪዝም መሰረተ ልማት ፕሮጀክቶች እየገነባ ያለው ሁሉንም ሥራ እሰራለሁ ብሎ አይደለም፤ የግሉን ዘርፍ ወደ ልማቱ ለመሳብ ነው:: የግሉ ዘርፍ ይህን ተነሳሽነት በመመልከት ልማቱን አጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል:: ልማት ሰላም እስኪ ሰፍን ድረስ የማይጠበቅ ስለመሆኑ የልማት ፕሮጀክቶቹ አመላክተዋልና የግሉ ዘርፍም ይህን ተነሳሽነት በመጠቀም ልማቱን ማካሄድ ይኖርበታል::

እነዚህ ፕሮጀክቶች በአስቸጋሪ ወቅትም ልማትን ማካሄድ እንደሚቻል ያመላከቱ ናቸው:: መሰል ፕሮጀክቶችን ሰላም ሲሰፍን ብቻ ሳይሆን መገንባት ያለብን ሰላም ፈታኝ ሁኔታ ውስጥ እያለችም መሆን እንደሚኖርበት አስገንዝበውናል:: ባለፉት አመታት የተገነቡ ፕሮጀክቶችም በእዚህ ሁኔታ ውስጥ ነው የተካሄዱት:: እንዲህ ሲሆን ፕሮጀክቶቹ የሰላሙ ቀጣይነት መገለጫዎች መሆንም ይችላሉ::

ማህበራዊ

# ባለውለታዎቻችን

## የኢትዮጵያ ዲፕሎማሲ ቤት!

ክብረአብ በላቸው

ኢትዮጵያ ጥንታዊ የዲፕሎማሲ ታሪክ ካላቸው ሀገራት አንዷ ነች::ኢትዮጵያ ከጥንት ጀምሮ በሃይማኖት በባህልና በንግድ እንቅስቃሴ ከበርካታ ሀገራት ጋር የጠነከረ ግንኙነት መሰረት የጣለችና በዲፕሎማሲው መስክም ተጠቃሽ ተሞክሮ ማዳበር የቻለች ሀገር ነች::

ኢትዮጵያ ከዋሻ ዲፕሎማሲ ዛሬ እስከ ደረስንበት እስከ ዘመነኛው የዲጂታል ዲፕሎማሲ ድረስ ዕምቅ ታሪክና ተሞክሮ ያላት ሀገር ነች:: በእነዚህ የዲፕሎማሲ ሂደቶች ኢትዮጵያ በውጭው ዓለም ገናና ሆና እንድትታይና ሉላዊነቷና አንድነቷ ተጠብቆ እንዲቆይ ያስቻሉ ስራዎች ተከናውነዋል::

በየዘመናቱ የነበሩ የኢትዮጵያ መሪዎችም ሀገሪቱን ከውጭውም ዓለም ጋር የሰመረ ግንኙነት እንዲኖራትና አልፎ ተርፎም ተጽዕኖ ፈጣሪ ሀገር እንድትሆን ዘርፈ ብዙ ግኙኝቶችን ሲመሰርቱ ቆይተዋል:: ጥንታዊ ዲፕሎማሲ ከንግስት ሳባ የእስራኤል ጉዞ ጋር የተያያዘ ሲሆን በዘመነ አክሱም የዲፕሎማሲ ዘመንም የሁለትዮሽና የባለብዙ ወገን ዲፕሎማሲያዊ መሰረቶች ተጥለዋል:: ከእነዚህ መካከል በንጉስ ኢዛና ዘመን ንግድና ሃይማኖትን መሰረት ያደረጉ ግንኙነቶች ተፈጥረዋል::

ወደ መካከለኛው ዘመን ስንመጣ የዲፕሎማሲው ዋነኛ አቅጣጫ የሀገርን ሉአላዊነትና አንድነትን ማጽናት ነበር:: ኢትዮጵያ ከውስጥም ከውጭም የሚመጡባትን የሉአላዊነት አደጋዎች በመጋፈጥና አንድነቷን አስጠብቆ መሄድ የዲፕሎማሲው ቁልፍ አቅጣጫ ነበር:: በተለይም በሃይማኖትና በባህል ታጥሮ የቆው የዲፕሎማሲ ግንኙነት ወደ ንግድና ወታደራዊ ግንኙነት ያደገበት ጊዜ ነበር::

19ኛው ክፍለ ዘመን የአውሮፓና የኢትዮጵያ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ያንሰራራበት ዘመን ነበር:: ዘመኑም አውሮፓውያን የአፍሪካ አህጉርን በተጠናከረ ሁኔታ ማሰስ የጀመሩበት ጊዜ ነበር:: አውሮፓውያን በሳይንስ ምርምር እና በሚሽነሪዎች አማካኝነት የክርስትና ሃይማኖትን ለማስፋፋት ከፍተኛ ጥረት ያደርጉ ነበር:: በተጨማሪም ንግድን ማስፋፋት ሌላው ዓላማቸው ነበር::

በወቅቱ የነበሩት የኢትዮጵያ መሪ አጼ ቴዎድሮስ ሀገራችውን ከዘመነ መሣፍንት ትርምስ በመታደግ አንድነቷን ለማረጋገጥና ለማዘመን ራዕይ ሰንቀው መታገል ቢጀምሩም በሀገር ውስጥ የተጠናከረ አመጽ ስለተነሳባቸው ይህንኑ ለማስታገስ ላይ ታች የሚሉበት ጊዜ ነበር:: በተጨማሪም ከአውሮፓ የመጡ የሃይማኖት ሰባኪዎች ጋር ግብግብ በመግጠም ለሀገራቸው የሚያስፈልጋት የቴክኖሎጂ ፈጠራ ስራዎችን ማስፋፋት እንጂ የሃይማኖት ትምህርትማ እዚህ ያሉት የኔ ሰዎች ምን ይሰራሉ በማለት ይሞግቱ ነበር::

የኢትዮጵያ የውጭ ግንኙነት ጉዳይ ታሪክ ሲታወስ በዓለም አቀፍ ብሎም በአፍሪካ ደረጃ የተከናወኑትን ወሳኝ የዲፕሎማሲ ክስተቶች፣ ከራሷ አልፋ የአፍሪካ ጥቅም አስከባሪ ሆነው ከሚነሱ ሀገሮች ቀዳሚውን ቦታ የሚሰጣት ሀገር ነች::

ለአብነት እንኳ ከ1960ዎቹ ዓ.ም. መነሻ ጀምሮ ኢትዮጵያ ለበርካታ የአፍሪካ ፀረ ቅኝ ግዛትና ፀረ አፓርታይድ እንቅስቃሴዎች ትልቅ ፖለቲካዊ ድጋፍ በመስጠት የምትታወቅ ሲሆን፣ በቀድሞው ፕሬዚዳንት መንግሥቱ ኃይለ ማርያም ዘመን በደቡብ አፍሪካ፣ በዚምባቡዌና፣ በናሚቢያ ለነበሩ ነፃ አውጪ ድርጅቶች ወታደራዊ ሥልጠና፣ ቁሳዊና ዲፕሎማሲያዊ ዕርዳታዎች ያደረገችው አስተዋጽኦ ተሰንዶ ይገኛል::

በተጨማሪም ኢትዮጵያ አፍሪካን በመወከል በቡድን 20 እና ቡድን 8 ስብሰባዎች፣ እንዲሁም ደግሞ በአየር ለውጥ ድርድሮች፣ በአፍሪካና በቻይና የትብብር ፎረም፣ እንዲሁም በአፍሪካ፣ ህንድና ደቡብ ኮሪያ የትብብር መድረኮችና በበርካታ ዓለም አቀፍ መድረኮች ኢትዮጵያንና አፍሪካን ያልወከለችበት ጊዜ አልነበረም::

የውጭ ግንኙነት ዋነኛ ማጠንጠኛ የሆነውና በሥራ ላይ ያለው ኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ በሀገር ውስጥ በሚታዩ የፖለቲካ ውይይቶችና የክርክር መድረኮች ውስጥ በብዛት በድክመት ሲቀርብ የማይስተዋል፣ የበርካታ ተዋንያንን ቀልብ የሚስብ የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ ስለመሆኑም ይነሳል::

የኢትዮጵያ የውጭ ግንኙነት አጀማመር የረዥም ጊዜ ታሪክ ያለው ሲሆን፤ በተነፃፃሪ በይፋና በተደራጀ መልኩ ከውጭ ዓለም የተጀመረው ግን በአፄ ቴዎድሮስ ዘመን፣ በ19ኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ አካባቢ እንደሆነ መረጃዎች ይጠቁማሉ:: በዚህ ወቅትም የመጀመሪያው ሊባል የሚችልና በተለይም በአፍሪካ ቀንድ ቀጣና ላይ ያተኮረ የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ መሰል ሰነድ ተዘጋጅቶ በተግባር ላይ የዋለ እንደነበር በታሪክ ተመራማሪዎች የተደረሰበት ሲሆን፣ ይኼም በዚያን ጊዜ ሀገሪቱን ከማዘመን ጋር የተሠራ ታላቅ ሥራ ተደርጎ በወቅቱ ተወስዷል::




ከአፄ ቴዎድሮስ በኋላ የመጡት ዮሐንስ አራተኛም ምንም እንኳን በአውሮፓያውያን ተስፋፊነትና በጣሊያን ሰርጎ መግባት የተነሳ ከግራም ከቀኝም የተወጠሩበት ሁኔታ ቢኖርም፣ መለስተኛ በሆነ ደረጃም ቢሆን የአፄ ቴዎድሮስን የውጭ ፖሊሲ ለማስቀጠል ጥረት ማድረጋቸውን ታሪክ መዝግቦታል:: እ.ኤ.አ. በ1889 አፄ ዮሐንስን የተኩትና በ1913 ያረፉት አፄ ምኒልክ ጣሊያንን በወቅቱ የባህላዊ ዲፕሎማቲክ ሥልት በሆነው በምልጃና በሽምግልና ማሳመንና ከሀገር ማስወጣት ባለመቻላቸው፣ አይቀሬው ዘመቻ ተከስቶ እ.ኤ.አ. በ1896 የመጀመሪያውን የዓድዋ የጦርነት ድል ሊያደርጉ ችለዋል::

እ.ኤ.አ. ከ1913 ጀምሮ ብዙም የጎላ ዲፕሎማቲክ ክስተት ሳፈጠር ቆይቶ የኢትዮጵያ የውጭ ግንኙነት በተለይም የውጭውን ዓለም አሠላለፍ በመቃኘት በአዲስ መልክ የተጀመረው እ.ኤ.አ. በ1930 አፄ ኃይለ ሥላሴ ከነገሡበት ጀምሮ ነው:: በወቅቱም ሀገሪቱ ሥርዓት ያላት፣ ጠንካራና ዓለም አቀፋዊ ሕጎች ተገዢ እንደሆነች በተለያዩ መንገዶች ማሳየት ጀመሩ:: የንጉሠ ነገሥት ዘመናቸውን ሳይጀምሩ እንኳን ገና አልጋ ወራሽ በነበሩበት ወቅት ሀገሪቱ የመንግሥታት ሊግ ( ሊግ ኦፍ ኔሽን) አባል እንድትሆን እ.ኤ.አ. በ1923 ተደራድረው መሥራች እንድትሆን አስችለዋታል::

እ.ኤ.አ. ከ1936 እስከ 1941 ድረስ የጣሊያን ወረራ እክል ሆኖ፣ ባያደናቅፍና ሒደቱን ባይቀለብስ ኖሮ ኢትዮጵያን በዓለም የፖለቲካ አሰላለፍ ጉልህ ሥፍራ እንዲኖራት የጀመሩት ጥረት ይሳካላቸው እንደነበር ብዙዎቹ ይስማሙበታል:: ይህ እውን ባይሆንም ጣሊያን ተሸንፎ ከወጣ፣ እሳቸውም ከግዞት ከተመለሱና እ.ኤ.አ. በ1941 እንደገና የንግሥና መንበራቸውን ከያዙ በኋላ የጀመሩትን ሀገሪቱን ከቀሪው ዓለም ጋር የማስተሳሰሩ፣ አቋሟን የመገንባትና ተሰሚነትን የማግኘት ጥረታቸውን ቀጥለዋል::

አፄ ኃይለ ሥላሴ ከሁለተኛው ጦርነት በኋላ በተለይም በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ውስጥ መታወቅ በመጀመራቸው፣ ከምእራባዊያን ጋርም መቀራረብ በመፍጠራቸውና ለአፍሪካ ሀገሮች ነፃነት ድምፅ ማሰማት በመጀመራቸው በወቅቱ ከአፍሪካ ሀገሮች ሁሉ የተለየ ተደማጭነትንና ተቀባይነትን ማግኘት ችለዋል:: በጋራ ጉዳዮችም ላይ በግንባር ቀደምነት ከሚሰለፉ ተርታ ሀገሪቱን ለማሰለፍ በቅተዋል::

በጋራ የሰላምና ደኅንነት ተሳትፎ እንደ አብነት የሚጠቀሰውም እ.ኤ.አ. ከ1951 እስከ 1953 የኮሪያ ጦርነት ወቅት አትዮጵያ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ጥላ ሥር ከአፍሪካ አገሮች የመጀመሪያዋ እግረኛ ወታደር ላኪ ሀገር ሆና መሳተፍዋ ነው:: በወቅቱ አሥራ ስድስት ሀገሮች ብቻ ነበሩ ለተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የፀጥታው ምክር ቤት ውሳኔና ጥሪ ምላሽ የሰጡት። በዚህ ጦርነት ኢትዮጵያ 6,037 ወታደሮች ያሳተፈች ሲሆን፣ በ235 የውጊያ ግንባሮች ተሳትፋ ሁሉንም አሸንፋለች:: በጦርነቱ 121 ወታደሮች የተሰው ሲሆን፣ በመጨረሻ በጦርነቱ ማብቂያ በተደረገው ማጣራት የጦር ምርኮኛና እስረኛ ያልነበራት ብቸኛ ሀገር ኢትዮጵያ እንደሆነች በታሪክ ተመዝግቦ ይገኛል:: በተጨማሪም እ.ኤ.አ. በ1960 ለኮንጎ የሰላም ማስከበር የሰላም አስከባሪ ሠራዊት በመላክ ተሳትፎ ተደርጓል::

ከዚህ በመነሳትም በተባበሩት መንግሥታትም ድርጅትም ይሁን በኃያላን ሀገሮች የተገኘውን አዎንታዊ ድጋፍና ትኩረት መሠረት በማድረግም፣ የአፍሪካ ሀገሮች ነፃ የሚወጡበት ሁኔታ የማመቻቸት ሥራ ንጉሡ ሠርተዋል:: በዚህም መሠረት የአፍሪካውያን የነፃነት ጉዳይ በአጀንዳነት ተይዞ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት መድረክ ውይይት እንዲካሄድበት ከማስቻል ባሻገር፣ የፀጥታው ምክር ቤት ውሳኔ እንዲያስተላልፍ ያላሰለሰ ጥረትና ግፊት አድርገዋል:: በዚህም የአፍሪካ ልሳን ተብለው የተጠቀሱ የመጀመሪያ የሀገር መሪ ለመሆን አስችሏቸዋል::

በወቅቱም የፓን አፍሪካኒዝም ጽንሰ ሃሳብና መርህ ውስጥ ለውስጥ ሲሠራበትና ሲመከርበት የነበረ በመሆኑ፣ ይኼንን በተደራጀ መንገድ ለማካሄድና ለማስተባበር እንዲረዳ የአፍሪካ አንድነት ጽሕፈት ቤትን ማቋቋም አስፈላጊ እንደሆነ የማስተማር ሥራን ንጉሡ ሠሩ:: ከፍተኛ የማሳመን ተግባራትን በማከናወን የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ጽሕፈት ቤት (OAU) በአዲስ አበባ እ.ኤ.አ. በ1963 ተመሠረተ:: ይኼም የንጉሡን ዲፕሎማሲያዊ ሥራዎች ብቃትና ውጤት አረጋገጠ:: በአፍሪካ መሪዎች በኩል ተቀባይነትንና ከበሬታን፣ በዓለም መሪዎች በኩል ደግሞ አድናቆትንና ዕውቅናን እንዲያገኙ አስቻላቸው።።

በአጠቃላይ በባለብዙ ወገን የዲፕሎማሲ ታሪካችን በጥንካሬ የሚታወሱ የስኬት ታሪኮች እንዳሉን ሁሉ ከባድ ፈተናዎችንም የተጋፈጥንበት በርካታ ጊዜያት አልፈዋል። ከላይ እንደተገለፀው የፋሽስት ጣሊያን መንግሥት ለሁለተኛ ጊዜ ኢትዮጵያን በኃይል በወረረ ጊዜ የሀገራችን የግዛት አንድነት እና ሉዓላዊነት እንዲከበር የዓለም መንግሥታት ከጎናችን እንዲቆሙ ለማድረግ በመንግሥታቱ ማህበር የኢትዮጵያ ዋና ፀሐፊነት በተወከሉት በአቶ አክሊሉ ሀብተወልድ እና በኢትዮጵያ የጄኔቫ ዴሊጌሽን መሪ ፊትአውራሪ ተክለሐዋሪያት ተክለማርያም አማካኝነት ሰፊ የዲፕሎማሲ ተጋድሎ ተደርጓል።

ሆኖም ኢትዮጵያ የተፈፀመባት ግፍ በዓለም ሀገራት በቂ ትኩረት ካለማግኘቱም በላይ የመንግሥታቱ ማህበርም የመበታተን እጣ ፈንታ ገጥሞታል። ድርጅቱ የሞተው ኢትዮጵያ ላይ በያዘው ፍርደ ገምድል አቋም ነበር:: እዚህ ላይ የቀዳማዊ ኃይለስላሴ የጄኔቭ ንግግር ይታወሳል:: በወቅቱ የድርጅቱ ዝም ብሎ ተመልካችነት፣ የጣሊያን ተወካዮች ግብረ ገብነት የጎደለው ተግባርና የንጉሱ የሁኔታ አያያዝ ብልሃት አንገትን ቀና የሚያስደርግ ዲፕሎማሲያዊ አካሄድ ነበር::

ከንጉሡ በኋላ የመጣው ወታደራዊው የደርግ ሥርዓት ኢትዮጵያን በአድኃሪያን የአረብ ሀገራትና ሶማሊያን በመሰሉ ተንኳሽ ጎረቤቶች የተከበበች ደሴት ናት ብሎ ስለሚያስብ፤ ኢትዮጵያ ከጎረቤት ሀገራት ጋር የነበራት ግንኙነት በትብብርና በወዳጅነት መንፈስ ሳይሆን በጥርጣሬ፣ በፉክክርና በጣልቃ ገብነት ላይ የተመሰረተ ነበር።

በሶሻሊስታዊ ርዕዮተ ዓለምና በሶሻሊስት ጐራ አጋርነት የተቃኘው የደርግ መንግሥት የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ከሶሻሊስት ሀገራት ወታደራዊ ድጋፍን በማስገኘት ረገድ የተሳካ ነበር ማለት ቢቻልም፣ ጉልህ የሆነ የኢኮኖሚ ድጋፍ በማስገኘትና የኢትዮጵያን ልማት በመደገፍ ረገድ ግን ስኬታማ ነበር ለማለት አያስደፍርም:: በዚህም ኢትዮጵያ ከአሜሪካና ከምዕራብ አውሮፓ ሀገሮች ጋር የነበራት ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት እጅግ የተዳከመበትና ከአንዳንዶቹ ጋርም ግንኙነቱ ሙሉ በሙሉ የተቋረጠበት ነበር::

በተጨማሪም ከአብዛኞቹ ጎረቤት ሀገራት ጋር በአለመተማመን መንፈስ፣ በግጭትና በጣልቃ ገብነት የታጀበው ግንኙነት ውጤቱ ለሁሉም አክሳሪ እንደነበር ከደርግ አስተዳደር ውድቀት ማግስት የታዩ ቀጣናዊ ክስተቶች አመላካች ናቸው። በአጠቃላይ ደርግ የተከተለው ርዕዮተ ዓለማዊ ጎራ የለየ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ፣ የቀዝቃዛው ጦርነት ባስከተለው ዳፋ እና በሌሎች ተያያዥ ምክንያቶች ከምዕራባውያኑ በተለይ ከአሜሪካ ጋር የነበረው ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት መቋረጥን ተከትሎ ሀገራችን የውክልና ጦርነቶች መቆራቆሻ ሜዳ በማድረጉ ኢትዮጵያ ብሄራዊ ጥቅሞቿን እንድታጣና ብዙ መከራና ችግርን እንድታስተናግድ ሆኗል::

የኢህአዴግ ወደ መንግሥት ስልጣን መምጣት ከዓለም አቀፍ ሥርዓት መቀየር ማለትም የሶሻሊስት ጎራው መበታተን፣ የቀዝቃዛው ጦርነት ማክተም እና አሜሪካ መራሹ የዓለም ሥርዓት ጅማሮ ጋር መገጣጠሙ ለኢህአዴግ የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ እንደ አንድ መነሻ ግብዓት መሆኑ አይቀሬ ነው:: ስለሆነም ኢህአዴግ የቀረፀው የኢትዮጵያ ውጭ ጉዳይ ፖሊሲ የቀዝቃዛው ጦርነት ማብቃትን ተከትሎ ዓለማዊ ፖለቲካው በነጻ ገበያ/ካፒታሊዝም መንሰራፋት፣ በክልላዊ ውህደት መስፋፋት፣ በሉአላዊ የኢኮኖሚ ትስስር መጠናከርና በመልክአ-ፖለቲካ ፍላጎቶች (Geopolitical interests) ፉክክሮች ጎልቶ መውጣት ዓውድ ውስጥ የተቃኘ ነው ለማለት ይቻላል።

በ 2010 ዓ.ም የመጣው የጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ መንግሥት "የኢትዮጵያ የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ ብሔራዊ ጥቅምን ባስጠበቀ መልኩ እንዲካሄድ እየሰራ እንደሆነ ይናገራል። ዜጋ ተኮር ዲፕሎማሲ፣ የአረንጓዴ ዲፕሎማሲ፣ ዲጂታል ዲፕሎማሲና የሀገር ውስጥ ዲፕሎማሲ በዋናነት በለውጡ መንግሥት የሚተገበሩ የዲፕሎማሲ መርሆዎች ናቸው።

አዲሱ ዲፕሎማሲ በ2010 ዓ.ም በኢትዮጵያ የመጣውን ለውጥ ተከትሎ አዲሱ መንግሥት ተለዋዋጭ ለሆነው ዓለም አቀፍ ግንኙነት የሰጠው ዲፕሎማሲያዊ ምላሽ ነው:: በዚህም መንግሥት በአፍሪካ ቀንድ ቀጣና ውስጥ ከሚገኙ ወዳጅ እና ጠላት ሀገራት ጋር ያለውን ግንኙነት ሰላምን ማዕከል በማድረግ ትልቅ እና ተምሳሌታዊ የዲፕሎማሲ ሥራ የተሰራበት ሲሆን፤ በዚህም በቀጣናው ኢትዮጵያ ከኤርትራ ጋር ግንኙነቷን በዋናነት ያሻሻለችበት የዲፕሎማሲ ሥራ ነበር::

ከላይ የተዘረዘሩ የኢትዮጵያን የውጭ ግንኙነት የሚመለከቱ ጉዳዮች በዋነኝነት የተከናወኑት ከተመሰረተ 116 ዓመታትን ባስቆጠረው የኢፌዴሪ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር መስሪያ ቤት አማካኝነት ነው። ከዘመንና ጊዜ ጋር አብሮ የሚራመድ ሆኖ የዘለቀው የኢፌዴሪ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ለኢትዮጵያ ሀገር መንግሥት ግንባታ የነበረው ሚና ጉልህ ሆኖ የሚታይ ነው።

በዘመናት መካከል ለሀገርና ለህዝብ ትልቅ ትርጉም ያላቸው የኢትዮጵያ የዲፕሎማሲና የውጭ ግንኙነት ሥራዎች ሲከወኑበት ቆይተዋል። እኛም ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ለሀገር ያበረከተውን እጅግ ከፍ ያለ አበርክቶ ከግምት ውስጥ በማስገባት በዚህ ለሀገርና ለህዝብ የሰሩ ግለሰቦችና ተቋማት በሚወደሱበት የባለውለታዎቻችን ገፅ ሥራዎቹን በማንሳት አመሰገንን።

# ስፖርት

## ትውልዱን ከማንነቱ የሚያስተዋውቅ የባሕል ስፖርት ሻምፒዮና እና ፌስቲቫል

ብርሃን ፈይሳ



ከታኅሣሥ ወር አንስቶ በጥር፣ በሚያዚያ እስከ ክረምቱ መግቢያ ድረስ መኸር በተሰበሰበበት ሜዳ የተለያዩ ጨዋታዎችንና የእርስ በእርስ ፉክክር ማድረግ በአብዛኛው የኢትዮጵያ ገጠራማ አካባቢዎች የተለመደ ነው:: እነዚህ ጨዋታዎች ዛሬ ላይ ለሚዘወተሩት ዘመናዊ ስፖርቶች መሠረት ቢሆኑም፤ ከዘመኑ ጋር እየተበረዘ፣ በወጣቱ ዘንድ ያለው ተዘውታሪነትም እየቀነሰ መምጣቱ እርግጥ ነው:: በመሆኑም ትውልዱን ወደ ማንነቱ ለመመለስ ወቅቱን ጠብቆ ባሕላዊ የስፖርት ውድድሮችን በክልሎች፤ እንዲሁም በሃገር አቀፍ ደረጃ ማካሄድ የተለመደ ነው::

ከባሕላዊ ውድድሮች ጎን ለጎንም የባሕል ፌስቲቫል በማዘጋጀትም እሴቱን ከማሳደግ ባለፈ ከትውልዱ ጋር የማስተዋወቅ ሥራም ይሠራል:: 20ኛው የመላው የኦሮሚያ ባሕል ስፖርት ሻምፒዮና እንዲሁም 16ኛው የባሕል ስፖርት ፌስቲቫልም ይህንኑ መሠረት በማድረግ በአምቦ ከተማ በመካሄድ ላይ ይገኛል:: ለቀናት በሚዘልቀው በዚህ ሻምፒዮና ላይም 20 ዞኖችና 13 ከተማ አስተዳደሮች ተወካዮቻቸውን እያፎካከሩ ይገኛሉ:: 1ሺህ 80 የሚሆኑ ተወዳዳሪዎች በባሕል ጨዋታዎቹ ላይ እየተሳተፉ ሲሆን፤ 3ሺህ 800 የሚሆኑት ደግሞ በባሕል ፌስቲቫሉ ላይ ተካፋይ ናቸው::

ውድድሩም በሃገር አቀፍ ደረጃ ዕውቅና ካገኙ የባሕል ጨዋታዎች መካከል በ10ሩ ይካሄዳል:: በፌስቲቫሉ ደግሞ በባሕላዊ አልባሳትና ጌጣጌጣቸው አምረው የተገኙት ተሳታፊዎች የጭፈራ እና የአመጋገብ ሥርዓታቸውን በማሳየት እርስ በእርሳቸው ይፎካከራሉ:: ዘንድሮ ለ21ኛ ጊዜ የኢትዮጵያ ባሕል ስፖርቶች ሻምፒዮና በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አዘጋጅነት የሚካሄድ ሲሆን በዚህ ሻምፒዮና ላይ ክልሉን ወክለው የሚሳተፉ የባሕል ስፖርት ተወዳዳሪዎችን መምረጥ የሻምፒዮናው ቀዳሚ ዓላማ ነው:: ሕዝቡ የራሱን ባሕል መግለጽ እንዲችል፤ እንዲሁም በክልሉ የሚገኙ ዞኖች ትውፊታቸውን ለሌላኛው ዞን በማስተዋወቅ እርስ በእርሳቸው ያላቸውን ግንኙነት ለማሳደግም ጠቃሚ ነው:: በሌላ በኩል ከሥልጣኔና ዘመናዊነት ጋር በተያያዘ ስለ ባሕሉ ያለው ግንዛቤ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተመናመነ የመጣውን ትውልድ ማንነቱን እንዲያውቅና ባሕሉን እንዲያሳድግ የሚጫወተው ሚና እጅግ ከፍተኛ ነው::

እንደሌሎቹ የኢትዮጵያ ክፍሎች ሁሉ የኦሮሚያ ክልልም በተለያዩ ባሕላዊ እሴቶች የበለጸገ መሆኑ ይታወቃል:: ነገር ግን ከዚህ ቀደም በዘርፉ የነበረው ሁኔታ ወደ ኋላ የመቅረት አዝማሚያ የታየበት እንደነበረ የሚያስታውሱት፤ በኦሮሚያ ክልል የባሕል ስፖርት ፌዴሬሽን ጽሕፈት ቤት ኃላፊ አቶ በቀለ ኢራሱ ናቸው:: በመሰል ውድድሮች ላይም በባሕል ልብስ ተውቦ መገኘት ያልተለመደ ነበር:: ፌዴሬሽኑም ይህንን በመገንዘብ በመተዳደሪያ ደንቡ ላይ የውድድር ተወዳዳሪዎች ወደ ሜዳ ሲገቡ ባሕላቸውን በሚያንጸባርቅ አልባሳት መቅረብ እንዳለባቸው በመደንገጉ፤ እንዲሁም ፌስቲቫሉም እንዲካሄድ በመደረጉ አስደናቂ ለውጦች ታይተዋል:: ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን ስፖርቱን የሚመራው የክልሉ ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ትኩረት በመስጠትና ድጋፍ በማድረግ የባሕል ስፖርት ጽሕፈት ቤት እንቅስቃሴ እንዲያንሰራራ አድርጓል:: በዚህም የተሳታፊ ዞኖችን፣ እንዲሁም ተወዳዳሪዎችን ቁጥር በማሳደግ የመላ ኦሮሚያ ሻምፒዮና ሊሆን ችሏል::

በሃገር አቀፍ ደረጃ በሚካሄደው ሻምፒዮና ላይም ክልሉ ጠንካራ ተፎካካሪ በመሆኑ ከደረጃ ወርዶ እንደማያውቅ ኃላፊው ይጠቁማሉ:: በቅርቡ የሚካሄደውን ሻምፒዮናም በበላይነት ለማጠናቀቅ ታቅዶ እየተሠራ ይገኛል:: ክልሉ በተለይ ከሚታወቅባቸው የባሕል ስፖርቶች መካከል አንዱ የፈረስ ስፖርት ነው:: ይህን የፈረስ ሃብት በትልቅ ደረጃ ለማስተዋወቅና ስፖርቱን ለማሳደግ የተጀመረ ፕሮጀክት ነበር:: ይኸውም የተለያዩ ማኅበራትን በማቋቋም በሰባቱ የፈረስ ስፖርቶች በየዓመቱ ውድድር እንዲካሄድ እየተደረገ መሆኑንም አቶ በቀለ ያብራራሉ:: አሁን ካለበት በይበልጥ እንዲያድግና ስፖርቱ እንዲስፋፋም እንደ ክልል አቅጣጫ የተያዘ ሲሆን፤ በቀጣይም ማኅበራትን በማደራጀት ይሠራል::

ነገር ግን የማንነት መገለጫ የሆነው ይህ ስፖርት አሁንም በይበልጥ እየተዘወተረ የሚገኘው በገጠራማ አካባቢዎች ነው:: በከተማ አካባቢዎች ያለው እንቅስቃሴ ደካማ የሚባል ነው:: በእርግጥ ቀድሞ ተሳታፊ ያልነበሩ ክልሎች በቅርቡ ተወዳዳሪዎችን መላክ ስለጀመሩ ጥቂት ለውጥ መጥቷል ማለት ቢቻልም፤ በታዳጊዎች ዘንድ ግን ምንም አልተሠራም በሚያስብል ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ኃላፊው አልሸሸጉም:: በመሆኑም የባሕል ስፖርትና ፌስቲቫልን በክልል ደረጃ ከማካሄድ ባለፈ በየዞኑና በወረዳ እንዲካሄድ በማድረግ ኅብረተሰቡን ተደራሽ ለማድረግ እየተሠራ ነው:: በዚህም ስፖርቱን ማሳደግና ወጣቱም ባሕሉን እንዲያውቅ ለማድረግ እንደሚቻልም ተስፋ ተደርጓል::